ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

# ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዷዊ ጥናት

( በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

ግዛቸው አግማሴ

መስከረም፣2014 ዓ.ም

ጅማ፣ኢትዮጵያ

# ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዷዊ ጥናት

( በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት )


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል


ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አማርኛን በማስተማር ኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች በከፊል ማሙያነት የቀረበ ጥናት


በ

ግዛቸው አግማሴ

ዋና አማካሪ፡- ሙሃመድ ጀማል

ረዳት አማካሪ፡- ኤባ ተሬሳ (ዶ/ር )


መስከረም፣2014 ዓ.ም

ጅማ፣ኢትዮጵያ

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍልውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዷዊ ጥናት በሚል ርእስ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በግዛቸው አግማሴ የቀረበው ይህ ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና ወጥነት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት

የአማካሪ ስም……………………………ፊርማ..................ቀን....................

የውጭ ፈታኝ ስም፡ …………………… ፊርማ...................ቀን......................

የውስጥ ፈታኝ ስም፡ ……………………ፊርማ...................ቀን...................

## ማረጋገጫ

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል  ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዷዊ ጥናት፤ በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት፣ በሚል ርእስ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል  አማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ግዛቸው አግማሴ

ፊርማ…………...............

ቀን.......................

## ምስጋና

ይህን የመመረቂያ ጥናታዊ ጽሁፍ በሰራሁበት ወቅት ያለመሰልቸት በተደጋጋሚ በማረም፣ በማስተካከልና አቅጣጫ በመምራትም ሆነ በአጠቃላይ ይህን ትምህርት በስኬት እንድማር በአማካሪነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከቱት የጅማ ዩኒቨርስቲ መምህራን ሙሃመድ ጀማል እና ኤባ ተሬሳ (PhD) ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ መሳካት አስፈላጊውን ትብብርና መረጃ እንዲሁም ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው የተባበሩኝን  የልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የመካነ እየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች በሙሉ አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረሻም ሀሳብ በመስጠትና የኮምፒውተር ጽሁፉን በመጻፍ የተባበሩኝን ለባለቤቴ ለወ/ሮ ማናህሎሽ ነጋ እና ለልጄ ተማሪ ፍቅርተ ግዛቸው በመጨረሻም ለረዱኝ ቤተሰቦቼ ሁሉ አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**


ምስጋና............................................................... i
አህጽሮተ ጥናት ........................................................ vii
የቁልፍ ቃላትና ሃረጋት ብያኔ................................................ viii

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ................................................ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................ 4
1.3 የጥናቱ አላማ....................................................... 8
1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት (ጠቀሜታ) ........................................... 8
1.5 የጥናቱ ወሰን ....................................................... 9
ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ....................................... 10
2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ................................................... 10
2.1.1. አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምንነት......................................... 10
2.1.2 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ....................................... 11
2.1.3 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ዉስጥ መተግበር የሚያስገኘዉ ጥቅም .................. 13
2.1.4 የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ማስፈፀሚያ ስልቶች ................................ 14
2.1.4.1 በግል ስራ የመማር ማስተማር ዘዴ ........................................ 14
2.1.4.2 በጥያቄና መልስ የመማር ማስተማር ዘዴ..................................... 14
2.1.4.3 በክርክር የመማር ማስተማር ዘዴ ......................................... 15
2.1.4.4 በቡድን ውይይት የመማር ማስተማር ዘዴ ................................... 15
2.1.4.5 በመተባበር የመማር ማስተማር ዘዴ ........................................ 16
2.1.5 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያስችሉ ይዘቶች አመራረጥ ...................... 16
2.1.6 የስነ-ጽሁፍ ምንነት.................................................. 16
2.1.7 የቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ግንኙነት ምንድን ነው?....................................... 17
2.1.8. ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያላቸው አስተዋጽኦ............................ 18
2.1.9 ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውሉ የስነጽሁፍ ስራዎች አመራረጥ ............................ 20
2.1.9.1 የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ባገናዘበ መልኩ መምረጥ ................................ 20
2.1.9.2 የተማሪዎችን የስነ-ፅሁፍ ዳራዊ ዕውቀት ባገናዘበ መንገድ መምረጥ ......................... 21
2.1.9.3 ከስነ-ፅሁፋዊ ስራው ጋር የተያያዙ ሌሎች ነጥቦች...................................... 21
2.1.10 ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በመተግበር ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች ...... 21
2.1.10.1 የመፅሀፉን ይዘት ለማስተማር የተሰጠው ጊዜ ያለመመጣጠን ችግር፡-............................ 22
2.1.10.2 ለመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ያለመስጠት ችግር፡- .................................. 22
2.1.10.3 የክፍል ተማሪ ጥምርታ ያለመጣጣም ችግር፡-......................................... 22
2.1.10.4 ከማስተማሪያ መሳሪያዎችና ከስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች፡-......................... 23
2.1.11 የተማሪዎች ተሳትፎ.................................................. 23
2.1.12 መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ............ 24
2.1.13 መምህራን ተማሪዎችን ለማሳተፍ ማከናዎን ያለባቸው ተግባርት ........................ 25
2.1.13.1. ለሰፊ ልምምድ የሚጋብዙ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ..................................... 25
2.1.13.2 የተለያዩ ማበረታቻዎችን መጠቀም ............................................ 26

2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 27
ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ዘዴ........ 29
3.1 የተጠኝዎች አመራረጥ ........ 29
3.1.1 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ ........ 29
3.1.2 የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ ........ 29
3.1.3 የመምህራን የናሙና አመራረጥ ........ 30
3.1.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ ........ 30
3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 32
3.2.1 ምልከታ ........ 32
3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ ........ 33
3.2.3 ቃለ-መጠይቅ........ 34
3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 35
3.4. የመረጃ ትክክለኛነትና አስተማማኝነት........ 36
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ........ 38
4.1 የመረጃ ትንተና ........ 38
4.1.1 በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ተዛምዷዊ ትንተና ........ 38
4.1.1.1 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከስነጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና ........ 39
4.1.1.2 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከስነጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና........ 41
4.1.1.3 የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና ........ 43
4.1.1.4 የስነጽሁ ስራዎች አስተዋጽኦ ከጥገኛ ተላውጦዎች ጋር ያለው ተዛምዶትንተና........ 44
4.1.1.5 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ከስነጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለውተዛምዶ ትንተና........ 46
4.1.1.6 ስነጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና........ 47
4.1.1.7 አጠቃላይ በተላውጦዎች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ተዛምዶ ማሳያ ትንተና ........ 49
4.1.2 በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተዛምዷዊ ትንተና ........ 51
4.1.2.1 ከመምህራን በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ በተላውጦዎች መካከል የእርስ በርስ ተዛምዶ ትንተና........ 52
4.1.2.2 ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ በተላውጦዎች መካከል የእርስ በርስ ተዛምዶ ትንተና ........ 54
4.1.3 በክፍል ውስጥ ምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ ትንተና፡፡........ 55
4.1.3.1 በክፍል ውስጥ ምልከታ በቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች በቁጥርና በመቶኛ ትንተና፡፡........ 56
4.1.3.2. ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋዉን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ........ 58
4.1.3.3 የስነጽሁፍ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው አስተዋጽኦ........ 60
4.1.3.4 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ........ 61
4.1.3.5 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ........ 62
4.1.3.6 በጽሁፍ መጠይቅ በቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች በቁጥርና በመቶኛ ትንተና........ 63
4.1.3.7 ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋዉን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ........ 65
4.1.3.8 ስነጽሁፋዊ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው አስተዋጽኦ ........ 67

4.1.3.9 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ............... 69
4.1.3.10 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ................. 71
4.1.3.11 በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች አጠቃላይ የሆነ የውጤት ትንተና ........................................ 72
4.1. 3.12 በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ትንተና ........................................ 74
4.2 የውጤት ማብራሪያ........................................ 79
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ ........................................ 83
5.1 ማጠቃለያ........................................ 83
5.2 መደምደሚያ ........................................ 84
5.3 የመፍትሔ ሀሣብ........................................ 85
ዋቢዎች (References) ........................................ 87

አባሪ ሀ ........................................90

አባሪ ለ ........................................94

አባሪ ሐ........................................98

አባሪ መ........................................99

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ3.1፦ በናሙናነት የተመረጡ ክፍሎች (ሴክሽኖች)ና የተማሪዎች ብዛት ............. 31

ሰንጠረዥ 4.1 የስነጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ እና የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር መካከል ያለው ተዛምዶ ትንተና ........................................................................................ 40

ሰንጠረዝ4.2 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከስነጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና ................................................................. 42

ሰንጠረዝ4.3 የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ትንተና .......... 43

ሰንጠረዥ4.4 የስነጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ከንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች ጋር ያለው ተዛምዶ ........................................................................................ 45

ሰንጠረዥ4.5 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ከስነ-ፅሁፋዊስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና .................................................. 46

ሰንጠረዥ4.6 ስነጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና.................. 48

ሰንጠረዥ4.7 በተላውጦዎች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ተዛምዶ ማሳያ ...................... 50

ሰንጠረዥ4.8 ከመምህራን በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ አጠቃላይ የሆነ በተላውጦዎች መካከል ያለው የእርስ በርስ ተዛምዶ ትንተና ...................... 52

ሰንጠረዥ4.9 ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ አጠቃላይ የሆነ በተላውጦዎች መካከል ያለው የእርስ በርስ ተዛምዶ ትንተና..........................................54

ሰንጠረዥ4.10 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር በቁጥርና በመቶኛ ስልት ......................................................................................... 57

ሰንጠረዥ4.11 ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋ ዊስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋዉን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምንይ መስላል? .................................................... 59

ሰንጠረዥ4.12 የስነጽሁፍ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? ......................................................................................... 60

ሰንጠረዥ4.13 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ ምን ይመስላል? .................................................................... 61

ሰንጠረዥ4.14 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ምንድን ናቸው? ......................................................................... 62

ሰንጠረዥ4.15 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ምን ይመስላል?................ 63

ሰንጠረዥ4.16 ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋዉን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን ይመስላል?................................................... 66

ሰንጠረዥ4.17 የስነጽሁፍ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? ......................................................................................... 68

ሰንጠረዥ4.18 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ ምን ይመስላል? ......................................................................... 70

ሰንጠረዥ4.19 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ምንድን ናቸው?............................................................................ 71

ሰንጠረዥ4.20 በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች አጠቃላይ የሆነ የውጤት ትንተና ......................................................................... 73

# *አህጽሮተ ጥናት*

*የጥናቱ ዋና ዓላማ መምህራን በ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎችን ተሳትፎ ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ይህን ዓላማ ለማሳካት የተመረጠው የምርምር ንድፍ አይነት መጠናዊ ሲሆን፤ገላጭ ተዛምዶዊ የምርምር ስልትን ተከትሏል።የጥናቱ ተሳታፊዎች በ2013 ዓ.ም በልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በመካነ ኢየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች ሲሆኑ፤ትምህርት ቤቶቹ በአመች የንሞና ስልት፣ 3 ወንዶችና 3 ሴቶች በድምሩ 6 መምህራን በጠቅላይ ንሞና ስልት እንዲሁም 90 ወንዶችና 90 ሴቶች በድምሩ 180 ተማሪዎችን ደግሞ በቀላል እጣ ንሞና ስልት ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋሉት ምልከታ፣ የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ-መጥይቅ ናቸው። የተሰበሰቡት መረጃዎች በSPSS ተተንትነው በመጠናዊና ገላጭ በሆነ ስልት ተብራርተዋል። በመረጃ ትንተናው መሰረትም የመምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር፣ ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር አዎንታዊና ጠንካራ የሆነ ተዛምዶ መኖሩን አሳይቷል፡፡ የስነጽሁፍ ስራዎች ጠቀሜታ እዲሁም የአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑን አሳይቷል፤ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ ስነጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዳሉ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡*

*በአጠቃላይ በመማር ማስተማር ግምገማ ዘርፍነት በቀረቡት ተላውጦዎች መካከል ያለው ግንኙነት የአብዛኞዎቹ ከ0.05 በላይ ሲሆን የጥንካሬ ደረጃቸው ይለያያል እንጅ ግንኙነት እንዳለም ታይቷል። በመቀጠል ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለማቃለል የመፍትሄ ሀሳብ ይሆናሉ ያሏቸውን አሰቀምጠዋል፡፡ በመጨረሻም ከተገኘው ውጤት በመነሳት ባለድርሻ አካላት የመምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ፣ ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር አዎንታዊና የጎላ ተዛምዶ ያለው መሆኑን ተገንዝበው መምህራንና ተማሪዎች የተለያዩ ልምድና ፍላጎት ሊኖራቸው እንደሚችል በመረዳት የትምህርት ይዘቶችን በተለያዩ ዘዴዎች በማቅረብ ተማሪዎችን በልዩ ልዩ ተግባራት ማሳተፍ ቢችሉ፣ እንዲሁም አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች በጥናቱ የተገለጸ በመሆኑ ችግሩን ለማቃለል የቁሳቁስ ድጋፍና የተማሪ ክፍል ጥምርታ ቢስተካከል የሚሉትን አስተያየቶች አጥኝው ጠቁሟል።*

# የቁልፍ ቃላትና ሃረጋት ብያኔ

ይህን ጥናት ለሚያነቡ አንባቢዎች የንባብ ሂደቱን ቀላል በማድረግ የተሟላ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማስቻል ታስቦ በጥናቱ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ቃላትና ሀረጋት ብያኔዎች በዚህ ንዑስ ክፍል ቀርቧል።

አሳትፊ ዘዴዎች፡- የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች በክፍል ውስጥ እንዲተገብሩ የሚያስችሉ የትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች ናቸው፡፡

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ፡- በመማር ማስተማር ሂደቱ በመምህሩ ታቅዶ የሚተገበር ሲሆን ተማሪዎች እርስ በእርሳቸዉና ከመምህራን ጋር በመተባበር የመማር ማስተማር ሂደቱን የተነቃቃና የተቀላጠፈ የሚያደርጉበት ዘዴ ነዉ፡፡

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር፡- ተማሪዎቹን የትምህርቱ ማዕከል ማድረግ ሲሆን የትምህርቱሂደትምተማሪዎችወደመማሪያክፍልከገቡጀምሮመምህራንየተማሪዎችንለውጥአስከ ሚገመግሙበት ያለውን ጊዜ ይይዛል ፡፡

የተማሪዎችተሳትፎ፡-ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በንቃት የሚያከናውኑትን ተግባር የሚያመለክትነው፡፡ ይኸውም ጥያቄ መጠየቅና ለጥያቄዎች መልስ መስጠት፣ አስተያየት መስጠት፣ የቡድን ውይይት መስራት፣ ለሚታዘዙት ተግባር ቀና የሆነ ስሜት መኖር፣የቤትና የክፍል ስራዎችን መስራትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ስነ-ጽሁፍ፡-በተለያዩ ቅርጾች በቋንቋ አማካኝነት የሚከሰት በቃልም ሆነ በጽሁፍ የሚገለፅ (ስነግጥምን፣ተውኔትን፣አጭር ልቦለድን፣የስነቃል ሀብቶችን)የሚያጠቃልል የፈጠራ ስራ ነው፡፡

ተዛምዶ፡-በተማሪዎችና በመምህራን ተግባራት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት የሚመለከትነው፡፡

# ምዕራፍ አንድ:- መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲፋጠን የበለጠ ደግሞ ቋንቋ መማር በተሻለ መንገድ ውጤታማ እንዲሆን ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ተግባር በንቃት ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ተገቢነት ያለውና መማርን የሚያበረታታ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም የመምህራን የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ውጤት አለው (Richards፣2001)፡፡ አሳታፊ የማስተማሬያ ዘዴ አተገባበር ተማሪዎቹን የትምህርቱ ማዕከል ማድረግ ሲሆን የትምህርቱ ሂደትም ተማሪዎች ወደ መማሪያ ክፍል ከገቡ ጀምሮ መምህራን የተማሪዎችን ለውጥ እስከ ሚገመግሙበት ያለውን ጊዜ ይይዛል (Tudor፣1993)፡፡ በመሆኑም አጥኝው ጥናቱን የሚያካሂደው ከሃገሪቱ የተማሪ ተኮር (ትምህርት ሚኒስቴር፣1989) የትምህርት ስትራቴጅክ ጋር ግንኙነት ያለውን የትምህርት ፍልስፍና መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ይህ ፍልስፍና በክፍል ውስጥ አግባብ ያለው የትምህርት መግቢያና ማጠቃለያ መስጠት፣ለትምህርቱ ይዘት ተገቢነት ያለውን የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም፣ አግባብነት ያላቸውን የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን መገልገል፤ እንዲሁም ተማሪዎች ለሚሰሯቸው ስራዎች ሁሉ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ አግባባዊ ምላሽ በወቅቱ መስጠት ተማሪዎች ለትምህርቱ ጥሩ የሆነ ፍላጎት እንዲያድርባቸው በማድረግ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም የመማር ማስተማሩን ተግባር ስኬታማ ለማድረግ መምህራን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያለባቸው ከትምህርቱ ይዘት ጋር ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ ይዞ በመገኘት መተግበር አለበት፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ትምህርቱን በትክክለኛው መንገድ እንዲማሩ ከመርዳቱም በላይ ለትምህርቱ ከፍ ያለ ግምት ሰጥተው በፍላጎት እንዲማሩት ለማድረግ እገዛ ያደርጋል Ur(1991) በማለት ይገልፃሉ፡፡

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን አተገባበር Silverman(1996) እንደየትምህርቱ አይነት ሊለያይ እንደሚችል ይገልጻሉ፡፡ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተዘውትረው ሲተገበሩ የሚታዩት አሳታፊ ዘዴዎች፡- ውይይት፣ ክርክር፣ ሥዕልን መተንተን፣ የፈጠራ ጽሁፍ ሥራና ድራማ የመሳሰሉት ሲሆኑ ከነዚህም በተጨማሪ መምህራን የትምህርቱን ይዘት ለማቅረብ አመች የሆኑትን የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችን መርጠው መጠቀም ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አሳታፊ ዘዴዎችን ለመተግበር የዘዴዎቹን አይነትና ባህሪ ማወቁ ብቻ ወደ ግብ አያደርስም፡፡ የተማሪዎቹ ቁጥር፣ የክፍሉ ሁኔታና የወንበሮቹ አደረጃጀት አተገባበሩን ይወስነዋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ

መተግበር በመማር ማስተማሩ ሂደት የአንድ ወገን እዉቀትና መረጃ አቅራቢ ብቻ ባለመሆኑ መምህራን የመማር ማስተማሩ አመቻቾች ሲሆኑ ተማሪዎች ደግሞ እንደማስተማሪያ ዘዴዎቹ በተናጥል፣ በጥንድ እንዲሁም በቡድን በመሆን የሚከራከሩበት፣ ድራማ የሚሰሩበት የክፍልና የቤትስራ የሚሰሩበት ወዘተ. በነጻነት የሚማማሩበት ዘዴ ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪዎቹን ተሳትፎ ለማጎልበት እንደትምህርቱ ይዘት የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍ ውስጥ ይዞ በመገኘት እንዲተገበሩ ማድረግ ከመምህራን የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

የቋንቋ ትምህርትን የመማር ማስተማር ተግባር በአንድ ወገን ብቻ ሊከዎን የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም ዓላማውን ከግብ ለማድረስና በቀላሉ ለማስረጽ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ Reed and Bergemann (1995) እንደገለጹት የመምህራን የክፍል ውስጥ የትምህርት አተገባበር በጣም አስፈላጊው የመማር ማስተማር ተግባር ተማሪዎችን በትምህርቱ ስራ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በትምህርቱ ስራ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ የመማር ማስተማሩ ተግባር ግቡን እንዲመታ ይረዳል፡፡ ይህም የተማሪዎቹን የቋንቋ ክሂልና እውቀት እንዲዳብር ያደርጋል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡

የተማሪዎች ተሳትፎ ማለት ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በንቃት የሚያከናውኑትን ተግባር የሚያመለክት ነው፡፡ ይኸውም ጥያቄ መጠየቅና ለጥያቄዎች መልስ መስጠት፣ አስተያየት መስጠት፣ የቡድን ውይይት መስራት፣ ለሚታዘዙት ተግባር ቀና የሆነ ስሜት መኖር፣ የቤትና የክፍል ስራዎችን መስራትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ Borich (2004) የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ መምህራን በክፍል ውስጥ ለገለፃ የሚያጠፉትን ረዥም ጊዜ በመቀነስ ተማሪዎች ሊሳተፉበት የሚያስችላቸውን ሰፊ የመዎያያ ጊዜ መስጠትና በተግባሩ እንዲሳተፉ በማድረግ የመማር ማስተማር ስራውን ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የመምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር በተማሪዎች መካከል የርእስ በርእስና ከመምህራቸው ጋር በሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያላቸውን ዕውቀት እንዲያሻሽሉ ያደርጋል፡፡በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ተግባር ተዋናኝ የሆኑት መምህራንና ተማሪዎች ተነጣጥለው የሚታዩ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም የተፈለገውን ለውጥ ለማምጣት የሁለቱ የተቀናጀ ተግባር መኖር ወሳኝነት እንዳለው ከምሁራን ሃሳብ እንገነዘባለን፡፡ ስለሆነም የትምህርት ስራ ተፈላጊውን የባህሪ ለውጥ ያስገኝ

ዘንድ የተማሪዎች ተሳትፎ መኖር እጅግ አስፈላጊ ነው። የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመጨመር ደግሞ መምህራን የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም ያስፈልጋል።

የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው። ተዛምዶ በተማሪዎችና በመምህራን ተግባራት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት የሚመለከት ነው። Elliott (2000) እንደገለጹት መማር በሚከዎንበት ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ ከመምህራን ተግባራት ጋር ተዛምዶ አለው። ይኸውም መምህራን በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባሮችን የሚያከናውኑ ከሆኑ የተማሪዎች ተሳትፎም ከፍተኛ ይሆናል ሲሉ ይገልፃሉ።

በክፍል ውስጥ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ለመተግበር አስፈላጊ ከሆኑት መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ የስነ-ፅሁፍ ስራ ነው። ስነ-ጽሁፍ በተለያዩ ቅርጾች በቋንቋ አማካኝነት የሚከሰት በቃልም ሆነ በጽሁፍ የሚገለፅ (ስነግጥምን፣ተውኔትን፣አጭር ልቦለድን፣የስነቃል ሀብቶችን) የሚያጠቃልል የፈጠራ ስራ በመሆኑ ስሜትን ይይዛል። ስለሆነም የተማሪዎችን ተሳትፎ ከፍ ያደርጋል። ይህን በተመለከተም Lazar(1993) ስነ-ጽሑፋዊ ስራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ተማሪዎችን እያዝናና ያስተምራል፤ ግላዊ ተሳትፎን ያዳብራል፤ ተማሪዉን በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበረታታል በማለት ይገልፃሉ።

በተጨማሪም በድሉ(2007) ስነ-ጽሁፍ ስሜትን የሚይዝና ቀልብን የሚገዛ የፈጠራ ስራ በመሆኑ ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግል መሳሪያ ነው። የተማሪዎች ተግባራዊ ተሳትፎ ከተመረጠው ስራ ሳቢመሆን አለመሆን ጋር ቀጥተኛ ዝምድና አለው። የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት ወጥሮ መያዝ የቻለ ስራ ሳቢ ነው። በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ተግባራዊ ድርሻ እንዲኖራቸው ያደርጋል። በቀረበው ስራ የተሳቡ ወይም በስራው ላይ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ስለስራው የበለጠ የማወቅ ጉጉት ይኖራቸዋል። ስለዚህ የበለጠ ለማወቅ በክፍል ውስጥ በሚከናዎነው ተግባር ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ።

በተጨማሪም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ውጤታማ ለማድረግ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚዘጋጁ መማሪያ መጽሀፍት ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ከተማሪዎች አቅምጋር አገናዝቦ በማቅረብ ዘዴውን ውጤታማ ማድረግ እንደሚቻል በአጽንኦት ገልፀዋል፡ ፡ ይሁን እንጂ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች እንዳሉም ሳይገልፁ አላለፉም። ይኸውም ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ለማስተማር ሲታሰብ ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል የስነ-ፅሁፍ

ስራዎችን በቅርብና በበቂ ሁኔታ ያለማግኘት ችግር ነው፡፡ይህ ችግር ግን ስነ-ፅሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ከመጠቀም ሙሉ በሙሉ ሊያግደን አይገባም፡፡ እንደችግሩ መምህሩ ያዘጋጁትን ቅንጫቢ ብቻ በመጠቀም የንግግር፣ የፅህፈት፣ የማዳመጥና ሌሎች የቋንቋ ትምህርትን ማስተማር ይቻላል በማለት ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ከነዚህ በላይ ከቀረበው የምሁራን ሃሳቦች በመነሳት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች እንዴት እንደሚተገበሩና ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለውን ተዛምዶ መመርመር ሲሆን ውጤቱ በተግባር ሲተረጎም መምህራን በሚተገብሩት የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎች ተሳትፎ ስኬታማ እንዲሆን በር የሚከፍት ጉዳይ እንደሚሆን ይታመናል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በክፍል ውስጥ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴዎችን ለመተግበር አስፈላጊ ከሆኑት መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ የስነ-ፅሁፍ ስራ እንደሆነ ቀደም ሲል በዳራው ላይ ተጠቁሟል፡፡ የሥነ-ጽሁፍ ስራዎችን ለቋንቋ ትምህርት ይሁነኝ ብሎ መሳሪያ ማድረግ የተጀመረው በ1980ዎቹ አካባቢ መሆኑን Carter and Long(1991)ያስረዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ስነፅሁፍን መሳሪያ ማድረግ ይህን ያህል እድሜ እንዳስቆጠረ ቢታዎቅም አሁንም ለቋንቋ ማስተማሪያነት ስነፅሁፍ አስፈላጊ ነው? የሚለው ጥያቄ ግን እያነጋገረ ነው ፡፡

ስነ ፅሁፍ ቋንቋን ከማስተማር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ በተለይ ከኮሌጂ በፊት ባለው የትምህርት ደረጃ ስነፅሁፍን ተማሪዎች እንዲማሩ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም የሚለው ሀሳብ ግንባር ቀደም የመከራከሪያ ርእሰ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩን የበለጠ አዎዛጋቢ ያደረገው ደግሞ የዘመናዊ ሥነልሳን መከሰት ነው፡፡ ዘመናዊ ሥነልሳን ከፅሁፍ ይልቅ የንግግር ቋንቋን ያስቀድማል፡፡ ሥነፅሁፍ ደግሞ በአብዛኛው በፅሁፍ የሚገለፅና የማይለዎጥ በቋንቋ የሚገለፅ ነገር ነው፡፡ በመሆኑም በዘመናዊ ሥነልሳን አተያይ ለቋንቋ ማስተማሪያ አስፈላጊ ባለመሆኑ በስርዓተ ትምህርት ሊካተት አይገባም ሲሉ Collie and Slater (1987) ያስረዳሉ፡፡

ይሁን እንጅ ይህን ሃሳብ በመቃወም ወንድወሰን (1995) ስነጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የማይሰጥበት አንዳችም ምክንያት የለም፡፡ እንዲያውም የማንኛውም የእውቀት መስክ ትምህርት ክብደት፣ ቅለቱ እየተመዘነ ደረጀውም እየተገመተ ከታች ጀምሮ በተከታታይነትና በተለጣጣቂነት በመስጠት ማደግ እንዳለበት የትምህርት ሳይንስ ይመክራል በማለት ይገልፃሉ፡፡

ከላይ ከተገለፁት አከራካሪ ሀሳቦች በመነሳት አሁን ቋንቋን ለመማር ማስተማር እየተሰጠ ካለው ስነጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ አንጻር ትክክለኛውን ሀሳብ ለመቀበል መፈተሽ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ በድሉ(1996) ደግሞ በኢትዮጵያ አሁን ባለው የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስነፅሁፍ ይህ ነው ተብሎ ሊገለፅ የሚችል ድርሻ የለውም በማለት ይገልፃሉ፡፡ ሥነፅሁፍ ለአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያነት ድርሻ የሌለው ከመርሃ ትምህርቱ ዝግጅት ወይስ አተገባበሩ? ከፍተኛውን ድርሻ የሚጫወተው መርሃ ትምህርቱ ወይስ ተግባሪው? የሚሉት ጥያቄዎች መነሳታቸው አይቀርም፡፡ አጥኝው አሁን ካለው ትክክለኛ እውነታ በመነሳት አስራ ሰባት ዓመታት ሲያስተምር ባስተዋለው የመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በአንደኛም ሆነ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የስነጽሁፍ ስራዎች በመርሃ ትምህርቱ ዝግጅት ያልተካተቱበት ጊዜ የለም፡፡ ነገር ግን አተገባበሩን በተመለከተ እያንዳንዱ መምህር ካለው ሙያዊ ብቃት አንጻር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴውን አተገባበር መፈተሽ ተገቢ ነው ብሎ ያምናል፡፡ አተገባበሩን በተመለከተም የተለያዩ ምሁራን ሃሳባቸውን ገልፀዋል፡፡

Bailey and Nunan (1996) እና Carter and Long (1991) እንደሚያስረዱት የአንድን ትምህርት ትግበራ የሚወስኑ ብዙ ተላውጦዎች ቢኖሩም መምህሩ ወሳኝ ነው፡፡መርሃ ትምህርት ዕቅድ ሲሆን ትግበራ ደግሞ ዕቅዱን ወደ ተጨባጭ ተግባር ለውጦ የማቅረብ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳን መርሃ ትምህርቱ በጥራት ቢዘጋጂም መምህሩ ዕቅዱን ወደ ተግባር ለመለወጥ ያለው ብቃት ወይም ግንዛቤ ዝቅተኛ ከሆነ ትግበራው ሊደናቀፍ ይችላል፡፡ የማስተማሩን ሂደት የመምራት፣ ተማሪዎችን የማደራጀት፣ የክፍልና የቤት ስራ የመስጠት፣ ተገቢ የሆነ ሥነ-ዘዴ የመጠቀም፣ መርጃ መሳሪያዎችን የማቅረብ፣ ምጋቤ ምላሽ የመስጠት ተግባር የመምህሩ በመሆኑ የትግበራውን ሂደት ስኬታማ ሊያደርገው ወይም ሊያደናቅፈው ይችላል፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው መምህሩ የትግበራውን ሂደት ስኬታማ ሊያደርገው ወይም ሊያደናቅፈው እንደሚችል ቢገለጽም፡፡ መምህራን ብቻ ክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ማከናዎናቸው የመማር ማስረማሩ ሂደት በጥሩ ሁኔታ ሊካሄድ አይችልም፡፡ መማር በሚከዎንበት ጊዜ ተማሪዎች የግዴታ በንቃት ሊሳተፉ ይገባል፡፡ ይህን በተመለከተ Elliott(2000) እንደገለጹት መምህሩ አስተማረ የሚባለው ትምህርቱን ስላቀረበ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችን በተግባሩ እንዲሳተፉ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎች ተሳትፎ መኖር አንዱና ዋንኛው የትምህርት ስኬት አመላካች በመሆኑ ነው፡፡መምህራን በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባሮችን የሚያከናውኑ ከሆነ የተማሪዎች ተሳትፎም ከፍተኛ ይሆናል በማለት ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በላይ የተገለጹትን ሁለት ሀሳቦች ስንመለከት ስነጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባራትን የሚያከናውኑት ዋናዎቹ መምህራን ወይስ ተማሪዎች? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ አጥኚው በሁለቱ መካከል ያለውን ተዛምዶ ምን እንደሚመስል መፈተሽ አስፈላጊ ነው ብሎ በማመኑ እንደአንድ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት አድርጎ ወስዷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ለማየት በተደረገው ሙከራ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ችግር ያለበት መሆኑን የሚያመላክቱ ጥናቶች ተገኝተዋል፡፡

Ethiopian National Agency For UNESCO (2001) በተደረገው ጥናት በኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው የትምህርት ማሻሻያ መርሀ ግብር የትምህርት ጥራት ችግር ያለበት መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በJICA (2012) የቀረበው ሪፖርት እንደሚያሳየው በ4ኛና በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በ2010 እ.ኤ.አ በተደረገው ሀገር አቀፍ ምዘና የተማሪዎቹ ውጤት ከትምህርት ሚኒስቴር የብቃት መመዘኛ በታች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራን ስለሚያስተምሩት የትምህርት አይነት በቂ ግንዛቤ የላቸውም፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከተለምዷዊው የማስተማር ዘዴ ወጣ ያለ አሰራርን የሚተገብሩበት ሁኔታም አይስተዋልም፡፡ሌለው ቀርቶ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን እንዴት እንደሚያስተምሩ አያውቁም (JICA,2012:v)፡፡ በጥቅሉ የትምህርት ጥራት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ የሄደበት ሁኔታ ይታያል (EGRA,2010 ፣JICA,2012 )፡፡

እነዚህ ጥናቶች የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበሩ ችግር ያለበት መሆኑን ቢዳስሱም የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለውን ተዛምዶ አልተመለከቱም፡፡ አለመመልከታቸው የተማሪዎች ተሳትፎ ከክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበሩ እንዴትነት ጋር ባለው ተዛምዶ ረገድ የምርምር ክፍተት መኖሩን ያመለክታል፡፡

ይኸውም የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ በመማር ማስተማሩ በኩል በጥሩ ሁኔታ እንዲከናዎን ለማድረግ የሚያስችል ከመሆኑ አንፃር የጋራ ግንዛቤን እንዲጨብጡ ለማድረግ በሚያስችል ጉዳይ ላይ ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ በምርምር ውጤቶች የተደገፈ የመማር ማስተማር ሂደት የሚተገበርበት ሁኔታ ክፍተት እንዲኖርበት ያደርጋል፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጥራት ላይም አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ በአጠቃላይ አጥኚው ባደረገው የንባብ አሰሳ ፡-

- ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ቋንቋን ለመማር ማስተማሩ ተግባር ባላቸው አስተዋጽኦ ላይ ሁለት ተቃራኒ ሀሳቦች በመነሳቱ አስተዋጽኦ አለው? ወይስ የለውም የሚለውን ጥያቄ መልስ ለማግኘት በጥናት መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘቡ፣
- መምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንዴት እንደሚተገበሩ መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘቡ
- የተማሪዎች ተሳትፎ ከመምህራን አተገባበር ጋር ያለው ተዛምዶ እንዴት እንደሆነ መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳቱ፣
- አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ መተግበር ያለውን ጠቀሜታና ሊያጋጥሙ የሚችሉ እንቅፋቶች ምን ምን እንደሆኑ መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳቱ አጥኝው ለጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች አድርጎ ተነስቷል፡፡

ስለዚህ ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ መሰረት በማድረግ ተካሂዷል፡ ፡ጥናቱ ይዟቸው የተነሳው ጥያቄዎችም፡-

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ምን ይመስላል? ]
2. ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን ይመስላል?
3. የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል ?
4. ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል ?
5. ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ምን ሊሆኑ ይችላል? የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ መምህራን በ2013 ዓ.ም በስራ ላይ ያለውን በ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎችን ተሳትፎ ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ከዚህ አጠቃላይ አላማ በመነሳት የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን አተገባበር መፈተሽ፣
- ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል መፈተሽ፣
- የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ፣
- ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ያላቸውን አስተዋጽኦ መፈተሽ፣
- ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ እንቅፋቶች ምን እንደሆኑ መፈተሽ እና የመፍትሄ ሀሳብ መፈለግ የሚሉት ናቸው፡፡

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት (ጠቀሜታ)

ይህ ጥናት በዋናነት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የተካተቱ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር እና በተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ከጥናቱ የሚገኘው ውጤት ለተማሪዎች፣ ለመምህራንና ለአጥኝዎች የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ከማስገኘት አንጻር አስፈላጊ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንዴት መተግበር እንዳለባቸው ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡
2. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ከመተግበር አኳያ ጥናቱ ከሚጠቁማቸው ሀሳቦች በመነሳት የማስተማሪያ ዘዴያቸውን እንዲቃኙ ይረዳል፡፡
3. በቋንቋ ትምህርት ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመተግበር ወቅት ለሚያጋጥሙ እንቅፋቶች የመፍትሄ ሀሳብ ይጠቁማል፡፡

4. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር እና የተማሪዎች ተሳትፎ ያላቸውን ተዛምዶ ጥቆማ ይሰጣል፡፡
5. በዚህ ርዕስ ዙሪያ በሰፊው ማጥናት ለሚፈልግ አካል እንደ መነሻ ሀሳብና ማጣቀሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ጎንደር ዞን በእስቴ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ሰባት የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በልዋዬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በመካነ ኢየሱስ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ብቻ ትኩረት አድርጓል፡፡ እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በአመች ንሞና ሲሆን ትምህርት ቤቶቹ የተመረጡበት ምክንያት ከተመራማሪው የስራ ቦታ ቅርብ በመሆናቸው የጥናቱን መረጃ ለማሰባሰብ ያለውን አመችነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ የተመረጡትም በነዚህ ትምህርት ቤቶች በ2013 ዓ.ም10ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡

ጥናቱ ሌሎች ትምህርት ቤቶችንና በእነዚህም ትምህርት ቤቶች ቢሆንም ሌሎች የክፍል ደረጃዎችንና የትምህርት አይነቶችን አያካትትም፡፡ ጥናቱ የተካሔደው በ10ኛ ክፍል ላይ ይሁን እንጅ በእነዚህ የክፍል ደረጃም ቢሆን ከስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ውጭ ያሉ ይዘቶች በጥናቱ አይካተቱም፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት መምህራን በ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ ዝምድና ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ሌሎች ይዘቶች ያልተካተቱበት ምክንያት የጥናቱን ሂደት ውስብስብና አስቸጋሪ ያደርጉታል ከሚለው ስጋት በተጨማሪ አጥኚው በስራ ላይ ሆኖ የሚያጠናው በመሆኑ ከጊዜ፣ጉልበትና የገንዘብ እጥረት ምክንያት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡- የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱ ደጋፊ የሆኑ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት የምሁራን ሐሳብ ማጠናከሪያ በማድረግ የቀረቡ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከጥናቱ ጋር ዝምድና ያላቸው የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ተዳሰውበታል።

## 2.1 ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት

በዚህ ርዕስ ስር በዋናነት ተጠቃለው የቀረቡ ንድፈ ሃሳባዊ ቅኝት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምንነት፣ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር፣አሳታፊየማስተማሪያዘዴን በክፍል ውስጥ መተግበር የሚያስገኘው ጥቅም፣ የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ማስፈፀሚያ ስልቶች፣ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያስችሉ ይዘቶች አመራረጥ፣ የስነ-ጽሁፍ ምንነት፣የቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ግንኙነት፣ ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያላቸው ጠቀሜታ፣ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውሉ የስነጽሁፍ ስራዎች አመራረጥ፣ ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በመተግበር ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች የተማሪዎች ተሳትፎ፣መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ እና ተማሪዎችን ለማሳተፍ መከናዎን ያለባቸው ተግባርትን በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን ያጠኗቸውን ጥናቶችና የፃፉቸውን መፃህፍት በመቃኘት ዝርዝር ማብራሪያ ይዟል።

### 2.1.1 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ምንነት

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አንድን ተግባር በአንድ ሰው ብቻ የሚተገበር ሳይሆን ሰዎችን በማስተባበር በአንድነት ተግባሩን ማከናዎን ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎች እርስ በእርሳቸውና ከመምህራን ጋር በመተባበር የመማር ማስተማር ሂደቱን የተነቃቃና የተቀላጠፈ የሚያደርጉበት ዘዴ እንደሆነ McArthut (1983)ያስረዳሉ። በተጨማሪም Cristal(1987) እንደገለፁት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች በክፍል ውስጥ እንዲተገብሩ የሚያስችሉ የትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች ሲሆኑ የተማሪዎችን ትኩረት፣ጥረት፣ችሎታና ተሳትፏዊ የመማር ብልሃትን ያፋጥናሉ ሲሉ ይገልጻሉ።

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች በክፍል ውስጥ እንዲተገብሩ የሚያስችሉ የትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች ናቸው። አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አንድ የቋንቋ መምህር ያዘጋጀውን የትምህርት ይዘት እንዴት ቢያስተምር የመማር

ማስተማር ሂደቱ ውጤታማ እንደሚሆንና የቋንቋ እውቀትን በተማሪዎች አዕምሮ እንዴት ማስረጽ እንደሚቻል የሚያመለክት ሳይንስ ነው (Richardsand Rodgers1986)፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የምንችለው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መምህራን መረጃ ሰጭ ብቻ ሳይሆኑ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ተግባር ንቁ ተሳታፊ በመሆን እርስ በእርስ የሚማሩበት መንገድ አመቻቾች እንደሆኑ ነው፡፡

## 2.1.2 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር

አሳታፊ የማስተማሬያ ዘዴ አተገባበር ተማሪዎቹን የትምህርቱ ማዕከል ማድረግ ሲሆን ተማሪዎች ወደ መማሪያ ክፍል ከገቡ ጊዜ ጀምሮ መምህራን የተማሪዎችን ለውጥ አስከ ሚገመግሙበት ያለውን ጊዜ የሚመለከት ሂደት ሲሆን ትምህርቱን በግልፅ ከማቅረብ ባሻገር ተማሪዎች በበርካታ ተግባራት እንዲሳተፉ በመምህሩ ታቅዶ የሚተገበርበት ዘዴ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Reed and Bergemann(1995) እንደገለጹት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ለተማሪዎች የመጨረሻውን የመማር ነፃነት የሚሰጥ ነው፡፡ መምህሩ የተማሪዎችን የመማር ሂደት ከመምራት ታቅበው ተማሪዎች በራሳቸው ስራ ራሳቸው ትምህርት አንዲዎያዩ፣ አንዲሰሩና የራሳቸውን ጥናትና ምርምር ለማከናዎን እንዲተጉ የሚያበረታቱበት መድረክ ነው፡፡ተማሪዎች በውይይት፣ በክርክር ችግሮችን በመፍታት ከፍተኛ ደረጃ ያለው የአስተሳሰብ ባለቤት እንዲሆኑ የሚደረግበት አተገባበር ነው፡፡ በተጨማሪም Baileyand Nunan (1996)፣Carter and Long(1991) የአንድን ትምህርት ትግበራ የሚወስኑ ብዙ ተላውጦዎች ቢኖሩም መምህሩ ወሳኝ ነው፡፡መምህሩ ዕቅዱን ወደ ተግባር ለመለወጥ ያለው ብቃት ዝቅተኛ ከሆነ ትግበራ ውሊደናቀፍ ይችላል፡፡ የማስተማሩን ሂደት የመምራት፣ተማሪዎችን የማደራጀት፣ የክፍልና የቤት ስራ የመስጠት፣ ተገቢ የሆነሥነ-ዘዴ የመጠቀም፣መርጃ መሳሪያዎችን የማቅረብ፣ ምጋቤ ምላሽ የመስጠት ተግባር የመምህሩ በመሆኑ የትግበራውን ሂደት ስኬታማ ሊያደርገው ወይም ሊያደናቅፈው ይችላል፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የምንችለው አሳታፊ የማስተማሬያ ዘዴ አተገባበር ለተማሪዎች የመማር ነጻነት የሚሰጥ ቢሆንም የመምህሩ ብቃት ለትግበረው ሂደት ስኬታማ መሆን ወይም አለመሆን ዋናው እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በክፍል ውሰጥ ተዘውትረው የሚተገበሩትን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች Silverman(1996) ሲገልጹ በቋንቋ ትምህርት ተዘውትረው የሚተገበሩት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ውይይት አንዱ ሲሆን ይኸውም ተማሪዎች የውይይት ደረጃቸውን ጠብቀው በመዎያየት ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ የሚያደርግ የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡

ክርክር:- ሁለት ቡድኖችን በማዋቀር በአንድ ሀሳብ ላይ የተለያዩ አላማዎችን በመያዝ እንዲከራከሩ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡ ሥዕልን መተንተን:- ስዕሎችን በአትኩሮት በማየት በተሸከሙት መልዕክት ዙሪያ ትንታኔ እንዲሰጡ የሚደረግበት ዘዴነው:: የፈጠራ ጽሁፍ ሥራ:- ተማሪዎች የተሰጣቸውን ሀሳብ መነሻ በማድረግ የራሳቸውን ሀሳብ በመጨመር አስፋፍተው እንዲጽፉ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡ ድራማ:- በድራማ መልክ አንድን የትምህርት ይዘት ማቅረቢያ ዘዴ ነው:: ከነዚህም በተጨማሪ መምህራን የትምህርቱን ይዘት ለማቅረብ አመች የሆኑትን የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችን መርጠው መጠቀም ይችላሉ በማለት ይገልፃሉ ፡፡

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የዘዴዎቹን አይነትና ባህሪ ማወቁ ብቻ ወደ ግብ አያደርስም፡፡ የተማሪዎቹ ቁጥር፣ የክፍሉ ሁኔታና የወንበሮቹ አደረጃጀት አተገባበሩን ይወስነዋል በማለት ይገልፃሉ፡፡ የመማሪያ ክፍሉ ውስጣዊ አደረጃጀት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያስችል ወይንም የማያስችል ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይም መቀመጫዎቹን ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በቀላሉ ለማንቀሳቀስ አመች ባልሆነበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህራን እንደትምህርቱ ይዘት የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በተለያየ አደረጃጀቶች እየለዋወጡ መጠቀም ስለሚቸግራቸው ዘዴዎቹን ከመተግበር ይልቅ ገለጻን አዘውትረው ለመጠቀም ይገደዳሉ ፡፡ በአንጻሩም የወንበሩ አደረጃጀት ምቹና ሰፊ በሆነው የመማሪያ ክፍል ውስጥ ወንበሮቹን በተለያየ ቅርጽ በማደራጀት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መተግበር ይቻላል፡፡ Jones(2004) ብዙና ጥቂት ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንዳስፈላጊነቱ ከመተግበር አኳያ ልዩነት እንዳለው ይገልጻሉ፡፡ በዚህም ትንሽ ቁጥር ባለው የመማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያዩ የወንበር አደረጃጀቶችን በመጠቀም ለተማሪዎቹ የሚሰጣቸውን ተግባራት በቀላሉ ለመቆጣጠር ከወዲያ ወዲህ እየተዘዋወሩ እገዛ ለማድረግ፣ለማበረታታት የተሰጠውን ጊዜ ለመቆጣጠር ለሰሩት ስራ በቂ የሆነ ማስተካከያና ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት ሲያስችል ብዙ ቁጥር ባለበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ግን ከላይ የጠቀስናቸውን ጉዳዮች በአንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለመተግበር አዳጋችነት ይኖረዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ መምህራን ተማሪዎቹ የተወያዩበትን ርዕሰ ጉዳይ ለማዳመጥና ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት አይቻላቸው ይሆናል፡፡ በዚህ ጊዜ የራሳቸውን ቴክኒክ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ የተለያየ እድሜ፣ ችሎታና ቋንቋ ያላቸው ተማሪዎች ተሰባጥረው ሊገኙ እንደሚችሉ ይገልፃሉ፡፡ በዚህም የተለያየ ዳራ ባለው የመማሪያ ክፍል ውስጥ መምህሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያደራጃቸውን ተማሪዎች ከተለያየ መገለጫቸው

አንጻር ማቀላቀል ይኖርበታል። ይህም ተማሪዎቹ እውቀትን ከመጋራት ባለፈ ጠንካራ የሆነ ወዳጂነትን እንዲመሰርቱ ያደርጋል በማለት ይገልፃሉ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት የምንችለው በክፍል ውስጥ የሚተገበረውን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ እንደትምህርቱ ይዘት ተስማሚ የሆነውን መርጦ በማቅረብ ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማድረግ የሚጠበቀው ከመምህራን መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ እንደ ትምህርቱ ይዘት የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለማቅረብ የተማሪው ቁጥር፣የክፍሉ ሁኔታ ወዘተ. ወሳኝነት እንዳለው መገንዘብ የሚያስፈልግ መሆኑን ነው።

## 2.1.3 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ መተግበር የሚያስገኘው ጥቅም

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ በመማር ማስተማሩ ሂደት ጊዜ የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚያስቀድምና የትምህርቱ ባለቤትም ተማሪዎች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የማስተማሪያ ዘዴ በመሆኑ በቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያነት ጉልህ ሚና ይጫወታል። አሳታፊ የመማር ማስተማርን ዘዴ ተግባራዊ በማድረግ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል የመግባባትና የጠበቀ የርስ በርሰ ግንኙነትን በመፍጠር ጠቀሜታ አለው።በመማር ማሰተማሩ ሂደት ወቅት አሳታፊ የመማር ማስተማር ጠቀሜታን አስመልክቶ Millis and Cottar (1998) እና Bligh (2000) እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡- የመማር ማስተማሩን ሂደት ማህበራዊ መሰረት እንዲኖረው ያደርጋል፤ ተማሪዎች በማስተማሩ ብልሃት በመጠቀም ክሂላቸውን የማሳደግ አጋጣሚ ያገኛሉ፤ የመምህሩን ጊዜና ጉልበት ይቆጥባል፤ ንቁ ለሆነ የማስተማር ትግበራ ጠቀሜታና አስፈላጊ የሆነ ብልሃት ነው፤በተለያየ መልኩ ውስብስብና ዝግጅት ባልተደረገባቸው ሀሳቦች ላይ ውይይት ለማድረግ ወዘተ. ይጠቅማል።

አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ የቋንቋውን መሰረታዊ ክሂሎች፣ የስነ-ፅሁፍና የስነ-ልሳን እውቀትን ለማዳበር ከማስቻላቸውም በላይ የተማሪዎችን የማስታዎስ ችሎታ፣ አንብቦ ወይም አዳምጦ የመረዳት ችሎታ፣ ነገሮችን የመተንተን፣ የመገምገምና አዲስ ነገር የመፍጠር ችሎታን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረክታል።

በአጠቃላይ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር በክፍል ውስጥ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ ከሚያስገኙት ጥቅሞች መካከል ተማሪዎች በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጭ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማድረግ የቋንቋን

ትምህርት ዓላማ ከግብ እንዲደርስ የሚያደረግ የተማሪዎችን የአመለካከትና የማገናዘብ ችግር የመፍታት አዲስ ነገር የማመንጨትና እርስ በርስ የመረዳዳት ባህል እንዲሰራበት የማድረግ ወዘተ. ጥቅምን ያስገኛል።

## 2.1.4 የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ ማስፈፀሚያ ስልቶች

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ማስፈፀሚያ ስልቶች ከሚባሉት ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ:- በግልስራ፣ በጥያቄና መልስ፣ በክርክር፣ በቡድንውይይት፣በመተባበር፣ ወዘተ.ከማስፈፀሚያ ስልቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

### 2.1.4.1 በግል ስራ የመማር ማስተማር ዘዴ

Harmer (1991) የግል ስራ አንድ ተማሪ እንዲሰራ የተሰጠበት ነገር ከመምህሩና ከጓደኞቹ እገዛ ነፃ በሆነ መልኩ ብቻውን የሚሰራበት መንገድ መሆኑንና በግል ስራ ተማሪዎች የሚሰሩበት ነገር ሁሉ ከመምህራንና ከጓደኛ ተፅእኖ ነፃ ለመሆን በራሳቸው አቅም ስለሆነ በራስ የመተማመን ብቃታቸውን ለመገንባት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ይገልፃሉ። በግል ስራ የመማር ማስተማር ዘዴ ተማሪዎች በግላቸው እንዲማሩ የሚደረግበት መንገድ ነው። በመሆኑም ይህን የማስተማሪያ ዘዴ ተፈፃሚ ለማድረግ የክፍል መምህሩ በዘዴው ተስማሚና አመች የሚሆን ርእስ መምረጥ፣ የሚመረጠው ርእስ የተማሪዎችን አቅም ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የተለያዩ በግል ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራትን (የክፍል ስራ፣ የቤትስራ፣ የፕሮጀክት ስራና የመሳሰሉትን) በተመጣጣኝ መንገድ መስራት እንዲችሉ አድርጎ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል።

### 2.1.4.2 በጥያቄና መልስ የመማር ማስተማር ዘዴ

Berliner and calfee (1996) በጥያቄና መልስ የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች አመራማሪ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅና በጥልቀት እንዲያስቡ በማድረግ በአጠቃላይ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ከምናደርጋቸው መንገዶች አንዱ ነው። የጥያቄና መልስ የመማር ማስተማር ዘዴ አንዱ ሲጠይቅ ሌላው ንቁ ተሳታፊ የሚሆንበት ዘዴ ሲሆን ጥያቄዎቹ መምህሩ ለተማሪዎች፣ ተማሪዎች ለመምህሩና ተማሪዎች ለተማሪዎች የሚጠይቋቸው ሊሆኑ ይችላሉ። በጥያቄና መልስ የመማር ማስተማር ዘዴ ወቅት ለማስተማሪያነት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከዕለቱ ትምህርት ርዕስ ጋር የተያያዙ እንዲሆኑ አድርጎ ማቅረብ፣ ጥያቄዎቹ ሁሉንም ተማሪዎች ማሳተፍ የሚችሉና አስተማሪ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ተማሪዎች የሚያነሷቸው ጥያቄዎች

በመምህሩ ከመመለሳቸው በፊት ተማሪዎች ራሳቸው እንዲሞክሯቸው እድል መስጠት፣ አንዳንድ በተማሪዎች የተመለሱ ጥያቄዎች ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለጋቸው መምህሩ ማብራራት አለበት ክፍል ውስጥ የማይመለሱ ጥያቄዎች ካሉ ደግሞ ተማሪዎች ከትምህርት ስዓት ውጭ መፃህፍትን አንብበው ወይም ሰዎችን ጠይቀው እንዲመልሱ የቤት ስራ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

### 2.1.4.3 በክርክር የመማር ማስተማር ዘዴ

በክርክር የመማር ማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ሀሳባቸውን ግንዛቤያቸውንና አቋማቸውን በሰለጠነ መንገድ መግለፅ እንዲችሉ የሚያደርግ ዘዴ ነው፡፡በተጨማሪም በክርክር የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ አማራጮች መኖራቸውን ለማሳየት የሚያስችል የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ በክርክር የመማር ማስተማር ዘዴን ስንጠቀም የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳዮቹ ለተከራካሪዎች ለዳኞችና ለአድማጮች አሻሚ ትርጉም የማይሰጡ ሊያከራክሩና የተለያዩ ሀሳቦችን ሊያንሸራሽሩ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡የመከራከሪያ ርዕሶቹ ሲመረጡ አንድ ትክክለኛ መልስ ያላቸው መሆን የለባቸውም፡፡ በተጨማሪም ተከራካሪዎቹ ለመከራከሪያ በተመረጡ ርዕሶች በራሳቸው ፍላጎት ደጋፊና ነቃፊ ሆነው እንዲቀርቡ የሚያደርጉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡በክርክሩ መጨረሻ መምህሩ ሁለቱንም ተከራካሪ ወገኖች ማበረታታት ይኖርበታል (Teaching Center፣ 2009)፡፡

### 2.1.4.4 በቡድን ውይይት የመማር ማስተማር ዘዴ

Brmfit (1984) የቡድን ስራ ከሁለት በላይ የሆኑ ተማሪዎች አንድ ላይ በመደራጀትና እርስ በርስ በመተግበር ሀሳባቸውን፣ እውቀታቸውንና አመለካከታቸውን የሚለዋወጡበት ንቁ ተሳትፎ የሚያሳዩበት መምህሩ በአስተባባሪነት የሚሰራበትና የአንድ ቡድን አባላት እንደአንድ ተማሪ ተደርጎ የሚታይበት ዘዴ ነው፡፡ በቡድን ውይይት የመማር ማስተማር ዘዴ መምህሩ የክፍሉን ተማሪዎች በትንንሽ ቡድኖች መድቦ ርዕስ በርሳቸው እየተዋያዩ እንዲማማሩ የሚደረግበት ዘዴ ነው፡፡ ይህ የመማር ማስተማር ዘዴ ቋንቋን በተግባቦታዊ ሁኔታ ለማስተማር ጠቃሚ ከሚባሉት ዘዴዎች አንዱ ሲሆን መምህራን የቡድን ስራውን ተግባራዊ ሲያደርጉ በአንድ ቡድን ላይ የሚደራጁ ተማሪዎችን ለመመደብ ትምህርታዊ መስፈርቶችን ማለትም ከፍተኛ መካከለኛ ዝቅተኛ እንዲሁም ትምህርታዊ ያልሆኑ መስፈርቶችን ማለትም እድሜን፣ ፆታን፣ ጓደኝነትና አካባቢን መሰረት አድርገው መመደብ አለባቸው፡፡

### 2.1.4.5 በመተባበር የመማር ማስተማር ዘዴ

Millis and Cottar (1998) እና Bligh (2000) በመተባበር የመማር ማስተማር ዘዴ ከሰሙ እንደምንረዳው ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ ተማሪዎች በመምህሩ አስተባባሪነት የሚሰጣቸውን ተግባራት እርስ በርስ ሀሳባቸውንና ልምዳቸውን በመለዋወጥ እንዲሁም ክህሎታቸውን በመጋራት በጋራ ትብብር የሚማሩበት መንገድ ነው። በመተባበር የመማር ማስተማር ዘዴ በሁሉም የክፍል ተማሪዎች የእርስ በርዕስ መረዳዳት ላይ የተመሰረተ የማስተማሪያ ዘዴ እንደሆነ ይናገራሉ። በመተባበር መማር ከውድድርና ፍክክር ነፃ በሆነ መልኩ ተማሪዎች ለመማር ተነሳሽ እንዲሆኑ፣ በመማር ማስተማሩ ተግባር በንቃት እንዲሳተፉና ለትምህርቱ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ የሚያደርግ የማስተማሪያ ዘዴ ነው ።

### 2.1. 5 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የሚያስችሉ ይዘቶች አመራረጥ

የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቀርቡ የቋንቋ ትምህርት ማስተማሪያ ይዘቶች ተማሪዎችን ማነሳሳት የሚችሉ በንቃት እንዲሳተፉ የሚያደርጉና የሚያበረታቱ፣ ተማሪዎች እየተዝናኑ የሚማሩበትን ምቹ ሁኔታዎች የሚፈጥሩ ተማሪዎች ሀሳብ በማፍለቅ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣እንዲጠይቁና እንዲመልሱ እድል የሚሰጡ የሚያበረታቱና መምህሩም ይህን ለመተግበር እንዲችል የሚያግዙ ይዘቶች ያለባቸው መሆኑን Tudor (1993)ይገልጻሉ።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳብ በመነሳት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እንዲወያዩ እንዲከራከሩ ሀሳባቸውን እንዲገልፁ በአጠቃላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያደርጉ ይዘቶችን እየመረጡ ማስተማር የብልህ መምህራን ተግባር ነው። ስለዚህ ስነፅሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር የላቀ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል።

## 2.1.6 የስነ-ጽሁፍ ምንነት

ዘሪሁን (2007) ስነ-ጽሁፍ በሰው ልጅ ታሪክ ለረጂም ዘመናት የቆየ ኪነጥበብ በመሆኑ ብዙ ሀሳቦች የተሰነዘሩበት፣ብዙ ክርክሮችና ምርምሮች የተደረጉበት መስክ ነው። ስለስነጽሁፍ የሚነገረው ቁጥሩ ብዙ ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የስነጽሁፍ ዋነኛ ጉዳይ ሰው ነው፤ ምንጩም ፈጣሪውም ተቀባዩም ሰው ነው ከሰው ህይዎት ተቀድቶ በስው ተፈጥሮ ስለሰው ተነግሮ የሰውን ጉዳይ ይዞ መልሶ ለሰው የሚቀርብ በመሆኑ ከሰው ልጅ ህይዎት ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው። ይህ ሰዋዊነቱ በማህበረሰብ ውስጥ ስነጽሁፍን ልዩ ቦታ ያሰጠዋል። እናም የብዙዎቹ መነጋገሪያ እንዲሆንያደርገዋል። መነጋገሪያም በመሆኑ በየጊዜው አዳዲስ መልኮችንና ተጨማሪ ትርጓሜዎችን እያያዘ

ይሄዳል፡፡ ከዚህም የተነሳ ብዙዎቹ የሚስማሙበት አንድ አይነት የስነጽሁፍ ብያኔ አይገኝም በማለት አስፍረዋል፡፡ ቢሆንም የተለያዩ የስነ-ጽሁፍ ብያኔዎችን ዳሰሳ አድርገው የሚከተለውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡

ስነ-ጽሁፍ በተለያዩ ቅርጾች በቋንቋ አማካይነት የሚከሰት፣ ስለሰዎች ለሰዎች፣ በሰዎች ስለሰዎች፣ የሚዘጋጅ የገጠመኝ ማንፀባረቂያና ህይወትን እውነትን ባንድ አጣምሮ የሚይዝ፣ ህልውናው በቃልም በጽሁፍም የሆነ የፈጠራ ስራ ነው ማለት እንችላለን፡፡ ይህ እንግዲህ በዋናነት ስነ ግጥምን፣ ተውኔትን፣ ረጅምና አጭር ልቦለዶችን እንዲሁም ከነዚህ ጋር ኪነጥበባዊ ተደራራቢነት ያላቸውን ጽሁፎችንና የተለያዩ የስነቃል ሀብቶችን ያጠቃልላል በማለት ገልፀዋል፡፡

Lazar (1993) የተለያዩ ምሁራን ስለስነጽሁፍ የሰጧቸውን ብያኔዎች እንደሚከተለው አስፍረዋል፡፡ ስነጽሁፍ በጥቅሉ ስሜትና ሃሳብ ነው፤ ስነጽሁፍ አንባቢዎች ወይም አድማጮች ግላዊ ምላሻቸውን እንዲያጭሩ የሚያደርግ የቋንቋ አጠቃቀም ነው፤ ስነጽሁፍ ደስታን (ፈንጠዝያ) ፣ሀዘን፣ ስሜትን፣ ራእይን ወዘተ በቃላት መግለጫ ነው፤ ስነጽሁፍ ማለት ብዙ ህዝብን የሚያገናኝ፣ የተለያዩ አዕምሯዊ ሃሳቦችንና እውቀቶችን የምንማርበት እንዲሁም እራሳችን የበለጠ ማዎቂያ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡

## 2.1.7 የቋንቋና ስነ-ፅሁፍ ግንኙነት ምንድን ነው?

ቋንቋና ስነ-ጽሁፍ የጠበቀ ግንኙነት አላቸው፡፡ ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ አማካይነት የሚገለጽ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Brumfit and Carter(1986) እንደሚከተለው ይገልጹታል፡፡ ስነ-ጽሁፋዊ ቴክስት በቋነቋ የሚገነባና ለትንተናውም በቅድሚያ መሰረት የሚያደርገው የቋንቋ አዎቃቀር ስርዓቱን ነው፡፡ ቋንቋው ለስነ-ጽሁፉ አንባቢ የማይገበው ከሆነ የጽሁፉን ጭብጥ በወጉ ሊረዳው ይቸገራል፡፡ የሚሰጠው ትንተና፣ ትርጉም ወይም ትችት ቋንቋውን መሰረት በማድረግ መሆኑም ግልጽ ነው፡፡ የቀረበበት ቋንቋ የቃላቱ፣ የአረፍተ ነገር ቅንብሩ፣ የቋንቋ አጠቃቀሙ የመሳሰሉት ለስነ-ጽሁፍ ብስለት ጠቀሜታ ያላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህ ስነ-ጽሁፉ ማለት ቋንቋን ዘወትራዊ ከሆነው ውጭ ለየት ባለ ሁኔታ መጠቀም ነው ወደሚለው ሀሳብ እንድናስብ ያደርገናል ፡፡

የስነ-ጽሁፍ መከሰቸው ቋንቋ ነው፡፡ ደራሲው ገጠመኙን ትዝብቱን በመረጠው የስነ-ጽሁፍ ቅርጽ የሚገልፀውና ለአንባቢ የሚያካፍለው በቋንቋ አማካይነት ነው፡፡ ታሪክ የሚተርከው፣ ገጸ-ባህሪያትን የሚቀርጸውና የሚያናግረው የማህበረሰቡን ገጽታ የሚያሳየውና ተፈጥሮን

የሚያደንቀው በቋንቋ ነው፡፡ ይህን ሁሉ የስነ ጽሁፍ ተግባር ለማከናወን ወይም ከግብ ለማድረስ የቋንቋ ችሎታ የቱን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡

## 2.1.8. ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያላቸው አስተዋጽኦ

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የተለያዩ የስነ-ጽሁፍ ስራዎችን የምንጠቀመው ለምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ መሰረት በማድረግ በርካታ መጻህፍትና የጥናት ስራዎች በተለያዩ የዘርፉ ምሁራን ቀርበዋል፡፡ ስነጽሁፍ በቋንቋ ማስተማር ክንውን ውስጥ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ይኸውም የቋንቋ ክሂል ዘርፎችን ማለትምማንበብ፣ መፃፍ፣ ማዳመጥና መናገርን ከዚህም በላቀ ደግሞ የቋንቋውን ስነልሳናዊ አገልግሎት በማስተማሪያ መሳሪያነት ጉልህ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የተለያዩ የቋንቋ ምሁራኖች ያስረዳሉ፡፡

ዘሪሁን (1998) እንደገለጹት ስነ-ፅሁፍ ሰዎች ገጠመኛቸውን በቋንቋ አማካኝነት የሚያንፀባርቁበት ኪነጥበብ ነው፡፡ ኪነ-ጥበብ በመሆኑ ውበት አለው፡፡ ውበት ካለው ደግሞ ስሜትን ይነካል፣ ይማርካል፣ ያስደስታል ይላሉ፡፡ ይህን የስነ-ጽሑፍ ውበት፣ ማራኪነት አስደሳችነት በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች አቅምና ዳራ ጋር አጣጥሞ ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ጉልህ አስተዋፅዖ ያበረክታል ለማለት ያስደፍራል በማለት ገልፀዋል፡፡

Hill (1986)ን ዘመንፈስ (1991) ጠቅሰው እንደገለፁት ስነ-ጽሑፍ የቋንቋ እውቀትን፣ ክህሎትን ለማዳበር ይጠቅማል በትምህርት ሂደትም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነቃቃል አንድ አስተማሪ መልመጃዎችን ከአንድ ቴክስት በሚያዘጋጅበት ጊዜ ስነ-ልሳናዊ ገፅታ ያላቸው ጥያቄዎችን ሊያሰናዳ ይችላል፡፡ በቴክስቱ ውስጥ ከሚገኙ ጭብጦች፣ ገፀ-ባህሪያት መቼት ወዘተ በመነሳት የገላጭ የትረካና የሌሎች አይነት ድርሰት መልመጃዎች ሊያዘጋጅም ይችላል፡፡ በዚህም ክንያት ስነጽሁፍ ቋንቋን ለማስተማር ጠቃሚ መሳሪያ ነው የሚባለው በማለት ገልፀዋል፡፡

Carter and Long (1991) Lazar (1993) እና Brumfit (1986 ) እንደሚያስገነዝቡት ስነ-ፅሁፍን በቋንቋ ትምህርት ለማካተት ያስፈለገበት ምክንያት የሶስት ማስተማሪያ ሞዴሎችን ዓላማ ግብ ለማሳካት ሲባል ነው፡፡ እነሱም፡- የባህል ተኮር ሞዴል ፣ የቋንቋ ተኮር ሞዴል እና የስብዕና ግንባታ ሞዴል ሲሆኑ ሶስቱም የየራሳቸው ዓላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና የተግባር ልምምድ ያላቸው ናቸው፡፡

የመጀመሪያው በባህላዊ ሞዴል መሰረት ስነ-ፅሁፍን ለቋነቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ስነ-ፅሁፍ የሰዎችን ሀሳብና ስሜት ይገልፃል። ከዚህ አንፃር በስነ-ፅሁፍ አማካኝነት ቋንቋን ማስተማር በዘመናት የተንፀባረቁ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ለሰው ልጆችትልቅ ዋጋና ሁለንተናዊ እሴቶች ያሏቸው ባህላዊ ሃብቶችን ተማሪዎች እንዲያገኙ ማስቻል ነው።(Carter and Long ፡1991)። ከዚህ በተጨማሪም Colli and Slater (1987) እንደሚገልጹት ተማሪዎች የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ባደገ መጠን እርካታን በማግኘት ለበለጠ ንባብ ይነሳሳሉ። በዚህም ሂደት ውስብስብ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ማድነቅና መተንተን ይማራሉ። ይህ ደግሞ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ባህልና ራሳቸውን በትኩረት እንዲመለከቱ እንዲመረምሩና እንዲረዱ ያነቃቃቸዋል። ስለዚህ ተማሪዎች የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን እንዲያነቡ ማበረታታትና ማገዝ ማለት ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎቹ የተፃፉበትን አካባቢና ማህበረሰብ አጠቃላይ ገፅታዎች እንዲረዱ ማገዝ ማለት ነው።

ሁለተኛው ቋንቋ ተኮር ሞዴል ሲሆን Lazar (1993)እንደሚሉት የዚህ ሞዴል አጠቃላይ እሳቤው በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ቋንቋና ስነ-ፅሁፍን አዋህዶ በማስተማር የተማሪዎችን የቋንቋ መማር ዓላማ፣ የቋንቋ ክሂሎችንና እውቀቶችን ለማዳበር ያስችላል የሚል ነው። በመሆኑም የቋንቋ ተኮር ሞዴል ትኩረት ስነ-ፅሁፍን ማጥናት ሳይሆን የስነ-ፅሁፍ ስራውን ለተከታታይ የቋንቋ ተግባራት እንደ ምንጭ መጠቀም ላይ ነው። ምክንያቱም ስነ-ጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከፍተኛ መነቃቃትን ስለሚፈጥርና የሰው ልጆችን የህይዎት ልምድና ገጠመኝ በማቅረብ የተማሪዎችን ትኩረት ስለሚስብ በራሳቸው ተነሳሽነት ቋንቋውን በልዩልዩ መልኩ ለመማር ስለሚረዳቸው ነው።

ሶስተኛው ስነ-ፅሁፍን ማስተማሪያ ሞዴል የስብዕና ግንባታ ሞዴል ነው። በዚህ ሞዴል ስነ-ፅሁፍን የማስተማር አስፈላጊነቱ የስነ-ፅሁፍ ፈተናን እንዲያልፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የተማሪዎችን ስብዕና ማደራጀት ወይም ማዳበር ነው። የመምህሩ ተግባርም የተማሪዎችን ስብዕና የሚያጎለብቱ የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን በመምረጥ ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ በንባብ እንዲጠመዱ በማድረግ የንባብ ፍላጎታቸውንና ዝንባሌያቸውን እንዲያሳድጉ ማነቃቃትና መረዳት ነው (Carter and Long፣1991)።

በአጠቃላይ ስነ-ፅሁፍን በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን እንዲያጎለብቱ የስነ-ልሳንና የስነ-ፅሁፍ እውቀታቸውን እንዲያሳድጉ ከማድረጉም በላይ ከሰው ልጆች ልዩ ልዩ ገጠመኞች የህይዎት ልምድ እንዲቀስሙ፣ አካባቢያቸውን፣ ባህላቸውን፣ ወግና ታሪካቸውን እንዲገነዘቡ፣ የበለጠ ለማወቅ ጥረት እንዲያደርጉ፣

ለተጨማሪ ንባብ እንዲነሳሱና ዓለምን በተለያየ መልኩ እንዲመለከቷት ያደርጋቸዋል። ስነ-ጽሁፍ ስሜትን የሚይዝና ቀልብን የሚገዛ የፈጠራ ስራ በመሆኑ ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግል መሳሪያ ነው ማለት ይቻላል።

ይህን አስመልክቶ በድሉ(2007) ስነ-ፅሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ለምን መጠቀም እንዳስፈለገ እንዲህ በማለት ይገልፃሉ። የስነጽሁፍ ስራ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያጎለብት መሆን አለበት። የተማሪዎች ተግባራዊ ተሳትፎ ደግሞ ለተመረጠው ስራሳቢ መሆን አለመሆን ጋር ቀጥተኛ ዝምድና አለው ። የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት ወጥሮ መያዝ የቻለ ስራ ሳቢ ነው። በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተግባራዊ ድርሻ እንዲኖራቸው ያደርጋል ። በቀረበው ስራ የተሳቡ ወይም በስራው ላይ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ስለስራው የበለጠ የማወቅ ጉጉት ይኖራቸዋል። ስለዚህ የበለጠ ለማወቅ በክፍል ውስጥ በሚከናወነው ተግባር ላይ ተሳታፊ ይሆናሉ።

## 2.1.9 ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውሉ የስነጽሁፍ ስራዎች አመራረጥ

በክፍል ውስጥ ቋንቋን ለማስተማር የሚመረጡ ስነፅሑፋዊ ስራዎች ሊያሟሏቸው ስለሚገባቸው መስፈርቶች በርካታ የዘርፉ አጥኚዎች ብዙ ብለዋል። ከነዚህም ውስጥ Lazer (1993)፣ Hill (1986*)፣ Carter*and Long (1991)፣ Brumfit and Carter (1986) ተጠቃሾች ናቸው። ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውሉ ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ከምንመርጥባቸው መስፈርቶች ውስጥም የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ፣ የተማሪዎችን የስነ-ፅሁፍ ዳራዊ ዕዉቀትና ከስነ-ፅሁፋዊ ስራው ጋር የተያያዙ ሌሎች ነጥቦችን ባገናዘ በመልኩ መምረጥ ተገቢ እንደሆነ ምሁራን ይመክራሉ። እነዚህ ቋንቋን ለማስተማር የሚውሉ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች መምረጫ መስፈርቶችም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡

### 2.1.9.1 የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ባገናዘበ መልኩ መምረጥ

Hill (1986) ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሊውሉ የታሰቡት የስነ-ፅሁፍ ስራዎች ቋንቋውን ከሚማሩት ተማሪዎች አንፃር መፈተሽ ይገባቸዋል።የተማሪዎች ማህበራዊ ሁኔታ፣ የተማሪዎች የቋንቋ ዳራ፣ የተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ዳራ፣ የተማሪዎች እድሜ፣ የተማሪዎች የእዉቀት ደረጃና የተማሪዎች ፍላጎት የሚሉት በዋናነት ይጠቀሳሉ። ተማሪዎች አንድን የስነ-ፅሁፍ ስራ የመርዳትና የማገናዘብ ችሎታቸው እንደየመጡበት አካባቢና እንዳደጉበት ማህበረሰብ የቋንቋ አጠቃቀም ሊለያይ ይችላል። ለማስተማሪያነት

የቀረበውን ስነ-ጽሁፋዊ ስራ አንብበው የመረዳት አቅም(ችሎታ) የቀረበውን ስራ በቶሎ የመለማመድ ሁኔታ ለነዚህ ዳራዎች ባላቸው ቅርበት ሊፋጠን ወይም ሊጓተት ይችላል፡፡

### 2.1.9. 2 የተማሪዎችን የስነ-ፅሁፍ ዳራዊ ዕውቀት ባገናዘበ መንገድ መምረጥ

Hill (1986) ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሊውል የታሰበው የስነ-ጽሁፍ ስራ ከተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ጋር የሚጣጣም መሆን እንዳለበት ያስገነዝባሉ፡፡ ይኸውም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውሉ የስነ-ፅሁፍ ስራዎች ሲመረጡ በቋንቋ አጠቃቀምና በስልት ደረጃቸው ቋንቋውን ከሚማሩት ተማሪዎች ችሎታ ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣሙ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የስነፅሁፍ ሥራዎቹ በቃላት አጠቃቀማቸውና በአረፍተነገር አዎቃቀራቸው ከተማሪዎቹ ችሎታ በላይ ወይምበታች እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ያሻል የስነፅሁፍ ስራዎች በዘይቤዎች በአረፍተነገር ደረጃም ቢሆን ከተለመደው የቋንቋው አዎቃቀር ህግ ውጭ የሚሆኑበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ በመሆኑም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡት የስነ-ፅሁፍ ስራዎች ተመርጠው ለቋንቋ ማስተማሪያነት ከመዋላቸው በፊት በጉዳዩ ዙሪ ያሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን እያነሱ መመርመር እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡ ከተማሪዎች ችሎታ(አቅም) በላይ ወይም በታች የሆኑ የስነ-ጸሁፍ ስራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ማዋል የመማር ማስተማር ሂደቱን ከማደናቀፍ ውጭ ለተማሪዎች የሚጨምርላቸው ነገር አይኖረውም፡፡

### 2.1.9.3 ከስነ-ፅሁፋዊ ስራው ጋር የተያያዙ ሌሎች ነጥቦች

Lazar (1993) ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ለማዋል ሲታሰብ፣ ከግንዛቤ መግባት አለባቸው ከሚባሉት ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች ውስጥ ከስነ-ፅሁፍ ስራው ጋር የተያያዙ ነጥቦችም ይጠቀሳል፡፡ እነዚህም ነጥቦች የስነ-ፅሁፋዊ ስራዎቹ በስፋት መገኘት፤ የስነ-ፅሁፋዊ ስራዎቹ የትክክለኛነት ደረጃና የስነ-ፅሁፋዊ ስራዎቹ በትምህርትነት ከሚሰጠዉ ቋንቋ መርሃ ትምህርት ጋር ያላቸው የዝምድና ደረጃ የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው በማለት ገልፀዋል፡፡

## 2.1.10 ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በመተግበር ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በቋነቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በመተግበር ወቅት በርካታ እንቅፋቶች ያጋጥማሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹን ቀጥለን እንመለከታለን፡-

### 2.1.10.1 የመፅሀፉን ይዘት ለማስተማር የተሰጠው ጊዜ ያለመመጣጠን ችግር፡-

የማስተማሪያ ጊዜና የመፅሀፉ ይዘት አለመጣጣም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የአሳታፊ ትምህርት ትግበራን ይገድባል፡፡ shank(1999) የማስተማሪያ ሰዓት እጥረት ሲገጥም የሚፈለገውን የማስተማሪያ ዘዴ መርጦ ለማስተማር አዳጋች ይሆናል፡፡ ሰፊ የሆነ የማስተማሪያ ጊዜ ሲኖር አሳታፊ ትምህርት በተገቢው መንገድ ሊተገበር ይችላል፡፡ የተለያዩ ስነ-ዘዴዎችን ለመተግበርም ያስችላል፡፡ የጊዜ እጥረት ካለ ግን መምህሩ ቀጥተኛ መምህር መራሽ ዘዴን እንዲጠቀም ይገደዳል በማለት ገልፀዋል፡፡

### 2.1.10.2 ለመምህራን የስራላይ ስልጠና ያለመስጠት ችግር፡-

መምህራን የሰለጠኑበት የማስተማሪያ ዘዴ አሁን ቋንቋን ለማስተማር ውጤታ ማነው ከምንለው ዘዴ ጋር ፍፁም የማይገናኝ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ መምህራን ይህን የማስተማሪያ ዘዴ በክፍል ውስጥ ለመተግበር አቀበት መስሎ ሊታያቸው ስለሚችል በፊት በሰለጠኑበትና በለመዱት የማስተማሪያዘዴ መጠቀምን የሚመርጡበት አጋጣሚ ይፈጠራል፡፡ Tudor(1996) መምህራን የሚሰለጥኑበት አቅጣጫና የአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴ የክፍል ውስጥ ትግበራ አንድነት ከሌለው በትግበረውና በመምህሩ መካከል አለመግባባት ይፈጠርና ትግበራው ሊደናቀፍ ይችላል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት ለመምህራን የስራላይ ስልጠና መስጠቱ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን ጨምረው ይገልፃሉ፡፡

### 2.1.10.3 የክፍል ተማሪ ጥምርታ ያለመጣጣም ችግር፡-

ብዙ ተማሪዎች ከመጠን በላይ የተጨናነቁበት የመማሪያ ክፍል የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችንና የሙከራ ስራዎችን ለማሰራት አያመችም፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ በርካታ ተማሪዎች ካሉ የእያንዳንዱን ተማሪ ፍላጎት ማወቅ አስቸጋሪ ከመሆኑም በላይ ሁሉንም ተማሪዎች በተሰጠው ሰአት ለማሳተፍ ከባድ ስለሚሆን ትግበራውን ያደናቅፈዋል፡፡ Jones (2004) የስነጽሁፍ ቴክስት ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲውል ብዙ ተማሪዎች ባሉበት የመማሪያ ክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ከመተግበር አኳያ የተለያዩ የወንበር አደረጃጀቶችን በመጠቀም ለተማሪዎቹ የሚሰጣቸውን ተግባራት በቀላሉ ለመቆጣጠር፣ ከወዲያ ወዲህ እየተዘዋወሩ እገዛ ለማድረግ፣ ለማበረታታት፣ የተሰጠውን ጊዜ ለመቆጣጠር ለሰሩት ስራ በቂ የሆነ ማስተካከያና ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት በአጠቃላይ ከላይ የጠቀስናቸውን ጉዳዮች በአንድ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለመተግበር አዳጋችነት

ይኖረዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ መምህራን ተማሪዎቹ የተወያዩበትን ርዕስ ጉዳይ ለማዳመጥና ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት አይቻላቸው ይሆናል፡፡

### 2.1.10.4 ከማስተማሪያ መሳሪያዎችና ከስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ጋር የተያያዙ ችግሮች፡

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ለመተግበር እንቅፋት ከሆኑት ነገሮች መካከል የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የስነ-ፅሁፍ ስራዎች በቅርብና በበቂ ሁኔታ አለመገኘት፤ የሚገኙት ደግሞ ለዘዴው የማይስማሙና ለክፍል ደረጀው የማይመጥኑ ከሆኑ ችግሩ እንዲባባስ ያደርጉታል፡፡ Farrant (1980) አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ለማቅረብ ተማሪዎች እንደልባቸው እየተንሸራሸሩ የሚቀመጡበትና በቡድንም ሆነ በጥንድ የስራ ተግባር ወቅት እንደፈለጉ ለመንቀሳቀስ የሚያስችሉ ወንበሮች ሊኖሩ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የመማሪያ መፃህፍት ከተማሪዎች ቁጥር ጋር አለመጣጣም፤ በቂ የሆኑ አጋዥ መፃህፍት አለመኖር ወዘተ በትግበራው ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ፡፡

በድሉ (2007) ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ለማስተማር ሲታሰብ ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል የስነ-ፅሁ ፍስራዎችን በቅርብና በበቂሁኔታ ያለማግኘት ችግር ነው፡፡ ይህች ግርግን ስነ-ፅሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ከመጠቀም ሙሉ በሙሉ ሊያግደን አይገባም፡፡ በእርግጥ የንባብ ክህሎትን ለማዳበርና አንዳንድ ተግባራትን ለማስፈፀም በቂ የስነ-ፅሁፍ ቅንጫቢዎች ሊያስፈልጉ ይችላሉ በዚህም እንደችግሩ መምህሩ ያዘጋጁትን ቅንጫቢ ብቻ በመጠቀም የንግግር፣ የፅህፈት፣ የማዳመጥና ሌሎች የቋንቋ ትምህርትን ማስተማር ይቻላል በማለት ይገልፃሉ፡፡

### 2.1.11 የተማሪዎች ተሳትፎ

የተማሪ ተሳትፎ ማለት ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት በንቃት የሚያከናውኑትን ተግባር የሚያመለክትነው፡፡ ይኸውም ጥያቄ መጠየቅና ለጥያቄዎች መልስ መስጠት፣ አስተያየት መስጠት፣የቡድን ውይይት መስራት፣ ለሚታዘዙት ተግባር ቀና የሆነ ስሜት መኖር፣ የቤትና የክፍል ስራዎችን መስራትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም የትምህርት ስራ ተፈላጊውን የባህሪ ለውጥ ያስገኝ ዘንድ የተማሪዎች ተሳትፎ መኖር እጅግ አስፈላጊ ነው (Teaching Center፣2009)፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎ ቁልፍ ባህሪ ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ለሚማሩት ትምህርት ትኩረት በመስጠት የሚያሳልፉትን ሰፊ የጊዜ ሽፋን ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የሚያደርጉት ተሳትፎ የሚቀርብላቸውን ትምህርት በጥልቀት እንዲገነዘቡና እንዲቀበሉ ጉልህ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ ልዩ ልዩ ክሂሎችንም በቀላሉና በፍጥነት ያዳብራሉ (Borich፣2004)፡፡

## 2.1.12 መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ

በዚህ ጥናት ተዛምዶ በተማሪዎችና በመምህራን ተግባራት መካከል ያለውን እድነትና ልዩነት የሚመለከት ነው፡፡ ይኸውም መማር በሚከዎንበት ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ ከመምህራን ተግባራት ጋር ግንኙነት አለው፡፡ መምህራን በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባሮችን የሚያከናውኑ ከሆኑ የተማሪዎች ተሳትፎም ከፍተኛ ይሆናል (Elliott፣2000)፡፡

KourliskY (1987) ቋንቋን መማርም ሆነ ማስተማር የሚቻለው የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሲኖር ነው፡፡ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በንቃት የሚሳተፉ ከሆነ የሚቀርበውን ትምህርት በጥልቀት እንዲገነዘቡና እንዲቀበሉ ይረዳል፡፡ መምህሩም የበለጠ እንዲሰራና እንዲበረታታ ያደርገዋል ፡፡

Lewis and Hill (1985) ቋንቋን ለማስተማር የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ወሳኝነት እንዳለው ሲያስረዱ ተማሪዎች እርስ በእርስና ከመምህራቸው ጋር በሚያደርጉት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያላቸውን ዕውቀት እንዲያሻሽሉ ያደርጋል ፡፡ በዚህ የተነሳ መምህራን የተማሪዎችን ቋንቋ ወይም ትምህርት ለማጎልበት በአብዛኛው ጊዜያቸው ተማሪዎችን እንዲሳተፉ የሚያደርግ የክፍል ውስጥ አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ መጠቀም እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ፡፡

Kadir & Asimiran (2014) እንዳሉትም መምህራን የመማር ማስተማሩ ሂደት መዘውር ናቸው፡፡ ዋንኛ ተግባራቸው የመማር ማስተማሩን ሂደት ማመቻቸትና አመራር መስጠት ነው ሲሉ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የመማር ባለሙያዎች መሆናቸውን ደግሞ (Sharma & Bansal, 2017) ያስገነዝባሉ፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች በትምህርትነት የቀረበውን ጽንሰ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን እንዴት መማር እንዳለባቸውም ጭምር ይማራሉ፡፡ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ፤ እንዲሁም ትምህርታዊ ተግባራቱ አሳታፊና ተማሪ መራሽ ናቸው፡፡ መምህራኑ የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚያመቻቹ ሲሆን ተማሪዎቹ ራሳቸውን እንዲችሉና ኃላፊነት እንዲወስዱ

ይበረታታሉ። ስለዚህ የቋንቋ መምህራን ይህንን ግምት ውስጥ በማስገባት የክፍል ውስጥ የትምህርት አተገባበር ሳቢና ምቹ ማድረግ አለባቸው።

Farrant (1980) በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማጎልበት በየትኛውም ደረጃ ላይ ያሉትን ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ትኩረት እንዲሰጡና የበለጠ እንዲሰሩ ይገፋፋቸዋል። ተማሪዎች የበለጠሊማሩ የሚችሉት በትምህርቱ ሂደት ከፍተኛ ተሳትፎ ሲኖራቸው በመሆኑ መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ የክፍል ውስጥ ተግባሮችን በአግባቡ ማደራጀት አለባቸው። በመሆኑም መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማሳደግ ከሚረዱ በርካታ ሁኔታዎች ውስጥ ጥቂቶቹ ፡-

## 2.1.13 መምህራን ተማሪዎችን ለማሳተፍ ማከናዎን ያለባቸው ተግባርት

የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት የተለያዩ ተግባራትን ማከናዎን ያስፈልጋል። እነዚህ ተግባራትም ለሰፊ ልምምድ የሚጋብዙ ጥያቄዎችን ማዘጋጀትና የተለያዩ ማበረታቻዎችን መጠቀም ናቸው።

### 2.1.13.1. ለሰፊ ልምምድ የሚጋብዙ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት

ለቋንቋ ትምህርት የሚዘጋጁ ጥያቄዎች ክሂሎችን ማዳበር ቀዳሚ ተግባራቸው መሆን አለበት። ይኸውም የጥያቄዎች ዓላማ ተማሪዎች መልሶችን ማግኘት አለማግኘታቸው ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች ወደ መልሶቹ ለመድረስ በሚያደርጉት ልምምድ የቋንቋ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው። ስለሆነም ወደ መልሶቹ ለመድረስ ቋንቋውን በስፋት መገልገልን የሚጠይቁ መልመጃዎችን ማዘጋጀትያስፈልጋል። ለምሳሌ ክፍት ቦታ መሙላት፣ አንድን ሀሳብ በራሳቸው አባባል ማብራራት፣ቅደም ተከተልን ማስተካከል ወዘተ ጥያቄዎችን ማካተት ይገባል (Doll፡1991)።

Borich (1995) እንደሚሉት ደግሞ የተማሪዎች ተሳትፎ የሚወሰነው መምህራን በክፍል ውስጥ ለገለፃ የሚያጠፉትን ረዥምጊዜ በመቀነስ ተማሪዎች ሊሳተፉበት የሚያስችላቸውን ሰፊ የመዎያያ ጊዜ እንዲያገኙ በማድረግ ነው።በመሆኑም መምህራን ተማሪዎችን በተግባሩ እንዲሳተፉ በማድረግ የመማር ማስተማር ስራውን ውጤታማ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

## 2.1.13.2 የተለያዩ ማበረታቻዎችን መጠቀም

መምህራን በሚያስተምሩበት ግዜ ተማሪዎችን በተለያየ መንገድ ማበረታታት አለባቸው፡፡ ተማሪዎች የሚበረታቱ ከሆነ ትምህርቱን ለመማር ተነሳሽነት ስለሚያድርባቸው በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ ይህን በተመለከተ Hedge (2000) ሲገልፁ ተማሪዎች አዘውትረው ሊሳተፉ የሚችሉት በተለያየ መንገድ መበረታታት ሲችሉ ሲሆን በተለያየ መንገድ መበረታታቸው የራሱ የሆነ ጥንካሬ ስላለው ለሌላ ጊዜ ደጋግመው እንዲሳተፉ ይጋብዛቸዋል፡፡ በተጨማሪም መምህራን የአንድን ትምህርት ክህሎትና ዝንባሌን ለማስረፅ የሚችሉት የተማሪዎች ሙሉ ተሳትፎ ሲታከልበትነው፡፡ ተሳትፎውም ማራኪና ውጤታማ የሚሆነው መምህሩ ለክንውኑ ቀና አመለካከት ሲኖረውና ተማሪዎችን የሚያበረታታ ሲሆን ነው፡፡ መምህራን ትምህርቱን በሚያቀርቡበት ጊዜ ፈቃደኛ የሆኑትን ተማሪዎች ብቻ ከመጠየቅ ይልቅ ፈቃደኛ ያልሆኑትንም ተማሪዎች መጠየቅና የተለያዩ የጥያቄ ስልቶችን በመጠቀም የሁሉንም ተማሪዎች  አትኩሮት ወደ አንድ አቅጣጫ ማድረግ ይቻላል፡፡

Kourlisky (1987) እንደሚሉት ሁልጊዜ እጁን የሚያወጣ አንድን ተማሪ ብቻ መጠየቅ እጅ የማያወጡ ተማሪዎች ትምህርቱን እንደይከታተሉና እንደይሳተፉ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ መምህራን ዝምተኛ ወይም እጃቸውን የማያወጡትን ተማሪዎች ለማሳተፍ የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው፡፡ ተማሪዎችን ባለመቅጣት ማስተማር ተሳትፏቸው እንዲጨምር ያበረታታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፈቃደኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን በመጠየቅ ትክክለኛ ምላሽ ላያገኙ ቢችሉም ሁሉም ሊሳተፉይችላሉ፡፡ ሆኖም ግን መምህሩ ፈቃደኛ ያልሆኑ ተማሪዎችን ሲጠይቅ በሚሰጡት ትክክለኛ ያልሆነ መልስ በመናደድ ወይም በመቆጣት ተማሪዎች ለመማር ያላቸውን ተሳትፎ መቀነስ የለበትም፡፡ በመሆኑም መምህሩ የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመጨመር የተማሪዎችን ምላሽ መቀበልና ማበረታታት አለበት፡፡ ይኸውም ተማሪዎች ለመምህሩ ምላሽ በሚሰጡበት ጊዜ መምህሩ ትኩረት ሰጥቶ ማዳመጥ፣ ፈገግ ማለት፣ ራስን መነቅነቅ ተማሪዎችን ያነሳሳል፡፡ ተማሪዎችም ለጥያቄው መልስ ለመስጠት በሚጠራጠሩበት ጊዜ ፈገግ በማለት እንዲቀጥሉና እገዛ በማድረግ ማበረታታት ያስፈልጋል (Cole and Chan:1994) ::

Nunan (1991) ሲገልፁም በትምህርት አቀራረብ ሂደት ተማሪዎች የመምህራንን የቅርብ ክትትል ይሻሉ፡፡ ለማንኛውም እንቅስቃሴያቸው (በሚናገሩበት ጊዜ፣ በሚፅፉበት ጊዜ፣ በሚጠይቁበት ጊዜ) መልካምና አበረታታች ምላሽን ይፈልጋሉ፡፡

በአጠቃላይ  በትምህርቱ  ሂደት አስፈላጊ በሚሆንበት ወቅት ዝንባሌያቸውንና ጥረታቸውን አውንታዊ በሆነ በጎምላሽ በማገዝ ትምህርቱ ሊቀርብ እንደሚገባው ይመክራሉ፡፡ ስለሆነም

መምህራን ትምህርቱን በሚያቀርቡበት ጊዜ የተማሪዎችን ሃሳብበ መቀበል ለሚሰሩት ስራ ሁሉ ትክክልኛ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋቸዋል፡፡

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ የቀደምት ጥናቶች ርዕስ ሥር ለመዳሰስ የሚሞከረው በአገር ውስጥ ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ ጋር ያላቸውን ዝምድና የተካሄዱትን ጥናቶች ነው፡፡ አጥኚው መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ በሚመለከት የተካሄዱ ጥናቶችን ማግኘት አልቻለም፡፡ ይሁን እንጂ የተማሪዎች ተሳትፎ በስነፅሁፍ አማካኝነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና እና የቡድን ውይይት ተግባራዊነትና ውጤታማነት በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በሚሉ ርእሶች በተናጠል የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው፡፡ በነዚህ ርዕሶች ላይ ጥናታቸውን ያካሄዱት ፍቅሬ (1994)፣ አሳየ (1997) ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የእነዚህ ጥናቶች ዓላማና ግኝትም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ፍቅሬ (1994) «የቡድን ውይይት ተግባራዊነትና ውጤታማነት በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በእንጦጦ ወንጌላዊት ትምህርት ቤት 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ግለ ክፍል ምርምር» በሚል ርእስ ያጠኑ ሲሆን የጥናቱ አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች የቡድን ውይይት እንዲያካሄዱ ቢደረግ ተግባራዊነቱ ምን እንደሚመስል ማመልከት ነው፡፡ ግኝቱም በልምምድ ሂደት በርካታ ተማሪዎች በሚገኙበት ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የቡድን ውይይትን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ታይቷል፡፡

አሳየ (1997) «በፋሲሎና በጣና ሐይቅ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን ይመስላል?» የሚል ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል መመርመር ሲሆን የጥናቱ ግኝትም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው የሚል ነው፡፡ ይኸውም መምህራን በክፍል ውስጥ አብዛኛውን ክፍለጊዜ ብቻቸውን እንደሚሸፍኑ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ምክንያቱም የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማጎልበት የሚረዱ የተለያዩ ዘዴዎችን አይጠቀሙም፡፡ እንዲሁም መምህራን ማበረታቻ የሚሰጡት መልሱን በትክክል ለመለሱ ተማሪዎች ብቻ ነው፡፡ ትክክለኛውን መልስ ያልመለሱ ተማሪዎችን ይወቅሳሉ፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሁሉም ጥናቶች መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር እና የተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ ጋር በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት ታይቶበታል። ይኸውም፡- የኔ ጥናት ከፍቅሬ ጋር የሚያመሳስለው ከማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የቡድን ውይይት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ እንዲያካሄዱ ቢደረግ ተግባራዊነቱ ምን እንደሚመስል ማተኮሩ ሲሆን ነገር ግን ለተግባራዊነቱ የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን አለመጠቀሙና ከማስተማሪያ ዘዴዎቹ ውስጥ በአንዱ አይነት ላይ ብቻ ማተኮሩ ልዩ ያደርገዋል።

የኔ ጥናት ከአሳየ ጋር የሚያመሳስለው በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ማተኮሩ ሲሆን ነገር ግን በማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ላይ ምንም ያለው ነገር አለመኖሩ ልዩ ያደርገዋል።

በአጠቃላይ ከዚህ ቀደም የተሰሩ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ የሚያመሳስላቸው ቢሆንም የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በተናጥል የተሰሩ ናቸው። ስለዚህ ይህ ጥናት ስነ-ፅሁፍ ስራዎችን በመጠቀም በአሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ ላይ ማተኮሩ ልዩ ያደርገዋል። በመሆኑም ይህ ጥናት የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል የሚል እምነት አለ ።

# ምዕራፍ ሶስት፡- የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት ተዛምዷዊ የአጠናን ስልትን የተከተለ ሲሆን ይህ የአጠናን ስልት የተመረጠበት ምክንያት Johnson and Christensen (2012) ተዛምዷዊ ጥናት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ጥገኛእና ነፃ መጠናዊ ተላውጦዎች ወይም ሁለትና ከዚያ በላይ ጥገኛና ነፃ ዓይነታዊ ተላውጦዎች በመካከላቸው ያለውን ተዛምዶ የሚያጠና የምርምር ንድፍ ነው በማለትይገልፃሉ፡፡ ይህን ንድፍ ሃሳብ መነሻ በማድረግ በምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በአሀዝና በአይነት ተተንትነዋል፡፡ የተደረሰበትን ማጠቃለያና መደምደሚያ ሀሳብቀርቧል፡፡

## 3.1 የተጠኝዎች አመራረጥ

የዚህ ጥናት አካላዮች በልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በመካነ ኢየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ምበመንግስት በመደበኛው መርሃ ግብር ተመዝግበው የሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችና በነዚ ህክፍሎች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ የተማሪዎችና የመምህራን የቁጥር ብዛት ለናሙና የተመረጡት ተመዝግበው በመማር ላይ ያሉ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች እና በነዚህ ክፍሎች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው፡፡ በዚህ ርዕስ ስር  በንዑስ ርዕስነት ተካተው የቀረቡት የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ፣ የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ፣የመምህራን የናሙና አመራረጥ እና የተማሪዎች  የናሙና አመራረጥ  የሚሉት  ናቸው፡፡

### 3.1.1 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተከናዎነው በ2013 ዓ.ም በደቡብ ጎንደር ዞን በእስቴ ወረዳ በልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በመካነ ኢየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትነው፡፡ ትምህርት ቤቶቹ የተመረጡበት የናሙና ስልት በአመች የንሞና ዘዴ ነው፡፡ በዚህ የንሞና ስልት የተመረጡበት ምክንያት ለአጥኚው የስራ ቦታ ቅርብ በመሆኑ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ያለችግር ማግኘት ያስችላል ብሎ በማሰብ ነው፡፡

### 3.1.2 የክፍል ደረጃ የናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጠው የክፍል ደረጃ የ10ኛ ክፍል ሲሆን የክፍል ደረጃው የተመረጠበት የንሞና ዘዴ ደግሞ በአመች የንሞና ዘዴ ነው፡፡ ሌሎች የክፍል ደረጃዎች ያልተመረጡበት ምክንያት በ2013 ዓ.ም ወደ 9ኛ ክፍል ገብተው ትምህርት የሚጀምሩት የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በ2012 ዓ.ም በኮቪድ አስራ ዘጠኝ ምክንያት የክልል ፈተናውን

ባለመፈተናቸው ወደ 9ኛ ክፍል የሚገቡት የክልል ፈተና ከተፈተኑ በኂላ በመሆኑ ይህ ደግሞ ጥናቱን በጊዜው ለማጥናት አመች ባለመሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም፡፡ 11ኛ ክፍል ያልተመረጡበት ምክንያት የልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት11ኛ ክፍል ማስተማር የጀመረው በ2013ዓ.ም በመሆኑ በቂ የሆነ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተሟልተው ባለመቅረባቸው የዚህ ክፍል ደረጃ ለጥናቱ ምቹ ሆነው አልተገኙም፡፡ በመሆኑም ለአጥኚው በሁለቱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተመሳሳይ የሆኑ የክፍል ደረጃዎችን ወስዶ ማጥናት ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት አመች ይሆናል ብሎ በማሰብ የ10 ክፍል ብቻ ለጥናቱ ተመራጭ አድርጓል ፡፡

## 3.1.3 የመምህራን የናሙና አመራረጥ

ለጥናቱ የተመረጡት የ10ኛ ክፍል መምህራን ሲሆኑ በልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ እንዲሁም በመካነ ኢየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አምስት ሲሆኑ የተመረጡበት የናሙና ስልት በጠቅላይ የንሞና ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ቁጥራቸው አንስተኛ በመሆኑ የጥናቱን አስተማማኝነት እንዳያሳጠው ለማድረግ ነው፡፡

## 3.1.4 የተማሪዎች የናሙና አመራረጥ

ለናሙናነት በተመረጡት ሁለት ትምህርት ቤቶች ውስጥ 10ኛ ክፍል በ26 ሴክሽን 908 ወንድና 876 ሴቶች በድምሩ1784 ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህን ተማሪዎች እያንዳንዱ መምህር ከሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ሁለት ሁለት የመማሪያ ክፍል በድምሩ 12 ሴክሽኖች በቀላል እጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያት ሁሉም መምህራን በሚያስተምሯቸው የመማሪያ ክፍሎች የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን በመጠቀም የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል ያለውን ተዛምዶ ለመፈተሽ አመች ስለሆነና መረጃውንም አስተማማኝ ለማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተመረጡት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቁ ለማካተት ለአጥኚው አስቸጋሪ ነው፡፡ ስለሆንም ያለው (2009) የጥናቱ የትክክለኛነት መጠን እንዲጨምር ከፈለግን ከጥናቱ አካላይ መጠን አንፃር የናሙናውን መጠን ከፍ ማድረግ ይኖርብናል፡፡ የናሙናው መጠን በቀነሰ ቁጥር የመረጃ ስህተት መጠን ይጨምራል፡፡ አንዳንድ ተመራማሪዎች 5%፣10%፣ 15%...ወዘተ የጠቅላላ የጥናቱ አካላይ በናሙናነት መመረጥ ይኖርበታል የሚል ሃሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ ነገር ግን ይሄ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም፡፡ ለምን ቢባል የጥናቱ አካላይ ብዛት ይህንን በተግባር ለመተርጎም አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በአጠቃላይ ግን የአካላዩ ቁጥር በበዛ ቁጥር የናሙናውም ቁጥር መብዛት ይኖርበታል በማለት ይገልፃሉ፡፡በመሆኑም

አጥኚው ከዚህ ሀሳብ በመነሳት ከጠቅላላው 1784 የተማሪዎች ቁጥር ብዛት 10% በናሙናነት ቢመረጥ መረጃውን አስተማማኝ ያደርገዋል በማለት 180 ተማሪዎች እንዲመረጡ ተደርጓል፡፡

## ሰንጠረዥ 3.1 በናሙናነት የተመረጡ ክፍሎች (ሴክሽኖች)ና የተማሪዎች ብዛት

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤቱ ስም | የመምህሩ ስም | ፆታ | የሚያስተምሩበትሴክሽንብዛት | ለክፍልውስጥምልከታለናሙናነትየተመጡ | | | | ለፅሑፍመጠይቅለናሙናነትየተመረጡተማሪዎች ብዛት | | | የአመራረጥዘዴ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ሴክሽን | የተማሪብዛት | | | | | | |
| | | | | | | | | ድ | | | ድ | |
| 1 | ልዋዬ 2ኛ ደረጃት/ቤት | መምህርአንድ | ሴ | A,B,C D,E,F | A | 34 | 31 | 65 | 8 | 7 | 15 | በቀላልዕጣ ንሞና |
| | | | | | D | 32 | 32 | 64 | 7 | 8 | 15 | |
| 2 | መካነኢየሱስሁለተኛደረጃት/ቤት | መምህርሁለት | ሴ | A,B,C እና D | B | 30 | 33 | 63 | 7 | 8 | 15 | በቀላል ዕጣ ንሞና |
| | | | | | D | 34 | 31 | 65 | 8 | 7 | 15 | |
| | | መምህር ሦስት | ወ | E,F‹G እናH | F | 29 | 33 | 62 | 8 | 7 | 15 | በቀላል ዕጣ ንሞና |
| | | | | | G | 33 | 32 | 65 | 7 | 8 | 15 | |
| | | መምህር አራት | ሴ | II,JK እና L | K | 31 | 33 | 64 | 7 | 8 | 15 | በቀላል ዕጣ |
| | | | | | L | 32 | 31 | 63 | 8 | 7 | 15 | |
| | | መምህር አምስት | ወ | M,N,O P እናQ | M | 34 | 31 | 65 | 8 | 7 | 15 | በቀላል ዕጣ |
| | | | | | N | 33 | 30 | 63 | 7 | 8 | 15 | |
| | | መምህር ስድስት | ወ | R,S,Tእና U | S | 34 | 30 | 64 | 7 | 8 | 15 | በቀላል ዕጣ |
| | | | | | U | 28 | 34 | 62 | 8 | 7 | 15 | |
| | ጠቅላላድምር | ስድስትመምህር | | 26 | 12 | 3 84 | 381 | 765 | 90 | 90 | 180 | |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ1 እንደሚታየው እያንዳንዱ መምህር ከሚያስተምሩባቸው የመማሪያ ክፍሎች ሁለት ሁለት በድምሩ 12 ሴክሽኖች ለክፍል ውስጥ ምልከታ በቀላል ዕጣ ንሞና እንዲሁም ከጠቅላላው አስር ፐርሰንት የተመረጡትን180 ተማሪዎች ለ12ቱ የክፍል ውስጥ ምልከታ ሴክሽኖች (180/12) እኩል በማካፈል ከእያንዳንዱ ክፍል 15 ተማሪዎች በእጣ የማውጣት ዘዴ ለፅሑፍ መጠይቅ ለናሙናነት ተመርጠዋል፡፡ አመራረጡን በተመለከተ በየሴክሽኑ የሚገኙ ተማሪዎች ዝርዝር ከየክፍል ሀላፊ መምህራን ከተወሰደ በኋላ የወንዶችና የሴቶች ቁጥር እንዲመጣጠን ጾታን መሰረት በማድረግ ከሁለት ከተከፈሉ በኋላ እኩል መጠንና አንድ አይነት ቀለም ባላቸው ወረቀቶች

ላይ ከእያንዳንዱ ጾታ የሚፈለገውን ብዛት ያህል በተዘጋጁት ወረቀቶች ላይ ቁጥር በመፃፍና ሌሎቹን ምንም ያልተፃፈባቸው በማድረግ ተጠቅልለው ከተደባለቁ በኋላ እያንዳንዱ ተማሪ እጣውን እንዲያወጡ በማድረግ ቁጥር የተፃፈባቸውን እጣ ያገኙትን በመመዝገብ ከጠቅላላው ሴክሽን 90 ወንዶችና 90 ሴቶች በድምሩ 180 ተማሪዎች በቀላል ዕጣ ንሞና ተመርጠዋል፡፡ ይህ የንሞና ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የሆነ የመመረጥ እድልን ስለሚሰጥ ነው፡፡

## 3.2 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የዚህ ጥናት ዓላማ መምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነዉ፡፡ ይህን ከግብ ለማድረስ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምልከታ፣የፅሁፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.2.1 ምልከታ

ምልከታ የዚህ ጥናት ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሲሆን ይህም የተመረጠበት ዋና አላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል በዝርዝር ለማስተዋልና ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡

ምልከታ የሚባለው ለተወሰኑ ጊዜያት መረጃ በሚሰበሰቡበት ቦታ ተገኝቶ ትክክለኛ ክስተቱን በመመልከት መረጃ የሚሰበሰብበት ሲሆን ለትንተና እንዲያመች በጽሁፍ ሊተረጎም ወይም ወደ መጠናዊ መረጃነት ሊለወጥ ይችላል (Ary and et al.,2010; Tavakoli,2012):: ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በክፍል ውስጥ ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና የተማሪዎችን ተሳትፎ መነሻ በማድረግ በአጥኚው ተዘጋጂቶ በአማካሪው ተገምግሞ የሚሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ለመጨረሻ ጊዜ ተሻሽለው ከተዘጋጁ በኋላ ስራ ላይ ውለዋል፡፡ ምልከታው የተካሄደው በቀላል እጣ ናሙና አመራረጥ በተጠኝነት በተመረጡት ተማሪዎችና መምህራን የመማር ማስተማሩ ሂደት በሚካሄድበት አስራ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች ተገኝቶ የመማር ማስተማሩን ሂደት በመመልከት በአንድ ክፍል ውስጥ ሁለት ክፍለ ጊዜ ማለትም እያንዳንዱ መምህር አራት ክፍለ ጊዜ በጠቅላላው ሃያ አራት ክፍለ ጊዜ በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ ደግሞ ለ40ደቂቃ ያህል ምልከታ በማድረግ በመጠናዊ መረጃነት በተዘጋጀው የማመሳከሪያ ቅፅ በጥኚው ተሞልቷል፡፡ ከፍሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው

በምልከታ የተገኙትን መረጃዎች ወደ መጠናዊ መረጃነት ለውጦ ለመመዝገብ ያገለገለው ደረጃዊ ልኬት(rating scale)ነው፡፡ Ary and et.al. (2010)ና Tavakoli (2012) እንደገለጹት ደረጃዊ ልኬት ተመልካቾች ለተመለከቷቸው ባህርያት ያላቸውን ሚዛናዊ ግምገማ የሚገልጹበት መንገድ ነው፡፡ ስለዚህም የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ለሚደረጉ ጥናቶች ምቹ የሆነ መረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለዚህ ጥናት መረጃ ለማሰባሰብ ያገለገሉት የምልከታ ቅጾች አራት ደረጃዎች ያሏቸው ሲሆን የነጥብ አሰጣጡ 4. በጣምእስማማለሁ 3. እስማማለሁ 2. አልስማማምና 1. በጣም አልስማማም በሚለው የስምምነት መግለጫ ስር/✓/ ምልክት በማድረግ መረጀው ተሰብስቧል፡፡ (አባሪ ሀ ይመልከቱ)፡፡

### 3.2.2 የፅሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የፅሁፍ መጠይቅ ሲሆን፣መጠይቁም የተዘጋጀው ለመምህራንና ለተማሪዎች ነው፡፡ የፅሁፍ መጠይቁ መሰረታዊ አላማ ደግሞ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ ዙሪያ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡ የጥያቄዎቹ ብዛት 21 ሲሆኑ ትኩረት የተደረገውም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር፣ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፣የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር እና በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል ያለው ተዛምዶ፣ የስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ የአሳታፊ ዘዴ ጠቀሜታ እና የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሙ እንቅፋቶችን በሚመለከት የቀረቡ ናቸው፡፡

የፅሁፍ መጠይቁ በአጥኙ ተዘጋጂቶ በአማካሪ ተገምግሞ የሚሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ለመጨረሻ ጊዜ ተሻሽለው ከተዘጋጁ በኋላ ስራ ላይ ውለዋል፡፡ የተዘጋጀው የመጠይቅ አይነት ዝግ (closed) ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን በምልከታ ከተሰበሰበው መረጃ ጋር ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ነው፡፡ ዝግ ጥያቄዎቹ የተመረጡበት ምክንያት ኮድ ለማድረግ፣ ለማቀናጀት፣ ለማጠቃለልና ለመተንተን አመች በመሆናቸው ነው፡፡

የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረጉት ለጥናቱ የተመረጡት የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ስድስት የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲሆን የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረጉት ምክንያት አንደኛ ተግባሪዎቹ እነሱ በመሆናቸው ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ ብሎ

በማመን ነው፤ ሁለተኛ ለአጥኚው በምልከታ ለሚሰበስበው መረጃ እንደረዳት አድርጎ በመውሰድ ነው፡፡ ስለሆነም ሁሉም (100%) በተገቢው ሁኔታ ሞልተው መልሰዋል፡፡ እንደዚሁም እነዚህ መምህራን ምልከታ ከሚደረግባቸው አስራ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ በእያንዳንዱ ክፍል አስራ አምስት በድምሩ 180 ተማሪዎች እንዲሞሉ የተደረገ ሲሆን 160 (88.89%) በትክክል ሞልተው ሲመልሱ 9 ወንዶችና 11 ሴቶች በድምሩ 20 (11.11%) ተማሪዎች ግን የጽሁፍ መጠይቅን ከአንዳንድ ድጥያቄዎች ላይ በመድገም ሌላዎቹ ላይ ደግሞ ሳይሞሉ በማለፍ (በመዝለል) ጥያቄው በትክክል ባለመሞላቱ መረጃን ስለሚያዛባ በትንተናው ውስጥ አልተካተቱም፡፡

### 3.2.3 ቃለ-መጠይቅ

ለዚህ ጥናት ሶስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ-መጠይቅ ሲሆን፣ ቃለ-መጠይቁም የተዘጋጀው ለመምህራን ነው፡፡ የቃለ-መጠይቁ መሰረታዊ አላማ ደግሞ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ ዙሪያ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለማግኘት ነው፡፡ የጥያቄዎቹ ብዛት አምስት ሲሆኑ ትኩረት የተደረገውም በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመተግበር ያላቸው አስተዋጽኦ ምን እንደሚመስል፣ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አዘውትረው ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የማስተማሪያ ዘዴን የሚመለከት፣አሳታፊ የማስተማሪ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል፣ በ10 ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡትን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ተጠቅመው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠሙ ችግሮች ምን እንደሆኑ እና የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን እንደሚመስል በሚመለከት የቀረቡ ናቸው፡፡

ቃለ መጠይቅ በቃል መረጃ የሚሰበሰብበት ስልት ሲሆን ልክ እንደ ፅሑፍ መጠይቁ በምልከታ የተገኘውን የመረጃ ውጤት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም የፅሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተመረጡት መምህራን በሙሉ በጠቅላይ የንሞና አመራረጥ ዘዴ በመምረጥ ቃለ-መጠይቁ ተካሂዷል፡፡

ቃለ- መጠይቆቹ ተጠኚዎቹ የሚሰማቸውን ሀሳብ ሳይገደቡ እንዲሰጡ የሚያደርግ በመሆኑ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ሊገኙ ይችላሉ በሚል የተዘጋጁ ሲሆኑ በዚህ ጊዜ

ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት የሌላቸውን በመተው ትክክለኛና አግባብነት ያላቸውን መረጃ ብቻ በመውሰድ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

## 3.3 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህን ጥናት ከግብ ለማድረስ ምልከታ ዋና የክፍል ውስጥ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን፣የፅሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ደግሞ በምልከታ የተገኘውን የመረጃ ውጤት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ደጋፊ የመረጃ መሰብሰቢያ ስልቶች ናቸው፡፡ ይህንን ለማከናዎን የይዘት ትንታኔ ተጠቅሟል፡፡ የይዘት ትንተና በንግግር ወይም በጽሁፍ የቀረበን መረጃ ወደ መጠናዊ መረጃነት ለመለወጥ የሚያገለግል አካሄድ ነው (Tavakoli, 2012 እና Ary,2010)፡፡ እንደ Tavakoli (2012) አገላለጽ የይዘት ትንተና አይነታዊ የምርምር ስልት ሲሆን የንግግር፣ የጽሁፍ ወይም በአይን በሚታይ መንገድ የተገለጹ መረጃዎችን ለመቁጠር ያገለግላል፡፡ በአይነተኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የተሰበሰበን መረጃ በቁጥር ለመግለጽ ያገለግላል፡፡ በመሆኑም ተመራማሪው ለተለያዩ ተግባራት ወካዮችን በመስጠት እያንዳንዱ ወካይ የተከናወነበትን ሁኔታ በቁጥር ይገልጽበታል (Ary፣2010)፡፡ የተወከሉት በቁጥር የሚገለጽ እንደመሆኑ መጠን መረጃዎቹ በመጠናዊ መረጃ መተንተኛ ዘዴ ተተንትነዋል፡፡ ይህም ተላውጦቹን የሚገልጹት መረጃዎች አስተማማኝነት በስታስቲካዊ ስሌት እንዲሰላ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር ሲሆን መረጃዎቹ ከመረጃ ማሳያ መንገዶች መካከል በሰንጠረዥ በየፈርጁ ተደራጅተው ይቀርባሉ (Tavakoli, 2012)፡፡

ይህ ጥናት በቅደም ተከተላዊ ጥምር የምርምር ስልት የተከናወነ እንደመሆኑ መጠን በመጀመሪያ በምልከታ እና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በመጠን ተገልጸው ከተተነተኑ በኋላ በአይነት ወደ ተገለጹ መረጃዎች ትንተና ተሸጋግሯል (ምእራፍ አራትን ይመልከቱ)፡፡ ይህ ጥናት ያነሳውን መሰረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችሉ በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ወደ መጠን ተለውጠው የተመዘገቡት በደረጃዊ ልኬት ነው፡፡ ያለው (2009) እንደገለጹት ደረጃዊ ልኬት የተለያዩ ሰዎች ወይም ነገሮች ከአንድ የተመረጠ ተላውጦ አንጻር የሚያሳዩትን ባህሪ በማወዳደር አንደኛው ከሌላው የበለጠ ወይም ያነሰ መሆኑን በደረጃ በሚያሳይ አህዝ የሚገለጽበት መንገድ ነው፡፡ ምልከታው የተከናወነው በአራት ዙር ሲሆን ለትንተና የተወሰደው ደግሞ የአራት ዙሩ አማካይ ነው፡፡ የአራት ዙሩ አማካይ ሲሰላ በደረጃዊ ልኬት የተገለጸው መረጃ ወደ እኩል ምጣኔ ልኬትነት ተቀይሯል፡፡ ስለዚህም በመረጃ ትንተና በምልከታና በፅሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በመጠናዊ የመረጃ አተናተን ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ አማካይ ውጤት (mean)፣ መደበኛ ልይይት (standard deviation)፣ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ

ለምናልባት ስህተት 0.05 በመተው የተሰበሰበው መረጃ በፒርሰን የተዛምዶ ስሌት (Pearson's coorelation coefficient)፣ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡ በደረጃዊ ልኬት የተገለጹ መረጃዎችን ለመተንተን በጥቅም ላይ ውለዋል። ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ደግሞ ከአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ አንዱ በሆነው በገለፃ ስልት ተተንትኖ ቀርቧል።

በነፃ ተላውጦዎችና በጥገኛ ተላውጦው መካከል ያለውን የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን በመጠቀም ነው። መስፈርቶችም የሚከተሉት ናቸው፡- 0.00-0.19 ዝምድና የለሽ ወይም በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ፣0.20-0.39 ዝቅተኛ ተዛምዶ፣ 0.40-0.59 መካከለኛ ተዛምዶ፣0.60-0.79 ከፍተኛ ተዛምዶ እና 0.80-1.00 በጣም ከፍተኛ ተዛምዶ (ጠንካራ) ተዛሞዶ

## 3.4.የመረጃ ትክክለኛነትና አስተማማኝነት

Ary (2010) እንደገለጹት ለምርምር ተግባር በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የሚሰበሰቡ መረጃዎች ትክክለኛነትና አስተማማኝነት መጠበቅ መቻል ይኖርበታል። ይህን ጥናት ለማከናወን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር በተያያዘ መረጃዎች ተገቢነትና አስተማማኝነት እንዲኖራቸው የሚከተለው ተግባር ተከናውኗል። የመረጃ ትክለኛነትን ለመጠበቅ የተከናወነው የመጀመሪያው ተግባር የምልከታና የጽሁፍ መጠይቅ ቅጾቹ ተዘጋጅተው ከተጠናቀቁ በኋላ ላማካሪ አስገምግሞ በተገቢነታቸው ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ ነው። የምልከታና የጽሁፍ መጠይቅ  ቅጾች የተዘጋጁት የመምህራኑን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የተማሪዎችን ተሳትፎ ተዛምዶ አስመልክቶ መረጃ ለማሰባሰብ ነው። በዚህ መሰረት የምልከታና የጽሁፍ መጠይቅ ቅጾቹ በአጥኚው ተዘጋጂቶ በአማካሪው ተገምግሞ የሚሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች ለመጨረሻ ጊዜ ተሻሽለው ተዘጋጅተው ከተጠናቀቁ በኋላ የምልከታ ቅጾቹ አስተማማኝ መረጃ ማስገኘት የሚችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ለሁለት የሁለተኛ ዲግሪ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በደረጃ ልኬት እንዲመዝኗቸው ከተደረገ በኋላ አስተማማኝነቱን ለመለካት በፒርሰን ስታስቲካዊ ቀመር የተሰላ ሲሆን አስተማማኝ መረጃ  ማስገኘት የሚያስችል  መሆኑን ለማወቅ የተሰላው የፒርሰን ቀመር ውጤት 0.86 ሲሆን በተጨማሪም ለ5 ሴትና ለ5 ወንድ በድምሩ ለ10 ተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጎ ውጤቱ 0.81 ነው። ያለው (2009) በገለጹት መሰረት ይህ ውጤት የሁለቱም የምልክታ ቅጾች አስተማማኝ መረጃ የማስገኘት አቅም በጣም ከፍተኛ መሆኑን አረጋግጧል። በመሆኑም የምልከታ ቅጾቹ ለመረጃ መሰብሰቢያነት በጥቅም ላይ ውለዋል።

የጥናቱን መረጃዎች ለመሰብሰብ ለክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ለጽሁፍ መጠይቅና ለቃለ-መጥይቅ የተዘጋጁ ነጥቦችን ለማስገምገም የቀረቡ መለኪያዎች፡፡ በ2005 ዓ.ም በስራ ላይ በዋለው በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርእና በተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ ላይ ለሚሰራ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ የሚሆኑ የክፍል ውስጥ ምልከታው፣ የጽሁፍ መጠይቁና የቃለ-መጠይቁ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት በማድረግ ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን. ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር የጥያቄ ቁጥር 1፣2፣3፣4፣5፣እና6
2. ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማጎልበት ያለው አስተዋጽኦ የጥያቄ ቁጥር 7፣8፣9 እና 10
3. የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለው ተዛምዶ፣ የጥያቄ ቁጥር 1-6 እና 7-10
4. የስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ የጥያቄ ቁጥር 11፣12፣13እና14
5. የአሳታፊ ዘዴ ጠቀሜታ 15፣16 እና 17
6. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሲተገብሩ የሚያጋጥሙ እንቅፋቶች የጥያቄ ቁጥር18፣19፣20፣እና 21

# ምዕራፍ አራት:- የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አለማ  የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር እና በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ እንደሆነ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ጥናቱ ተዛምዷዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ ሲሆን በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የቀረቡትን መጠናዊ የምርምር ስልትን በመጠቀም እንዲሁም በቃለ-መጠይቅ የቀረቡትን ደግሞ በገለጻ ስልት በመጠቀም ውጤቱ የሚቀርብ እንደሆነ ተጠቅሷል። በዚህ መሰረትም በምልከታ፣በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ-መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነዋል። በመጀመሪያ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ምን ይመስላል? የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ምን ይመስላል? የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው? የስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስዋጽኦ ምን ይመስላል? አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ምን ይመስላል?  በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ምንድን ናቸው?  የሚሉት የምርምር ጥያቄዎች በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል።

### 4.1.1 በምልከታ የተገኙ መረጃዎች ተዛምዷዊ ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ  ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለውን ተዛምዶ  በምልከታ ለመፈተሽ 21 ጥያቄዎችን የያዘ ነው። እነዚህ 21 ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው አራት አማራጮችን የያዙ ሲሆኑ በ24 ክፍለ ጊዜ በኣራት ዙር ምልከታ የተመረጡት ውጤቶች በኮድ ሽት ከሰፈረ በኋላ የእያንዳንዱ ጥያቄ አማካይ ውጤት በ(SPSS) ኮምፒተር ሶፍት ዌር  ውስጥ በማስገባት ውጤቱ ተሰልቷል። በስሌት የተገኘው ስታስቲካዊ መረጃ ደግሞ በእያንዳንዱ  የጥናቱ የጥያቄ አይነት በመከፋፈል በገለጻ  ተብራርቶ ቀርቧል። የጥናቱ ውጤትም በእያንዳንዱ ትንተና መጨረሻ ላይ ቀርቧል።

### 4.1.1.1 የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና

የጥናቱ አንደኛ ጥያቄ ሆኖ የቀረበው የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ምን ይመስላል? የሚልነበር፡፡ ይህን ለመፈተሽ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በነፃ ተላውጠው እና በጥገኛ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን በመጠቀም ሲሆን 0.00-0.19 ዝምድና የለሽ ወይም በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ ፣ 0.20-0.39 ዝቅተኛ ተዛምዶ ፣0.40-0.59 መካከለኛ ተዛምዶ፣0.60-0.79 ከፍተኛ ተዛምዶ ደግሞ 0.80-1.00 በጣም ከፍተኛ ተዛምዶ (ጠንካራ) ተዛሞዶ የሚል ነው፡፡ በተሰለው ስታስቲካዊ መረጃ መሰረት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ተተንትኗል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.1 የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ እና የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር መካከል ያለው ተዛምዶ ትንተና

| ተ.ቁ | የመምህራን አተገባበር በተመለከተ የቀረቡ ተላውጦዎች | አማካይ/Mean | መደበኛልይይት/ Std. D | የዝምድና ኮሬሽንት (Correlations coefficient) | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ውጤት | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| | የስነጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ | 11.542 | .1882 | 1 | -.343 | .331 | -.887* | .765 | -.159 |
| 1 | መምህሩ/ሯ...ተማሪዎችን እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ ወዘተ. በማድረግ እንዲሳተፉ አድርገዋል ፡፡ | 2.667 | .1231 | -.343 | 1 | .351 | .369 | -.171 | .231 |
| 2 | መምህሩ/ሯ...ተማሪዎችን በግል፣ በጥንድና በቡድን በማደራጀት የክፍልና የቤት ስራ ተግባራትን እየሰሩ እንዲሳተፉ አድርገዋል ፡፡ | 2.292 | .3509 | .331 | .351 | 1 | .065 | .030 | .000 |
| 3 | መምህሩ/ሯ..የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመጠቀማቸው ሁሉንም ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ አድርገዋል ፡፡ እንዲሳተፉ አበረታተዋል፡፡ | 2.625 | .2500 | -.887* | .369 | .065 | 1 | -.887** | .342 |
| 4 | መምህሩ/ሯ... እንደ ትምህርቱ ይዘት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዲሳተፉ አድርገዋል፡፡ | 2.708 | .1794 | .765 | -.171 | .030 | -.887** | 1 | -.476 |
| 5 | መምህሩ/ሯ... የተለያዩ ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲሳተፉ አድርገዋል፡፡ | 2.500 | .3989 | -.159 | .231 | .000 | .342 | -.476 | 1 |
| 6 | መምህሩ/ሯ...ተማሪዎች ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ እንዲሁ ያታንና እድሜን ያማከለ አድርገው በመመደብ ሃሳባቸውን እንዲለዋዎጡና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አበረታተዋል ፡፡ | 2.708 | .0973 | -.542 | .632* | .388 | .701* | -.759** | .293 |

P<0.05

የጉልህነት ተዛምዶ (P<0.05) እንዳላቸው በሰንጠረዥ 4.1.1የተገለጠ ሲሆን በፐርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ከተተነተነው ከመጀመሪያ ውሰን ጠረዥ ስንነሳ በመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር (በንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች ) እና በስነጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ (ነፃ ተላውጦ) መካከል የጥንካሪ ደረጃው ይለያል፡፡ ከቀረቡት ውጤቶች (r=-.887*) በጣም ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ አላቸው፤ (r=.765) ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው፤(r=-.542) መካከለኛና አውንታዊ ተዛምዶ አላቸው ፤ (r=.331) ዝቅተኛ የሆነ አዎንታዊና (r=-.343) ዝቅተኛ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑንያሳያሉ፡፡ በመጨረሻም (r=-.159 ) በጣም ዝቅኛየሆነ አሉታዊ ተዛምዶ ያላቸው

መሆኑን ያሳያሉ። ይህም መምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎን ተጠቅመው የመማር ማስተማሩን ሂደት ሲተገብሩ ..የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመጠቀም ሁሉንም ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታቸው፣...እንደ ትምህርቱ ይዘት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን እንደሚያሳትፉ ማድረጋቸው፣ መምህሩ/ሯ...ተማሪዎችን ከፍተኛ፣መካከለኛና ዝቅተኛ እንዲሁም ያታንና እድሜን ያማከለ አድርገው በመመደብ ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታቸው። ...ተማሪዎችን በግል፣ በጥንድና በቡድን በማደራጀት የክፍልና የቤት ስራ ተግባራትን እየሰሩ እንዲሳተፉ ማድረጋቸው፣ ተማሪዎችን እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ ወዘተ. በማድረግ እንዲሳተፉ ሲደረግ፣ በአንፃሩ...የተለያዩ ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲሳተፉ አለማድረጋቸው በዚህ ትንተና ያሳያል። በአጠቃላይ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ($p < 0.05$) ዝምድና ያላቸው ናቸው።

በአጠቃላይ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ (ነፃተላውጦው) ጋር ያለው ተዛምዶ አብሬጅ 0.5045 በመሆኑ መካከለኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል።

### 4.1.1.2 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና

የጥናቱ ሁለተኛ ጥያቄ ሆኖ የቀረበው ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማጎልበት ያለው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? የሚል ነበር። ይህን ለመፈተሽ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል። በመሆኑም በነፃ ተላውጦው እና በንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን በመጠቀም ተተንትኗል።

## ሰንጠረዝ 4.2 የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና

| ተ.ቁ | ተማሪዎችን ተሳትፎ የተመለከቱ ተሳውጦዎች | አማካኝ / Mean | መደበኛ ልይይት Std.De | የዝምድና ኮሬሽንት( Correlations coefficient) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ውጤት | 7 | 8 | 9 | 10 |
| | የስነ ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ | 11.542 | .1882 | 1 | .263 | .429 | -.542 | -259 |
| 7 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግል፣ በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በመስራት ተሳትፈዋል፡፡ | 8.417 | 7.3711 | .263 | 1 | -.834** | -.314 | .271 |
| 8 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እርስ በእርስ የሚማሩበትን መንገድ በመፍጠር ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ | 1.854 | .5883 | .429 | -.834** | 1 | .199 | .061 |
| 9 | ተማሪዎች በእለቱ ትምህርር ላይ ጥያቄ በመጠየቅና መልስ በመስጠት፣ አስተያየት በመስጠት ተሳትፎ | 2.396 | .1982 | -.542 | -.314 | .199 | 1 | .067 |
| 10 | ተማዎች በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት፣ክርክር፣ንግግር፣ወዘተ. በሚከናወኑበት ጊዜ ትኩረት በመስጠት ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ | 2.521 | .2491 | -.259 | -.271 | .061 | -.067 | 1 |

**P<0.05**

የጉልህነት ተዛምዶ (P<0.05) እንዳላቸው በሰንጠረዥ 4.1.2 የተገለጠ ሲሆን በፐርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ከተተነተነው ከጥያቄ ቁጥር 7 እስከ 10 ስንነሳ በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እና በስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች መካከል ያላቸው ተዛምዶ የጥንካሬ ደረጃው ይለያል፡፡ ከቀረበው ውጤት (r=-.542) መካከለኛ የሆነ አሉታዊና (r=.429) ደግሞ መካከለኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ሌሎች (r=.263) ዝቅተኛ የሆነ አዎንታዊና (r=-.259) ዝቅተኛ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ተማሪዎች በእለቱ ትምህርር ላይ ጥያቄ በመጠየቅና መልስ በመስጠት፣ አስተያየት በመስጠት ተሳትፎ የሚያደርጉ መሆናቸውን፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እርስ በአርስ የሚማማሩበትን መንገድ በመፍጠር ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን፣ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግል፣ በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በመስራት ተሳታፊ መሆናቸው፣ እንዲሁም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስነ-ጽሁፍ ስራዎችን በመጠቀም የቡድን ውይይት፣ ክርክር፣ ንግግር፣ ወዘተ. በሚከናወንበት ጊዜ ትኩረት በመስጠት ንቁ ተሳታፊ መሆናቸውን

ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ የሚደርስ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ($p<0.05$) ዝምድና ያላቸው ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ (ንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች) ከስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ (ነፃ ተላውጦው) ጋር ያለው የተዛምዶ መጠን አብሬጅ 0.373 በመሆኑ ዝቅተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤትያሳያል፡፡

### 4.1.1.3 የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና

የጥናቱ ሶስተኛ ጥያቄ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል? የሚል ነበር፡፡ ይህን ለመፈተሽ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን በመጠቀም ተተንትኗል፡፡

**ሰንጠረዝ 4.3 የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያላቸው ተዛምዶት ትንተና**

| ተ.ቁ | የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያላቸው ተዛምዶ | አማካይ/ Mean | መደበኛልይይት / Std. D | የዝምድና ኮሬሽንትCorrelations coefficient) | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | የመምህራን አተገባበር | የተማሪዎች ተሳትፎ |
| 1-6 | የመምህራን አተገባበር<br>Pearson Correlation<br>Sig. (2-tailed) | 15.46 | .621 | 1 | .855*<br>.030 |
| 7-10 | ተማሪዎች ተሳትፎ<br>Pearson Correlation<br>Sig. (2-tailed) | 8.75 | .447 | .855*<br><br>.030 | 1 |

$P<0.05$

የጉልህነት ተዛምዶ ($P<0.05$) እንዳላቸው በሰንጠረዥ 4.3 የተገለፀ ሲሆን በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ከተተነተነው ከሶስተኛው ሰንጠረዥ ስንነሳ ($r=.855^{*}$) በጣም ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በመጠቀም በክፍል ውስጥ የዕለቱን ትምህርት ከግብ ለማድረስ የመምህራን የማስተማሪያ

ዘዴ አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ እንዳለው ውጤቱ ($p < 0.05$) ጉልህ ተዛምዶያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያለው ($r=.855^*$) በመሆኑ በጣም ከፍተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

### 4.1.1.4 የስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ከጥገኛ ተላውጦዎች ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና

የጥናቱ አራተኛው ጥያቄ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? የሚል ነበር፡፡ ይህን ለመፈተሽ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም በነፃ ተላውጦውና በንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን ተጠቅሟል፡፡

## ሰንጠረዥ4.4 የስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ከንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች ጋር ያለውን ተዛምዶ ማሳያ በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ዘዴ

| ተ.ቁ | ስነ-ጽሁፍ ስራዎች ከጥገኛ ተላውጦዎች ጋርለ ያለውተዛምዶ | ማካይ/Mean | መደበኛልይይት Std.De | የዝምድና ኮፊሸንት (Correlationcoefficient) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ውጤት | 11 | 12 | 13 | 14 |
| | የስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ | 11.542 | .1882 | 1 | .542 | -.728 | .728 | .686 |
| 11 | ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን ትኩረት ስለሚስብ በራሳቸው ተነሳሽነት ቋንቋውን በልዩ ልዩ መልኩ ለመማር የተማርዎችን ተሳትፎ አነሳስተዋል። | 2.708 | .2984 | .542 | 1 | -.386 | .437 | .321 |
| 12 | የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩሂድት መጠቀም የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያነሳሱ ናቸው ። | 5.813 | 3.0843 | -.728 | -.386 | 1 | -.113 | -.182 |
| 13 | ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየቀያየሩ ለመተግበር አመች ናቸው። | 2.854 | .1671 | .728 | .437 | -.113 | 1 | .286 |
| 14 | ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ንዲሆኑ አድርጓል ። | 2.896 | .1287 | .686 | .321 | -.182 | .286 | 1 |

P<0.05

የጉልህነት ተዛምዶ (P<0.05) እንዳላቸው በሰንጠረዥ 4.1.4 የተገለጠ ሲሆን በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ከተተነተ ነው ከአራተኛው ሰንጠረዥ ስንነሳ በክፍል ውስጥ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን መጠቀም ከንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች ጋር ያለው ተዛምዶ የጥንካሬ ደረጃው ይለያል። ከቀረቡት ውጤቶች (r=.728) ከፍተኛና አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ፣ (r=-.728) ከፍተኛና አሉታዊ የሆነ ተዛምዶ፣ እንዲሁም (r=.686) ከፍተኛና አዎንታዊ የሆነ ተዛምዶ አላቸው። (r=.542) መካከለኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶአላቸው። ይህም ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየቀያየሩ ለመተግበር አመች እነደሆኑ፣ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂድት መጠቀም የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያነሳሱ መሆናቸው፣ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረጋቸው፣

እንደዚሁም ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን ትኩረት ስለሚስብ በራሳቸው ተነሳሽነት ቋንቋውን በልዩ ልዩ መልኩ ለመማር የተማርዎችን ተሳትፎ የሚያነሳሳ መሆኑን ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ($p< 0.05$) ዝምድና ያላቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ከንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች ጋር ያለው የተዛምዶ መጠን አብሬጅ 0.671 በመሆኑ ከፍተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

### 4.1.1.5 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ከስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና

የጥናቱ  አምስተኛው ጥያቄ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ምን ይመስላል? የሚል ነበር፡፡ ይህን ከስነ-ጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለውን ተዛምዶ በፒርሰን የተዛምዶ ትንተና ተግባራዊ ተደርጓል በመሆኑም በነፃ ተላውጠውና በንዑስ ጥገኛ ተላውጦዎች መካከል ያለውን የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን ተጠቅሟል፡፡

**ሰንጠረዥ 4.5 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ከስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ**

| ተ.ቁ | በአሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ስር የሚነሱ ተላውጦዎች | አማካይ/Mean | መደበኛልይይት /Std. D | የዝምድና ኮፊሸንት (Correlations coefficient) | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ውጤት | 15 | 16 | 17 |
| | የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ | 11.54 | .188 | 1 | -.728 | .728 | -.759 |
| 15 | ---የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ እየቀያየሩ መጠቀም የተማሪዎች ተሳትፎ | 2.875 | .1306 | -.728 | 1 | -.169 | .033 |
| 16 | ---አሳታፊየመማር ማስተማር ዘዴን በክፍል ውስጥ መጠቀም የመምህሩን ጉልበትና ጊዜ ይቀንሳል፡፡ | 2.896 | .1287 | .728 | -.169 | 1 | .162 |
| 17 | ---ተማሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ | 7.1875 | 4.5516 | -.759 | .033 | .162 | 1 |

P<0.05

የጉልህነት ተዛምዶ (P<0.05) እንዳላቸው በሰንጠረዥ 4.1.5 የተገለጠ ሲሆን በፒርሰን የተዛምዶ መጠን መለኪያ ከተተነተነው ከአምስተኛው ሰንጠረዥ ስንነሳ በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ከስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋርያለው የጥንካሬ ደረጃው ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም ከቀረበው ውጤት (r=-.759) እና(r=-.759) ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ ሲኖራቸው፣ (r=.728) ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ እየቀያየሩ መጠቀም የተማሪዎች ተሳትፎ እንደሚጨምር፣ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን በክፍል ውስጥ መጠቀም የመምህሩን ጉልበትና ጊዜ እንደሚቀንስ ፣ እንዲሁም ተማሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማድረግ ጠቀሜታ ያላቸው እንደሆነ ጥናቱ የሚያሳይ ነው፡፡ከንዑስ ጥገኛ ተላውጠዎች ጋር (p< 0.05) ዝምድና ያላቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ከስነጽሁፍ ስራዎች አስተዋጽኦ ጋር ያለው ተዛምዶ የጥንካሬ ደረጃው በአብሬጅ 0.738 በመሆኑ ከፍተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

### 4.1.1.6 ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና

የጥናቱ ስድስተኛው ጥያቄ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ምንድን ናቸው? የሚል ነበር፡፡ ችግሮቹ ከስነ-ጽሁፍ ስራዎች ጋር ተዛምዶ አለው ወይስ የለውም የሚለውን በፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተተንትኗል፡፡ በመሆኑም በነፃ ተላውጠውና በንዑስ ጥገኛ ተላውጠዎች መካከል ያለውን የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን ተጠቅሟል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.6 ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር ያለው ተዛምዶ ትንተና

| ተ.ቁ | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መተግበር በሚያጋጥሙ ችግሮች ስር የሚነሱ ተላውጠዎች | ማካይ/ mea | መደበኛልይይ /std.D | የዝምድና ኮፊሸንት (Correlationcoefficient) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ውጤት | 21 | 22 | 23 | 24 |
| | የስነጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ | 7.396 | 4.336 | 1 | -.944** | .152 | .682* | -.997** |
| 18 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ መምህሩ የእለቱንየትምህርት ይዘት ለማከናዎን የጊዜ እጥረት አጋጥሟቸዋል | 2.521 | .391 | -.944** | 1 | -.179 | -.650* | .949** |
| 19 | መምህሩ ክፍሉ ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለማግኘት ችግር ገጥሞታል ፡፡ | 2.896 | .129 | .152 | -.179 | 1 | -.441 | -.213 |
| 20 | በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በመብዛቱ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር አስቸግሯል ፡፡ | 3.042 | .3168 | .682* | -.650* | -.441 | 1 | -.648* |
| 21 | በክፍል ውስጥ የወንበ አደረጃጀት ባለመኖሩ አሳታ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበ አስቸግሯል፡፡ | 5.730 | 2.986 | -.997** | .949** | -.213 | -.648* | 1 |

P<0.05

የጉልህነት ተዛምዶ (P<0.05) እንዳላቸው በሰንጠረዥ 4.1.6 የተገለፀ ሲሆን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ከሚያጋጥሙ ችግሮች (ንዑስ ጥገኛ ተላውጠዎች) ጋር ያለውን ተዛምዶ በፒርሰን ተዛምዶ መለኪ ዘዴ ተተንትኗል፡፡ የጥንካሪ ደረጃው ይለያል፡፡ ከቀረቡት ውጤቶች (r=-.997**) እና (r=.944**) በጣም ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተዛምዶ አላቸው፡፡ (r=.682*) ደግሞ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ አላቸው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ (r=.152) በጣም ዝቅተኛ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ

አላቸው፡፡ ይኸውም  በክፍል ውስጥ የወንበር አደረጃጀት ባለመኖሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር እንደሚያስቸግር፣ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ መምህሩ የእለቱን የትምህርት ይዘት ለማከናዎን የጊዜ እጥረት እንደሚያጋጥመው፣ በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በመብዛቱ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር እንደሚያስቸግር  የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለማግኘት አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ብዙም ለችግር የማይዳርግ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ከጥገኛ ተላውጦው ጋር ($p< 0.05$) ዝምድና ያላቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ስነጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ከሚያጋጥሙ ችግሮች ጋር ያለው ተዛምዶ የጥንካሬ  ደረጃው በአብሬጅ 0.694 በመሆኑ ከፍተኛ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

#### 4.1.1.7 አጠቃላይ በተላውጦዎች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ተዛምዶ ማሳያ ትንተና

ከላይ በሰንጠረዥ4.1፣ 4.2፣ 4.4 ፣4.5 እና 4.6 የቀረቡትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ አጠቃላይ በተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶና፣ የጉልህነት ደረጃ ወይም በመካከላቸው የታየው ልዩነት ምን እንደሚመስል ተዳሷል፡፡ ይህም በጥናቱ ለቀረቡት ጥያቄዎች አጠቃላይ የሆነ መረጃ የሚገኝበት ነው፡፡ ይህን ለመፈተሽ የፒርሰን  የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የተዛምዶ የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችንተ ጠቅሟል፡፡

## ሰንጠረዥ4.7 በተላውጦዎች መካከል ያለው የእርስ በርስ ተዛምዶ

| ተ.ቁ | ተላውጦ | መምህር ተገባበር | የተማሪ ዎች ተሳትፎ | የስነፅሁፍ አስተዋጽኦ | አሳታፊየማስተ ማሪያዘዴጠቀ ሜታ | ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመምህራንተገባበር<br>Sig. (2-tailed) | 1 | .998**<br>.000 | .997**<br>.000 | .995**<br>.000 | .016<br>.960 |
| 2 | የተማሪዎችተሳትፎ<br>Sig. (2-tailed) | .998**<br>.000 | 1 | .993**<br>.000 | .991**<br>.000 | .038<br>.907 |
| 3 | የስነፅሁፍአስተዋጽኦ<br>Sig. (2-tailed) | .997**<br>.000 | .993**<br>.000 | 1 | .997**<br>.000 | .010<br>.975 |
| 4 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ<br>Sig. (2-tailed) | .995**<br>.000 | .991**<br>.000 | .997**<br>.000 | 1 | .026<br>.936 |
| 5 | ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች<br>Sig. (2-tailed) | .016<br>.960 | .038<br>.907 | .010<br>.975 | .026<br>.936 | 1 |

N=24 P<0.05

ሰንጠረዥ 4.7 እንደሚያሳየው የመምህራን አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር(r=.998**)፣ ከስነፅሁፍ አስተዋጽኦ ጋር (r=.997**)፣ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ ጋር (r=.995**)፣ በጣም ከፍተኛና አዎንታዊ የሆነ ጉልህ ተዛምዶ አሳይቷል፤ በአንፃሩ ደግሞ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች (r=.016) አዎንታዊና በጣም ዝቅተኛ የሆነ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

የተማሪዎች ተሳትፎ ከመምህራን አተገባበር ጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ(r=.998**)ተዛምዶ አሳይቷል፤ ከስነ-ፅሁፍ ጠቀሜታጋር አዎንታዊና (r=.993**) ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (r=.991**)ተዛምዶ አሳይቷል፤ በአንጻሩ ደግሞ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር አዎንታዊና መጣም ዝቅተኛ የሆነ (r=.038) ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

የስነ-ፅሁፍ አስተዋጽኦ ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (r=.993**) ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፤ ከመምህራን አተገባበር ጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ(r=.997**) ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፣ ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (r=.997**)ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፤ በአንጻሩ ደግሞ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮችጋር አዎንታዊና (r=.010)በጣም ዝቅተኛ የሆነ ተዛምዶ እንዳለው የትንተና ውጤቱ አሳይቷል፡፡

ሌላኛው ተላውጦ አሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ ሲሆን ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር አውንታዊና በጣም ዝቅተኛ የሆነ (r=.026) ተዛምዶ አሳይቷል፤ በአንጻሩ ድግሞ ከመምህራን አተገባበር ጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (r=.995**) ተዛምዶ አሳይቷል፣ ከተማሪዎች ተሳትፎጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (r=.991**) ከስነ-ጽሁፍ አስተዋጽኦ ጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (r=.997**) ተዛምዶ መኖሩን ያሳያል፡፡

ሌላኛው ሊነሳ የሚገባው የመጨረሻው ጉዳይ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር ያለው ተዛምዶ ነው፡፡ ይህ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ ጋር አዎንታዊና በጣም ዝቅተኛ የሆነ (r=.026) ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ከመምህራን አተገባበር ጋር አዎንታዊና በጣም ዝቅተኛ የሆነ (r=.016) ተዛምዶ አሳይቷል፤ ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር አዎንታዊና በጣም ዝቅተኛ የሆነ (r=.038) ተዛምዶ አሳይቷል፤ እንዲሁም ከስነ-ጽሁፍ አስተዋጽኦ ጋር አዎንታዊና በጣም ዝቅተኛ የሆነ (r=.010) ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ በምልከታ ከተገኘው መረጃ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ትንተና በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ዘዴ በጣም ከፍተኛ (ጠንካራ) ጉትህ የሆነ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

### 4.1.2 በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተዛምዷዊ ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለውን ተዛምዶ በጽሁፍ መጠይቅ ለመፈተሽ 21 ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ 21 ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ ምልከታ የተሰበሰበውን መረጃ ለማጠናከር ሲባል የቀረቡ ናቸው፡፡ ስለሆነም አጥኚው በምልከታ የተጠቀመበትን ቸክ ሊስት የተወሰኑ የቃላት ለውጥ በማድረግ በተመሳሳይ ርዕስ በፅሁፍ መጠይቅ ለመምህራንና ለተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም በምልከታ የተገኘው ውጤት በትክክል የተገለጸ መሆኑን ለማረጋገጥ አጥኚው የድርጊቱ ባለቤት ከሆኑት መምህራንና ተማሪዎች የተሰበሰበው የመረጃ ውጤት ጠቃሚ ነው ብሎ ስላመነበት ነው፡፡ በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት በ(SPSS) ኮምፒተር ሶፍት ዌር ውስጥ በማስገባት ውጤቱ ተሰልቷል፡፡ በስሌት የተገኘው ስታስቲካዊ መረጃ ደግሞ በእያንዳንዱ የጥናቱ የጥያቄ አይነት በቀረበበት በመከፋፈል በገለጻ ተብራርቶ

ቀርቧል፡፡ ከዚህ በታች በ4.1.2.1 እና በ4.1.2.2 ባለው ሰንጠረዥ በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ዘዴ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

### 4.1.2.1 ከመምህራን በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ በተላውጦዎች መካከል የእርስ በርስ ተዛምዶ ትንተና

ከመምህራን በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና አጠቃላይ በተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶና፣የጉልህነት ደረጃ ወይም በመካከላቸው የታየው ልዩነት ምን እንደሚመስል ተዳሷል፡፡ ይህም በምልከታ የተገኘው ውጤት ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ የቀረበ ውጤት ትንተና ነው፡፡ ይህን ለመፈተሽ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም የተዛምዶ የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን ተጠቅሟል፡

### ሰንጠረዥ4.8 ከመምህራን በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ አጠቃላይ የሆነ በተላውጦዎች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ተዛምዶ ትንተና

| ተ.ቁ | ተላውጦ | የመምህራን አተገባበር | የተማሪዎች ተሳትፎ | የስነፅሁፍ አስተዋጽኦ | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታ | ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመምህራን አተገባበር<br>Sig. (2-tailed) | 1 | -.857*<br>.029 | .707<br>.116 | .686<br>.132 | .686<br>.132 |
| 2 | የተማሪዎች ተሳትፎ<br>Sig. (2-tailed) | -.857*<br>.029 | 1 | -.728<br>.101 | -.765<br>.077 | -.765<br>.077 |
| 3 | የስነ-ፅሁፍ አስተዋጽኦ<br>Sig. (2-tailed) | .707<br>.116 | -.728<br>.101 | 1 | .728<br>.101 | .243<br>.643 |
| 4 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜ<br>Sig. (2-tailed) | .686<br>.132 | -.765<br>.077 | .728<br>.101 | 1 | .647<br>.165 |
| 5 | ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች<br>Sig. (2-tailed) | .686<br>.132 | -.765<br>.077 | .243<br>.643 | .647<br>.165 | 1 |

N=6 $P<0.05$

ሰንጠረዥ4.8 እንደሚያሳየው የመምህራን አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ ጉልህ (r=-.857*) ተዛምዶ አሳይቷ፤ ከስነ-ፅሁፍ አስተዋጽኦ ጋር አውንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (r=.707) ተዛምዶ አሳይቷ፣ ከአሳታፊ

የማስተማሪያ ዜዴዎች ጠቀሜታ ጋር (r=.686) ተዛምዶ አሳይቷ፣ እንዲሁም ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር አውንታዊና ከፍተኛ የሆነ (r=.686) ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

የተማሪዎች ተሳትፎ ከአተገባበር ጋር አሉታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (r=-.857*) (ጉልህ) ተዛምዶ አሳይቷ፤ ከስነ-ፅሁፍ አስተዋጽኦ ጋር አሉታዊና ከፍተኛ የሆነ (r=-.728) ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴዎች ጠቀሜታጋር አሉታዊና ከፍተኛ የሆነ (-.765) ተዛምዶ አሳይቷ፣ እንዲሁም ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር አሉታዊና ከፍተኛ የሆነ (-.765) ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

የስነ-ፅሁፍ አስተዋጽኦ ከአተገባበር ጋር አዎንታዊና ከፍተኛ የሆነ (r=.707)ተዛምዶ አሳይቷል፤ ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር አዎንታዊና ከፍኛ የሆነ (r=.728) ተዛምዶ አሳይቷል፤ እንዲሁም ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር አሉታዊና ከፍኛ የሆነ(r=-.728) ተዛምዶ አሳይቷል፤ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር አዎንታዊና ዝቅተኛ የሆነ (r=.243) ተዛምዶ እንዳለው የትንተና ውጤቱ አሳይቷል፡፡

አሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ ከተሳትፎ ጋር አሉታዊና ከፍተኛ የሆነ (r=-.765) ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፤ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር አዎንታዊና መካከለኛ የሆነ (r=.647) ተዛምዶ አሳይቷል፣ ከስነ-ጽሁፍ አስተዋጽኦ ጋር አዎንታዊና ከፍተኛ የሆነ (r=.728) ተዛምዶ አሳይቷል፣ከአተገባበር ጋር አዎንታዊና መካከለኛ የሆነ (r=.686) ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

የዚህ ትንተና የመጨረሻው ጉዳይ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር ያለው ተዛምዶ ነው፡፡ ይህ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ከተሳትፎ ጋር አሉታዊና ከፍተኛ የሆነ (r=-.765) ተዛምዶ አሳይቷል፤ ከአተገባበር ጋር አዎንታዊና ከፍተኛ የሆነ (r=.686) ተዛምዶ አሳይቷል፤ ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ ጋር አዎንታዊና ከፍተኛ የሆነ (r=.647) ተዛምዶ አሳይቷል፤ከስነ-ጽሁፍ አስተዋጽኦ ጋር አዎንታዊና ዝቅተኛ የሆነ(r=.243) ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ ከመምህራን በጽሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ትንተና በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ዘዴ በጣም ከፍተኛ (ጠንካራ)ና ጉትህ የሆነ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል ፡፡

## 4.1.2. 2 ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ በተላውጦዎች መካከል የእርስ በርስ ተዛምዶ ትንተና

ከላይ በሰንጠረዥ 4.1.2.2 ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና አጠቃላይ በተላውጦዎች መካከል ያለውን ተዛምዶና፣ የጉልህነት ደረጃ ወይም በመካከላቸው የታየው ልዩነት ምን እንደ ሚመስል ተዳሷል። ይህም በምልከታ የተገኘው ውጤት ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ የቀረበ ውጤት ትንተና ነው። ይህን ለመፈተሽ የፒርሰን የተዛምዶ መወሰኛ ተግባራዊ ተደርጓል። በመሆኑም የተዛምዶ የጥንካሬ ደረጃ ለማሳየት ያለው (2009) የገለፁትን አምስት የተዛምዶ ጥንካሬ መጠን መለኪያ መስፈርቶችን ተጠቅሟል።

### ሰንጠረዥ 4.9 ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰ በመረጃ አጠቃላይ የሆነ በተላውጦዎች መካከል ያለውን የእርስ በርስ ተዛምዶ ትንተና

| ተ.ቁ | ተላውጦ | የመምህራን አተገባበር | የተማሪዎች ተሳትፎ | የስነፅሁፍ አስተዋጽኦ | አሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ | ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመምህራን አተገባበር<br>Sig. (2-tailed) | 1 | .385**<br>.000 | .153<br>.054 | .316**<br>.000 | .097<br>.224 |
| 2 | የተማሪዎች ተሳትፎ<br>Sig. (2-tailed) | .385**<br>.000 | 1 | .168*<br>.034 | .305**<br>.000 | .194*<br>.014 |
| 3 | የስነ-ፅሁፍ አስተዋጽ<br>Sig. (2-tailed) | .153<br>.054 | .168*<br>.034 | 1 | .165*<br>.038 | .083<br>.296 |
| 4 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ Sig. (2-tailed) | .316**.<br>000 | .305**<br>.000 | .165*<br>.038 | 1 | .327**<br>.000 |
| 5 | ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች<br>Sig. (2-tailed) | .097<br>.224 | .194*<br>.014 | .083<br>.296 | .327**<br>.000 | 1 |

N=160 P<0.05

ሰንጠረዥ 4.9 እንደሚያሳየው የመምህራን አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ እና ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ አዎንታዊ ጋር ጉልህ የሆነ ተዛምዶ አሳይቷ፤ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች፣ ከስነፅሁፍ ጠቀሜታ እና ከግንኙነት ጋር ደግሞ አዎንታዊና ዝቅተኛ የሆነ ተዛምዶ አሳይቷል። የተማሪዎች ተሳትፎ ከሁሉም ተላውጦዎች ጋር ማለትም

ከአተገባበር፣ ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ፣ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች፣ ከግንኙነትና ከስነፅሁፍ ጠቀሜታ ጋር ጉልህ የሆነ አዎንታዊ ተዛምዶ አሳይቷል ።

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታ ከአተገባበር፣ ከተሳትፎ፣ ከስነ-ጽሁፍ ጠቀሜታና ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር አውንታዊና ጉልህ የሆነተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ከዚህ በተገላቢጦ ከግንኙነት ጋር አውንታዊና በጣም ዝቅተኛና ጉልህነት የሌለው ተዛምዶ አሳይቷል፡፡

የዚህ ትንተና የመጨረሻው ጉዳይ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር ያለው ተዛምዶ ነው። ይህ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ከተሳትፎ፣ ከግንኙነትና ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ ጋር አውንታዊና ጉልህ የሆነ ተዛምዶ አሳይቷል፤ ይሁን እንጂ ከአተገባበርና ከስነጽሁፍ ጠቀሜታ ጋር አውንታዊና በጣም ዝቅተኛ የሆነ ተዛምዶ እንዳለው አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ ከተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳትፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያላቸው ተዛምዶ ትንተና በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ዘዴ ጉትህ የሆነ ተዛምዶ ያለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል ።

## 4.1.3 በክፍል ውስጥ ምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ ትንተና፡፡

በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር እና በተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ ዙሪያ በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ በአጥኚው፣ በመምህራንና በተማሪዎች በተሰበሰቡ መረጃዎች በተመለከተ የሚያሳየው ቁጥራዊ መረጃ እንደየጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ለምልከታም ሆነ ለጽሁፍ መጠይቅ 21 መጠይቅ የቀረቡ ሲሆን ከአንዳንድ የቃላት አጠቃቀም በስተቀር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ዋናው የመረጃ መሰብሰቢያ ምልከታ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቁ ደግሞ ደጋፊዎች ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ አራት አማራጮች ተሰጥቷል፡፡ ከዚህ በመነሳትም እንደ የጥያቄዎቹ ቅደም ተከተል ስታስቲካዊ መረጃውን መሰረት በማድረግ ተተንትኗል፡፡

## 4.1.3.1 በክፍል ውስጥ ምልከታ የተሰበሰቡ መረጃዎች በቁጥርና በመቶኛ ትንተና

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ምን ይመስላል? በምዕራፍ ሁለት ላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረት አንድ የቋንቋ መምህር ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋውን ሲያስተምር አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርጓል የሚባለው፡- ለማስተማሪያነት በቀረበዉ የስነ-ፅሁፍ ስራ አማካይነት የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስተማር ከቻሉ፤ በቀረበው የስነ-ፅሁፍ ስራ አማካኝነት ተማሪዎቹን በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን በማደራጀት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ እንዲሳተፉ ማድረግ ከቻሉ፤የተጠቀመበት የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎቹን ንቁ ተሳታፊ ካደረጋቸው፤ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ያልገባቸውን በመጠየቅና በመመለስ መማማር ከቻሉና መምህሩም እነዚህንና መሰል ተግባራት ማከናዎን ከቻለ ነው፡፡

ሰንጠረዥ4.10 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር በቁጥርና በመቶኛ ስልት

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | | | የምልታ በዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4(%) | 3(%) | 2(%) | 1(%) | |
| 1 | መምህሩ/ሯ...ተማሪዎችን እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ ወዘተ. በማድረግ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ አድርገዋል | - | 16(66.7%) | 8(33.3%) | - | 24 |
| 2 | መምህሩ/ሯ ...ተማሪዎችን በግል በጥንድና በቡድን በማደራጀት የክፍልና የቤት ስራ ተግባራትን እየሰሩ እንዲሳተፉ አድርገዋል፡፡ | - | 14(58.3%) | 10(41.7%) | - | 24 |
| 3 | መምህሩ/ሯ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመጠቀማቸው ሁሉንም ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ አበረታተዋል፡፡ | - | 19(79.2%) | 5(20.8%) | - | 24 |
| 4 | መምህሩ/ሯ...በሚተገብሩበት ጊዜ እንደትምህርቱይዘት የተለያዩ ዘዴዎችንበመጠቀም ተማሪዎችእንዲሳተፉአድርገዋል፡ | - | 18(75.0%) | 6(25.0%) | - | 24 |
| 5 | መምህሩ/ሯ... በሚተገብሩበት ጊዜ የተለያዩ ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲሳተፉአድርገዋል፡፡ | - | 18(75.0) | 6(25.0%) | - | 24 |
| 6 | መምህሩ/ሯ...በሚተገብሩበት ጊዜ ተማሪዎችን ከፍተኛ፣መካከለኛና ዝቅተኛእንዲሁምፆታንና እድሜን የማከለ አድርገው በመመደብ ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አበረታተዋል | - | 8(33.3%) | 16(66.7%) | - | 24 |

በክፍል ውስጥ በተደረገ 24 ጊዜ ምልከታ መምህራን በ16(66.7%) ክፍለ ጊዜዎች ተማሪዎችን እንዲከራከሩ፣እንዲወያዩ ወዘተ.በማድረግ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን

ተግባራዊ አድርገዋል። በ14(58.3%)ክፍለ ጊዜዎች ደግሞተማሪዎችን በግል፣በጥንድና በቡድን በማደራጀት የክፍልና የቤት ስራ ተግባራትን እየሰሩ እንዲሳተፉ በማድረግ አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴን በከፊል ተግባራዊ ተደርጓል። በ19(79.2%) ክፍለ ጊዜዎች በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን በንቃት እንዲሳተፉ አበረታተዋል። 18(75%) ክፍለ ጊዜዎች እንደትምህርቱ ይዘት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዲሳተፉ አድርገዋል። 18(75%)ክፍለ ጊዜዎች የተለያዩ ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ በመጠየቅ ተማሪዎችን እንዲሳተፉ አድርገዋል። በአንፃሩ16 (66.6%) ክፍለ ጊዜዎች ተማሪዎችን በደረጃ ከፍተኛ፣መካከለኛና ዝቅተኛ እንዲሁም ፆታንና እድሜን ያማከለ አድርጎ በመመደብ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ አለመደረጉን የተገኘዉ ዉጤት አመላክቷል።ከዚህ የምልከታ ውጤት የምንገነዘበው የ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ የሚደርጉ መሆናቸውን ነዉ። ይህን ለማለት ያስቻለኝ ምክንያት ደግሞ ከተደረጉት 24 ምልክታዎች መካከል በ64.58% ክፍለ ጊዜዎች ዘዴው በከፍተኛ ሁኔታ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ ሁኔታ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በ35.42% ክፍለ ጊዜዎች ግን ያልተተገበረባቸው ናቸው። ስለሆነም ሙሉ በሙሉ ባይሆንም እንኳን በአብዛኛው ክፍለ ጊዜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

### 4.1.3.2. ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋውን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ

ምዕራፍ ሁለት ላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረት ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋውን ሲማሩ ተሳትፎ አላቸው የሚባለው፡- በክፍል ውስጥ በግል፣በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በመስራት ሲሳተፉ፤ በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት፣ክርክር፣ ንግግር፣ወዘተ. በሚከናወኑበት ጊዜ ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ፤በእለቱ ትምህርት ላይ ጥያቄ በመጠየቅና መልስ በመስጠት፣ አስተያየት በመስጠት ሲሳተፉ እና በክፍል ውስጥ እርስ በእርስ የሚማማሩበትን መንገድ በመፍጠር በንቃት መሳተፍ ሲችሉ ነው።

## ሰንጠረዥ 4.11 ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋውን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | | | የምልታ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4(%) | 3(%) | 2 (%) | 1(%) | |
| 7 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግል፣በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በመስራት ተሳትፈዋል። | - | 17(70.8%) | 7(29.2%) | - | 24 |
| 8 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት፣ክርክር፣ንግግር፣ወዘተ. በሚከናወኑበት ጊዜ ትኩረት በመስጠት ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል። | - | 16(66.7%) | 8(33.3%) | - | 24 |
| 9 | ተማሪዎች በእለቱ ትምህርት ላይ ጥያቄ በመጠየቅና መልስ በመስጠት፣ አስተያየት በመስጠት ተሳትፎ አድርገዋል ። | - | 16(66.7%) | 8(33.3%) | - | 24 |
| 10 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እርስ በአርስ የሚማማሩበትን መንገድ በመፍጠር ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል ። | - | 9(37.5%) | 15(62.5 %) | - | 24 |

በዚህ መሰረት በክፍል ውስጥ በተደረገ 24 ጊዜ ምልከታ ተማሪዎች በ17 (70.8%) ክፍለ ጊዜዎች በክፍል ውስጥ በግል፣በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በመስራት ተሳትፈዋል። በ16 (66.7%) ክፍለ ጊዜዎች በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት፣ክርክር፣ ንግግር፣ወዘተ. በሚከናወኑበት ጊዜ ትኩረት በመስጠት ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል። በ16(66.7%) ክፍለ ጊዜዎችተማሪዎች በእለቱ ትምህርት ላይ ጥያቄ በመጠየቅ፣ መልስ በመስጠት፣ አስተያየት በመስጠት ተሳትፎ አድርገዋል። በአንጻሩ በ15(62.5%)ክፍለ ጊዜዎች በክፍል ውስጥ እርስ በአርስ የሚማማሩበትን መንገድ በመፍጠር ንቁ ተሳታፊ አለመሆናቸውን የተገኘው ውጤት አመላክቷል። ከዚህ የምልከታ ውጤት የምንገነዘበው የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ሲማሩ ተሳትፎ የሚደርጉ መሆናቸውን ነው። ይህን ለማለት ያስቻለኝ ምክንያት ደግሞ ከተደረጉት 24 ምልክታዎች መካከል በ60.42% ክፍለ ጊዜዎች ዘዴው በከፍተኛ ሁኔታ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ ሁኔታ ተሳትፎ ያደረጉ ሲሆን በ39.58% ክፍለ ጊዜዎች ግን ተሳትፎ ያልተደረገባቸው ናቸው። ስለሆነም ሙሉ በሙሉ ባይሆንም እንኳን በአብዛኛው ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ተሳትፎ ያደረጉ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

### 4.1.3.3 የስነ-ጽሁፍ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው አስተዋጽኦ

ስነ-ጽሑፍ ውበት፣ማራኪነት፣አስደሳችነት ስላለው በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ጉልህ አስተዋፅዖ ያበረክታል፤ በትምህርት ሂደትም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነቃቃል ፤ስነ-ፅሁፍ የሰዎችን ሀሳብና ስሜት ይገልፃል፡፡ ውስብስብ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በማድነቅ መተንትን ይማሩበታል፣ የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ ያጎለብታል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.12 የስነ-ጽሁፍ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው አስተዋጽኦ በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | | | የምልከታ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4(% | | 2(%) | 1(%) | |
| 11 | ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎች ትኩረት ስሚስብ በራሳቸው ተነሳሽነት ቋንቋውን በልዩ ልዩ መልኩ ለመማር የተማርዎችን ተሳትፎ አነሳስተዋል፡፡ | - | 20(83.3%) | 4(16.7%) | - | 24 |
| 12 | የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂድት መጠቀም የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያነሳሱ ናቸው ፡፡ | - | 20(83.3%) | 4(16.7%) | - | 24 |
| 13 | ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች እየቀያየሩ ለመተግበር አመች ናቸው፡፡ | - | 20(83.3%) | 4(16.7%) | - | 24 |
| 14 | የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አድርጓል ፡፡ | - | 20(83.3%) | 4(16.7%) | - | 24 |

በክፍል ውስጥ በተደረገ 24 ጊዜ ምልከታ 20 (83.3%) ክፍለ ጊዜዎች ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን ትኩረት ስለሚስብ በራሳቸው ተነሳሽነት ቋንቋውን በልዩ ልዩ መልኩ ለመማር የተማሪዎችን ተሳትፎ ያነሳሱ መሆኑ፡፡ 20(83.3%) ክፍለ ጊዜዎች የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂድት መጠቀም የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያነሳሱ መሆናቸው፡፡ 20(83.3%) ክፍለ ጊዜዎች ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየቀያየሩ ለመተግበር አመች መሆናቸው፡፡ 20(83.3%) ክፍለ ጊዜዎች የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ እየቀያየሩ መጠቀም የተማሪዎች ተሳትፎ የሚጨምር መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ ከዚህ

ውጤት የምንገነዘበው ስነጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ ለመማር ማስተማሩ ተግባር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ከተደረጉት 24 ምልክታዎች መካከል በ83.33% ክፍለ ጊዜዎች ስነጽሁፋዊ ስራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው መሆኑን ሲያመለክት 16.67% ግን ስነጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ የሌላቸው መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

## 4.1.3.4 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ

በክፍል ውስጥ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ ከሚያስገኙት ጥቅሞች መካከልተማሪዎች በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ዉጭ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ፤የተማሪዎችን የማገናዘብ ችግር የመፍታት፣ አዲስ ነገር የማመንጨትና እርስ በርስ የመረዳዳት ባህል እንዲሰራበት የማድረግ ወዘተ. ጥቅምን ያስገኛል፡፡

### ሰንጠረዥ4.13 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | | | የምልከታ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4(%) | 3(%) | 2(%) | 1(%) | |
| 15 | የተለያዩአሳታፊየማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ እየቀያየሩ መጠቀም የተማሪዎች ተሳትፎ ይጨምራል ፡፡ | 4(16.7%) | 13(54.2%) | 7(29.2%) | - | 24 |
| 16 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎች ነገሮችን የመተንተን፣የመገምገምችሎታን ለማሳደግወዘተ.ከፍተኛአስተዋጽኦአለው፡ | 4(16.7%) | 12(50%) | 8(33.3%) | - | 24 |
| 17 | አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን በክፍል ውስጥ መጠቀም የመምህሩን ጉልበትና ጊዜ ይቀንሳል፡፡ ተማሪዎችን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ | 3(12.5%) | 12(50%) | 9(37.5%) | - | 24 |

በክፍል ውስጥ በተደረገ 24 ጊዜ ምልከታ17(70.9%) ክፍለ ጊዜዎች የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ እየቀያየሩ በሚጠቀሙ ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ እንደሚጨምር፤ ነገሮችን የመተንተን የመገምገም ችሎታን ለማሳደግ ወዘተ. ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው፤ 16(66.7%) ክፍለ ጊዜዎች አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን

በክፍል ውስጥ መጠቀም የመምህሩን ጉልበትና ጊዜ እንደሚቀንስ፤15(62.5%) ክፍለ ጊዜዎችተማሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የማድረግ ጠቀሜታ እዳለውጥናቱ ያሳያል ። ከዚህ ውጤት የምንገነዘበው ስነጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ ለመማር ማስተማሩ ተግባር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያሳያል። ምክንያቱም ከተደረጉት 24 ምልክታዎች መካከል በ66.67% ክፍለ ጊዜዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን ሲያመለክት 33.33% ግን ጠቀሜታ የሌላቸው መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

### 4.1.3.5 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

የመጽሀፉን ይዘት ለማስተማር የተሰጠው ጊዜ አለመጣጣም፤የክፍል ተማሪ ጥምርታ ያለመጣጣም ችግር ፤ከማስተማሪያ መሳሪያዎችና ከስነጽሁፋዊ ስራዎች ጋር የተያያዘ ችግር፤ለመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ያለመስጠት ችግር እንደሆኑ በምዕራፍ ሁለት ተገልጾዋል።

## ሰንጠረዥ 4.14 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | | | የምልታ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4% | 3(%) | 2(%) | 1(%) | |
| 18 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥተግባራዊ ማድረግ መምህሩ የእለቱን የትምህርትይዘት ለማከናዎን የጊዜ እጥረት አጋጥሟቸዋል ። | 4(16.7%) | 12(50 %) | 8(33.3%) | - | 24 |
| 19 | በክፍል ውስጥ የወንበርአደረጃጀት ባለመኖሩ | 4(16.7%) | 10(41.7 %) | 10(41.7) | - | 24 |
| 20 | በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በመብዛቱ | 5(20.8%) | 10(41.7% ) | 9(37.5%) | - | 24 |
| 21 | መምህሩ ክፍሉ ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለማግኘት ችግር ገጥሞታል ። | 4(16.7%) | 10(41.7 %) | 10(41.7%) | - | 24 |

በክፍል ውስጥ በተደረገ 24 ጊዜ ምልከታ 16(66.7%) ክፍለ ጊዜዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ መምህሩ የእለቱን የትምህርት ይዘት ለማከናዎን የጊዜ እጥረት እንዳጋጠምው፡፡ 16(66.7%) ክፍለ ጊዜዎች በክፍል ውስጥ የወንበር አደረጃጀት ባለመኖሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ማስቸገሩ፡፡ 15(62.5%) ክፍለ ጊዜዎች በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር በመብዛቱ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ያስቸገረ መሆኑን፡፡ 14(58.4%) ክፍለ ጊዜዎች መምህሩ ክፍሉ ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለማግኘት ችግር እንደገጠመ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ከዚህ ውጤት የምንገነዘበው መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ሙሉ ለሙሉም ባይሆን ችግር የሚገጥም መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም ከተደረጉት 24 ምልክታዎች መካከል በ61.46% ክፍለ ጊዜዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ችግር የሚገጥም መሆኑን ሲያመለክት 38.54% ደግሞ ችግር የማይገጥም መሆኑን የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

### 4.1.3.6 በጽሁፍ መጠይቅ በቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች በቁጥርና በመቶኛ ትንተና፡፡

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ምን ይመስላል? ምዕራፍ ሁለት እንደተገለጸው አንድ የቋንቋ መምህር ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋውን ሲያስተምር አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርጓል የሚባለው፡- ለማስተማሪያነት በቀረበው የስነ-ፅሁፍ ስራ አማካይነት የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ማስተማር ከቻሉ፤በቀረበው የስነ-ፅሁፍ ስራ አማካኝነት ተማሪዎቹን በተናጠል፣ በጥንድና በቡድን በማደራጀት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ እንዲሳተፉ ማድረግ ከቻሉ፤የተጠቀመበት የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪዎቹን ንቁ ተሳታፊ ካደረጋቸው፤በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች ያልገባቸውን በመጠየቅና በመመለስ መማማር ከቻሉና መምህሩም እነዚህንና መሰል ተግባራት ማከናዎን ከቻለ ነው፡፡

## ሰንጠረዥ 4.15 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መረጃው የተሰበሰበው | 4እና3(%) | 2እና1(%) |
| 1 | …ተማሪዎችን እንዲከራከሩ እንዲወያዩ ወዘተ. በማድረግ እንዲሳተፉ አደርጋለሁ፡፡ | ከመምህራን | 4(66.7%) | 2(33.3%) |
| | | ከተማሪዎች | 105(65.6%) | 55(34.4 %) |
| 2 | ..ተማሪዎችን በግል በጥንድና በቡድን በማደራጀት የክፍልና የቤት ስራ ተግባራትን እየሰሩ እንዲሳተፉ አደርጋለሁ ፡፡ | ከመምህራን | 2(33.3%) | 4(66.7%) |
| | | ከተማሪዎች | 150 (93.7%) | 10(6.3%) |
| 3 | በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመጠቀም ሁሉንም ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ አበረታታለሁ፡፡ | ከመምህራን | 4(66.7%) | 2(33.3%) |
| | | ከተማሪዎች | 151(94.4%) | 9(5.6%) |
| 4 | ..በምተገብርበት ጊዜ እንደ ትምህርቱ ይዘት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዲሳተፉ አደርጋለሁ፡፡ | ከመምህራን | 3(50%) | 3(50%) |
| | | ከተማሪዎች | 93(58.1%) | 67(41.9%) |
| 5 | .. በምተገብርበት ጊዜ የተለያዩ ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ በመጠየቅ ተማሪዎች | ከመምህራን | 3(66.7%) | 3(33.3%) |
| | | ከተማሪዎች | 112(70%) | 48 (30%) |
| 6 | ..በምተገብርበት ጊዜ ተማሪዎችን ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ እንዲሁም ፆታንና እድሜን ያማከለ አድርጌ በመመደብ ሃሳባቸውን እንዲለዋወጡና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አበረታታለሁ ፡፡ | ከመምህራን | 3(50%) | 3(50%) |
| | | ከተማሪዎች | 97(60.6%) | 53(39.4%) |

ከተራ ቁጥር1 እስከ 6 የተዘረዘሩት ተላውጦዎች ምህራን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው አሳታፊ ማስተማሪያ ዘዴዎችን እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ የሚመለከት ሲሆን የመምህራንና የተማሪዎችን መረጃ መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

…ተማሪዎችን እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ ወዘተ.በማድረግ እንዲሳተፉ አደርጋለሁ ለሚለው ጥያቄ 4(66.7%) መምህራንና 105(65.6%) ተማሪዎች መስማማታቸውን ሲገልጹ 2(33.3%) መምህራንና 55(34.4%) ተማሪዎች ግን የማይስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ..ተማሪዎችን በግል በጥንድና በቡድን በማደራጀት የክፍልና የቤት ስራ

ተግባራትን እየሰሩ እንዲሳተፉ አደርጋለሁ ለሚለው ጥያቄ 2(33.3%)መምህራንና 150(93.7%)ተማሪዎች መስማማታቸውን ሲገልጹ 4(66.7%) መምህራንና 10(6.3%) ተማሪዎች ግን የማይስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመጠቀም ሁሉንም ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ አበረታታለሁ፡፡ ለሚለውጥያቄ 4(66.7%) መምህራንና 151(94.4%) ተማሪዎች መስማማታቸውን ሲገልጹ 2(33.3%) መምህራን 9(5.6%) ተማሪዎች ግን የማይስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ..በምተገብርበት ጊዜ እንደ ትምህርቱ ይዘት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎች እንዲሳተፉ አደርጋለሁ ለሚለው ጥያቄ 4(66.7%) መምህራንና 93(58.1%) ተማሪዎች መስማማታቸውን ሲገልጹ 2(33.3%) መምህራንና 67(41.9%)ተማሪዎች ግን የማይስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡...በምተገብርበት ጊዜ የተለያዩ ጥያቄዎችን በክፍል ውስጥ በመጠየቅ ተማሪዎች እንዲሳተፉ አደርጋለሁ ለሚለው ጥያቄ 3(50%) መምህራንና 112(70%) ተማሪዎች መስማማታቸውን ሲገልጹ 3(50%)መምህራንና 48(30%) ግን የማይስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡...በምተገብርበት ጊዜ ተማሪዎችን ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ እንዲሁም ፆታንና እድሜን ያማከለ አድርጌ በመመደብ ሃሳባቸውን እንዲለዋዎጡና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አበረታታለሁ ለሚለው ጥያቄ 4(66.7%) መምህራን 96(60.6%) ተማሪዎችመስማማታቸውን ሲገልጹ 2(33.3%) መምህራንና 53(39.4%) ግን የማይስማሙ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከመምህራንና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ ውጤትየተገኘው የ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን በአብዛኛዎቹ መምህራን ስነፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ተግባራዊ የሚደርጉ ናቸው፡፡ ይህን ለማለት ያስቻለኝ ምክንያት ደግሞ ከ6 መምህራን ውስጥ በ55.6% እንዲሁም ከ160 ተማሪዎች 74.6% ዘዴው በከፍተኛ ሁኔታ፣ በመካከለኛና በዝቅተኛ ሁኔታ ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆናቸውን ሲገልጹ 44.4% መምህራንና 25.6% ተማሪዎች ግን የማይተገብሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ስለሆነም ሙሉ በሙሉ ባይሆንም እንኳን በአብዛኛው ክፍለ ጊዜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን የተገኘው የመረጃ ትንተና ያመለክታል፡፡

### 4.1.3.7 ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋውን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ

ምዕራፍ ሁለት ላይ በቀረበው ሀሳብ መሰረት ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ ቋንቋውን ሲማሩ ተሳትፎ አላቸው የሚባለው፡- በክፍል ውስጥ በግል፣በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በመስራት ሲሳተፉ፤በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት፣ክርክር፣ ንግግር፣

ወዘተ. በሚከናወኑበት ጊዜ ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ፤በእለቱ ትምህር ላይ ጥያቄ በመጠየቅና መልስ በመስጠት፣አስተያየት በመስጠት ሲሳተፉ እና በክፍል ውስጥ እርስ በእርስ የሚማማ ሩበትን መንገድ በመፍጠር በንቃት መሳተፍ ሲችሉ ነው፡፡

## ሰንጠረዥ4.16 ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋውን ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መረጃው የተሰበሰበው | 4እና3(%) | 2እና1(%) |
| 7 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግል፣ በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በመስራት ተሳትፈዋል፡፡ | ከመምህራን | 2(33.3%) | 4(66.7%) |
| | | ከተማሪዎች | 137(85.6%) | 23(14.4%) |
| 8 | ተማሪዎችበክፍል ውስ የቡድንውይይት፣ ክርክር፣ንግግር፣ወዘተ. በሚከናወኑበት ጊዜ ትኩረት በመስጠት ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ | ከመምህራን | 3(50%) | 3(50%) |
| | | ከተማሪዎች | 101(63.1%) | 59 (36.9%) |
| 9 | ተማሪዎች በእለቱ ትምህር ላይ ጥያቄ በመጠየቅና መልስ በመስጠት፣ አስተያየት በመስጠት ተሳትፎ አድርገዋል ፡፡ | ከመምህራን | 2(33.3%) | 4(66.7%) |
| | | ከተማሪዎች | 106 (66.2%) | 54 (33.8%) |
| 10 | ተማሪዎችበክፍል ውስጥ እርስ በእርስ የሚማማሩበትን መንገድ በመፍጠርንቁ ተሳታፊ ሆነዋል ፡፡ | ከመምህራን | 4(66.7%) | 2(33.3%) |
| | | ከተማሪዎች | 97(60.6%) | 63 (39.4%) |

ሁለተኛው ከተራ ቁጥር 7 እስከ10 የተዘረዘሩት ተላውጦዎች የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚመለከቱ ሲሆን ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ቋንቋውን ሲማሩ ተሳትፏቸው ምን ይመስላል? የሚለውን የሚመለከት ሲሆን የመምህራንና የተማሪዎችን መረጃ መሰረት በማድረግ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግል፣ በጥንድና በቡድን የሚሰሩ ተግባራትን በመስራት ተሳትፈዋል ለሚለው ጥያቄ 3(50%) መምህራንና137(85.6%) ተማሪዎች የሚሳተፉ መሆናቸውን ሲገልጹ 3(50%)መምራንና 23(14.4%) ተማሪዎች ግን የማይሳተፉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት፣ክርክር፣ንግግር፣ ወዘተ. በሚከናወኑበት ጊዜ ትኩረት በመስጠት ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል ለሚለው ጥያቄ 1(16.7%)መምህርና 101(63.1%) ተማሪዎች የሚሳተፉ መሆናቸውን ሲገልጹ 5(83.3%)

መምህራንና 59(36.4%) ተማሪዎች ግን የማይሳተፉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ተማሪዎች በእለቱ ትምህርር ላይ ጥያቄ በመጠየቅና መልስ በመስጠት፣ አስተያየት በመስጠትተሳትፎ አድርገዋል ለሚለው ጥያቄ 3(50%) መምህራንና 106(66.2%) ተማሪዎች የሚሳተፉ መሆናቸውን ሲገልጹ 3(50%) መምህራንና 54(33.8%) ተማሪዎች ግን የማይሳተፉ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እርስ በአርስ የሚማማሩበትን መንገድ በመፍጠር ንቁ ተሳታፊ ሆነዋል ለሚለው ጥያቄ 4(66.7%) መምህራንና 97(60.5%) የሚሳተፉ መሆናቸውን ሲገልጹ 2(33.3%) መምህራንና 63(39.4) ተማሪዎች ግን የማይሳተፉ መሪሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ የጽሁፍ መጠይቅ ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስዎችን ተጠቅመው ሲማሩ ተሳትፏቸው በመምህራንና በተማዎች መካከል የውጤት ልዩነት ታይቷል፡፡ 45.8% መምህራን ይሳተፋሉ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ነገር ግን 73.5% ተማሪዎች ደግሞ ይሳተፋሉ የሚልምላሽ ሰጥተዋል፡፡ 54.2% መምህራንና 26.5% ተማሪዎች የማይሳተፉ መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

## 4.1.3.8 ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው አስተዋጽኦ

ስነ-ጽሑፍ ውበት፣ ማራኪነት፣ አስደሳችነት ስላለው በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ጉልህ አስተዋፅዖ ያበረክታል፤ በትምህርት ትሂደትም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነቃቃል ፤ስነ-ፅሁፍ የሰዎችን ሀሳብና ስሜት ይገልፃል፡፡ ውስብስብ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን በማድነቅ መተንትን ይማሩበታል፣የተማሪዎችን ግላዊተሳትፎ ያጎለብታል፡፡

## ሰንጠረዥ4.17 የስነ-ጽሁፍ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው አስተዋጽኦ በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መረጃው የተሰበሰበው | 4እና3(%) | 2 እና1(%) |
| 11 | ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን ትኩረት ስሚስብ በራሳቸውተነሳሽነት ቋንቋውን በልዩ ልዩ መልኩ ለመማር የተማርዎችንተሳትፎአነሳስተዋል፡፡ | ከመምህራን | 3(50%) | 3(50%) |
| | | ከተማሪዎች | 157(98.1%) | 3 (1.9%) |
| 12 | የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂድት መጠቀም የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎየሚያነሳሱ ናቸው ፡፡ | ከመምህራን | 4(66.7%) | 2(33.3%) |
| | | ከተማሪዎች | 153(95.6%) | 7 (4.4%) |
| 13 | ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍልውስጥ የተለያዩአሳታፊየማስተማሪያ ዘዴዎችን እየቀያየሩ ለመተግበር አመች ናቸው፡፡ | ከመምህራን | 3(50%) | 3(50%) |
| | | ከተማሪዎች | 152(95%) | 8 (5%) |
| 14 | የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀምተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ አድርጓል ፡፡ | ከመምህራን | 4(66.7%) | 2(33.3%) |
| | | ከተማሪዎች | 149(93.1%) | 11(6.9%) |

ሶስተኛው ከተራ ቁጥር11 እስከ14 የተዘረዘሩት ተላውጦዎች የስነ-ጽሁፍ ስራዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸውን አስተዋጽኦ የሚመለከት ሲሆን ከመምህራንና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን ትኩረት ስለሚስብ በራሳቸው ተነሳሽነት ቋንቋውን በልዩ ልዩ መልኩ ለመማር የተማርዎችን ተሳትፎ ያነሳሱ ናቸው ለሚለው ጥያቄ 3(50%) መምህራንና 157(98.1%) ተማሪዎች ተሳትፎን የሚያነሳሱ መሆኑን ሲገልጹ 3(50%) መምህራንና 3(1.9%)ተማሪዎች ግን ተሳትፎን የማያነሳሱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የስነጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂድት መጠቀም የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያነሳሱ ናቸው ለሚለው ጥያቄ 4(66.7%) መምህራንና 153(95.6%) ተማሪዎች ተሳትፎን የሚያነሳሱ መሆኑን ሲገልጹ 2(33.3%) መምህራንና 7(4.4%) ተማሪዎች ግን ተሳትፎን የማያነሳሱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ስነጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ

አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እየቀያየሩ ለመተግበር አመች ናቸው ለሚለው ጥያቄ 3(50%) መምህራንና 152(95%) ተማሪዎች ተሳትፎን የሚያነሳሱ መሆኑን ሲገልጹ 3(50%) መምህራን 8(5%) ግን ተሳትፎን የማያነሳሱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ እየቀያየሩ መጠቀም የተማሪዎች ተሳትፎ ይጨምራ ለሚለው ጥያቄ 3(50%) መምህራንና 149 (93.1%) ተማሪዎች ተሳትፎን የሚያነሳሱ መሆኑን ሲገልጹ 3(50%) መምህራንና 11(6.9%) ግን ተሳትፎን የማያነሳሱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ የጽሁፍ መጠይቅ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ ለመማር ማስተማሩ ተግባር ያላቸው አስተዋጽኦ መካከለኛ የሆነ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም 58.4% መምህራንና 95.45% ተማሪዎች ስነጽሁፋዊ ስራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው መሆኑን ሲያመለክቱ 41.6% መምህራንና 4.55% ተማሪዎች ግን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አስተዋጽኦ የሌላቸው መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

### 4.1.3.9 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ

በክፍል ውስጥ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ተግባራዊ ማድረግ ከሚያስገኙት ጥቅሞች መካከል ተማሪዎች በትምህርት ቤትና ከትምህርት ቤት ውጭ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ፤ የተማሪዎችን የማገናዘብ ችግር የመፍታት፣አዲስ ነገር የማመንጨትና እርስ በርስ የመረዳዳት ባህል እንዲሰራበት የማድረግ ወዘተ. ጥቅምን ያስገኛል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.18 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መረጃው የተሰበሰበው | 4እና3(%) | 2 እና1(%) |
| 15 | የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ እየቀያየሩ መጠቀም የተማሪዎች ተሳትፎ ይጨምራል፡፡ | ከመምህራን | 5(83.3%) | |
| | | ከተማሪዎች | 151(94.4%) | 9 (5.6%) |
| 16 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎች ነገሮችን የመተንተን የመገምገም ችሎታን ለማሳደግ ወዘተ.ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ | ከመምህራን | 5(83.3%) | 1(16.7%) |
| | | ከተማሪዎች | 152 (95%) | 8 (5%) |
| 17 | አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን በክፍል ውስጥ መጠቀም የመምህሩን ጉልበትና ጊዜ ይቀንሳል ተማሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑየማድረግጠቀሜታአለው | ከመምህራን | 5(83.3%) | 1(16.7%) |
| | | ከተማሪዎች | 152 (95 %) | 8 (5%) |

አራተኛው ከተራ ቁጥር 15 እስከ 17 የተዘረዘሩት ተላውጦዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ጠቀሜታ ለመማር ማስተማሩ ያላቸውን ጠቀሜታ የሚመለከት ሲሆን ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡ መምህራን የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ እየቀያየሩ በሚጠቀሙ ጊዜ የተማሪዎች ተሳትፎ ይጨምራል ለሚለው ጥያቄ 5(83.35(83.3%) መምህራንና 151 ( 94.45(83.3%) ተማሪዎች ተሳትፎን የሚጨምር መሆኑን ሲገልጹ 1(16.7%) መምህርና 9(5.6) ተማሪዎች ግንተሳትፎን የማይጨምር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴ የመገምገም ችሎታን ለማሳደግ ወዘተ. ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ለሚለው ጥያቄ 5(83.3%) መምህራንና 152(95%) ተማሪዎች ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ሲገልጹ 1(16.7%)መምህራንና 8(5%)ተማሪዎች ግን የማይጠቅም መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን በክፍል ውስጥ መጠቀም የመምህሩን ጉልበትና ጊዜ ይቀንሳል ለሚለው ጥያቄ 5(83.3%) መምህራንና 152(95%) ተማሪዎች ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ሲገልጹ 1(16.7%) መምህራንና 8(5%) ተማሪዎች ግን የማይጠቅም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ የጽሁፍ መጠይቅ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ለመማር ማስተማሩ ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም 83.3% መምህራንና 94.8% ተማሪዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ለመማር ማስተማሩ

ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን ሲገልጹ 16.7% መምህራንና 5.2% ተማሪዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ለመማር ማስተማሩ ጠቀሜታ የሌላቸው መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

### 4.1.3.10 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች

የመጽሀፉን ይዘት ለማስተማር የተሰጠው ጊዜ አለመጣጣም፤ የክፍል ተማሪ ጥምርታ ያለመጣጣም ችግር ፤ ከማስተማሪያ መሳሪያዎችና ከስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ጋር የተያያዘ ችግር፤ለመምህራን የስራ ላይ ስልጠና ያለመስጠት ችግር እንደሆኑ በምዕራፍ ሁለት ተገልጽዋል፡፡

### ሰንጠረዥ4.19 አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች በቁጥርና በመቶኛ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የጥያቄዎቹ ምላሽ በአሀዝና በፐርሰንት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መረጃው የተሰበሰበው | 4እና3(%) | 2 እና1(%) |
| 18 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ተግባራዊማድረግመምህሩየእለቱንየትምህርትይዘትለማከናዎንየጊዜእጥረትአጋጥሟቸዋል | ከመምህራን | 3(50%) | 3(50%) |
| | | ከተማሪዎች | 155(96.9%) | 5 (3.1%) |
| 19 | በክፍልውስጥየወንበር አደረጃጀት ባለመኖሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር አስቸግሯል፡፡ | ከመምህራን | 5(83.3%) | 1(16.7%) |
| | | ከተማሪዎች | 153(95.6%) | 7(4.4%) |
| 20 | በክፍልውስጥየተማሪዎች ቁጥር በመብዛቱ አሳታፊ የማስተማሪያዘዴዎችንለመተግበር አስቸግሯል ፡፡ | ከመምህራን | 5(83.3%) | 1(16.7%) |
| | | ከተማሪዎች | 154(96.2%) | 6 (3.8%) |
| 21 | መምህሩክፍሉ ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለማግኘት ችግር ገጥሞታል ፡፡ | ከመምህራን | 4(66.7%) | 2(33.3%) |
| | | ከተማሪዎች | 152 (95%) | 8(5%) |

አምስተኛው ከተራ ቁጥር 18 እስከ 21 የተዘረዘሩት ተላውጦዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮችን የሚመለከት ሲሆን ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ መምህሩ የእለቱን የትምህርት ይዘት ለማከናዎን የጊዜ እጥረት አጋጥሞታል ለሚለው ጥያቄ 5(83.3%) መምህራንና 155(96.9%) ተማሪዎች የጊዜ እጥረት ያጋጠመ መሆኑን ሲገልጹ 1(16.7%) መምህራንና5(3.1) ግን የማያጋጥም መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የወንበር አደረጃጀት ባለመኖሩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር አስቸግሯል ለሚለው ጥያቄ 5(83.3%) መምህራንና 153(95.6%) ተማሪዎች አስቸጋሪ መሆኑን ሲገልጹ 1(16.7%) መምህራንና 7(4.4%) ግን የማያስቸግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር መብዛቱ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ያስቸግራል ለሚለው ጥያቄ 5(83.3%) መምህራንና 154(96.2%) ተማሪዎች አስቸጋሪ መሆኑን ሲገልጹ 1(16.7%) መምህራንና 6(3.8%) ተማሪዎች ግን የማያስቸግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ መምህሩ ክፍሉ ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ያለማግኘት ችግር ገጥሞታል ለሚለው ጥያቄ 4(66.7%) መምህራንና 152(95%) ችግር ያጋጠመ መሆኑን ሲገልጹ 2(33.3%) መምህራንና 8(5%) ግን ቸግር የማያጋጥም መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ የጽሁፍ መጠይቅ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ሙሉ ለሙሉም ባይሆንም ችግር የሚገጥም መሆኑን ያሳያል፡፡ ምክንያቱም 79.2% መምህራንና 95.9% ተማሪዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ችግር የሚገጥም መሆኑን ሲያሳይ 20.8% መምህራንና 4.1% ተማሪዎች ግን ችግር የማይገጥም መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

### 4.1.3.11 በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች አጠቃላይ የሆነ የውጤት ትንተና

ከ4.1.4.1 እስከ 4.1.4.10 በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር እና በተማሪዎችተሳትፎ ተዛምዶ በተከናዎነው የክፍል ውስጥ ምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች በአማካይ በቁጥርና በመቶኛ የውጤት ትንተና ቀርቧል፡፡ ይህም በአጥኝው፣በመምህራንና በተማሪዎች የተሰበሰበው መረጃ በጥያቄዎቹ አይነት በማደራጀት ተጨምቆ በጥናቱ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ አስገኝተዋል፡፡

## ሰንጠረዥ 4.20 በምልከታና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች አጠቃላይ የሆነ የውጤት ትንተና

| ተ.ቁ | ተላውጦዎች | በምልከታ አዎንታዊ | በጽሁፍ መጠይአዎንታዊ ምላሽ | | | በምልከታአሉታዊ | በጽሁፍመጠይቅአሉታዊ ምላሽ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በአጥኚው | በመምህራን | በተማሪዎች | | በአጥኚው | በመምህራን | በተማሪዎች | |
| | | 24 ክ/ጊዜ | 6መምህራን | 160 ተማሪዎች | አማካይ | 24 ክ/ጊዜ | 6መምህራን | 160ተማሪዎች | አማካይ |
| 1 | የመምህራን አተገባበር | 64.58% | 55.6% | 74.6% | 64.9% | 35.42 % | 44.4% | 25.6 % | 35.1% |
| 2 | የተማሪዎች ተሳትፎ | 60.42 % | 45.8% | 73.5% | 59.9% | 39.58 % | 54.2% | 26.5 % | 40.1% |
| 3 | ስነ-ጽሁፍ አስተዋጽኦ | 83.33% | 58.4% | 95.45% | 79.1% | 16.67 % | 41.6% | 4.55 % | 20.9% |
| 4 | አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ጠቀሜታ | 65.3% | 83.3% | 94.8% | 81.1% | 34.7% | 16.7% | 5.2% | 18.9% |
| 5 | ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች | 63.6% | 79.2% | 95.9% | 79.6% | 36.4% | 20.8% | 4.1% | 20.4% |

የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከፍተኛ ነው፡፡ ይኸውም 64.9% የተተገበር ሲሆን 35.1% ግን ያልተተገበረ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል ፡፡

ተማሪዎች ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅመው ሲማሩ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መካከለኛ ነው፡፡ ይኸውም 59.9% የተሳተፉ ሲሆን 40.1% ግን ያልተሳተፉ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡

የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለው ተዛምዶ ሰንጠረዥ4.3 በምልካታ .855 እንዲሁም ሰንጠረዥ4.8 በጽሁፍ መጠይቅ .857 የተገኘው የውጤት ትንተና መሰረት አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ (ጠንካራ) ተዛምዶ ያለው መሆኑ በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ዘዴ ተረጋግጧል፡፡

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ያላቸው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ይኸውም 79.1% አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ሲያመለክት 20.9% ግን አስተዋጽኦ የሌለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል ፡፡

በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ጠቀሜታ በጣም ከፍተኛ ነው። ይኸውም 81.1% ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ሲያመለክት 18.9% ግን ጠቀሜታ የሌለው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል ።

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ከፍተኛ ነው። ይኸውም 79.6% ችግሮች ያሉ መሆኑን ሲያመለክት 20.4% ግን ችግሮች የሌሉ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል ።

## 4.1.3.12 በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበ መረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ሶስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለመጠይቅ ሲሆን በክፍል ውስጥ ምልከታ የተሰበሰበውን መረጃ ለማጠናከር ሲባል የቀረቡ ናቸው ። በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ ተዛምዶ ዙሪያ ለመምህራን በቀረበ ቃለ-መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ አይነታዊ በሆነው የገለጻ ስልትተተንትኗል።

በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ስነ-ጽሁፋዊስራዎች አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመተግበር ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል? ካለዎት ልምድ ተነስተው ሀሳበዎትን ቢገልጹልኝ? ለሚለው ጥያቄ የተሰጠ መልስ

1. ስነ-ፅሁፎች የፈጠራ ስራዎች ናቸዉ ። እነዚህ የፈጠራ ስራዎች የሰዉን ልጅህይወት ፍንትዉ አድርገዉ የማሳይት ብቃት አላቸዉ። ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ለስሜት ቅርብ የሆኑና ምስል ከሳች በመሆናቸዉ የሰዎችን ቀልብ ይስባሉ፤ይማርካሉ። ተማሪዎችም ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ ያደርጋሉ። ስለዚህ፣ ለመማር ንቁ ተሳታፊም ይሆናሉ። በመሆኑም ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን በክፍል ዉስጥ ለመተግበር ጠቀሜታአለው። በልምድ ያገኘሁት ነገር ቢኖር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ለማድረግና የቋንቋን ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የስነ-ፅሁፍ ስራዎችን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ችያለሁ። ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ የተማሪዎቹ ተሳትፎ ሲቀንስ ለእነሱ የሚመጥን የስነ-ፅሁፍ ቅንጫቤ በመጠቀም ቋንቋዉን ለማስተማር ጥረት አደርጋለሁ። በማድረጌም ዉጤታማ እሆናለሁ።

እኔ እስከማዉቀዉ ድረስ ከኢ-ስነፅሁፋዊ ስራዎች ይልቅ ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ተስማሚ ናቸው። ምክንቱም ስነጽሁፎች በባህሪያቸው ካስተማሪነታቸው ጎን ለጎን

አዝናኝም ናቸዉ። ይህ ባህሪያቸዉ በክፍል ዉስጥ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት በማነሳሳት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

ባለኝ የስራ ልምድ አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ስነ-ፅሁፍን እንደመሳሪያ መጠቀም የላቀ አስተዋፅዖ እንደሚበረክቱና አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ዉስጥ ለመተግበር ስነ-ፅሁፎች የላቀ ብቃት እንዳላቸዉ ተረድቻለሁ፡

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች ተማሪዎች የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ በነጻነት ስሜታቸውን የሚገልጹበት በመሆኑ አሳታፊ የመማር ማስተማር ስነዘዴን ለመተግበር በእጂጉ ጠቃሚዎች ናቸው።

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን የመናገር ልምድ፣ የመከራከር፣ የመዎያየት ልምድ በማዳበር ፍርሃትን ለማስዎገድ ይጠቅማል ።

ከዚህ በላይ ለጥያቄ አንድ ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች 6 (100%) መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይኸውም ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ ዘዴን ለመተግበር ጠቃሚ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ሆነው ተገኝተዋል። ከዚህ ውጤት በመነሳት ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳላቸው ከመምህራን በተገኘ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል።

2. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አዘውትረው ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የማስተማሪያ ዘዴ ኢ-አሳታፊ ወይስ አሳታፊ የትኛውን ነው? አዘውትረው ተግባራዊ የሚያደርጉበት ምክንያት ለምን እንደሆነ ቢገልፁልኝ?

በክፍል ውስጥ ይህኛውን ብቻ አዘውትሬ እተገብራለሁ ለማለት እቸገራለሁ። ምክንያቱም የማስተማሪያ ስነዘዴው የሚዎሰነው በእለቱ የትምህርት ይዘት ላይ ተመርኩዞ ነው። ስለሆነም እንደይዘቱ ባህሪ የተለያየ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እተገብራለሁ።

በአብዛኛው ኢ-አሳታፊ (በመምህር ብቻ የሚቀርብ ገለጻ) ነው የምጠቀመው። ምክንያቱም ከጊዜ እጥረት፣ ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር በገለጻ የመማር ማስተማር ዘዴእተገብራለሁ ።

እንደሁኔታው አመችነት የሚከዎን ነው። ተማሪዎች ተወያይተው ሃሳብ እንዲያመነጩ በሚፈለግበትጊዜ፣ በጥያቄና መልስ በትምህርት መካከል እንዲነቃቁ ለማድረግ፣ክትትላቸው ምን ያህል እንደሆነ ለመረዳትና ለማገዝ አሳታፊ ዘዴን እተገብራለሁ። የእለቱን የትምህት ይዘት ለመሸፈን አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ግን የገለጻን ስልት ብቻ እጠቀመቀለሁ።

እንደ ሁኔታው መፃሃፉ ላይ የሚገኙት ይዘቶች ይወስኑታል።ማለታም ለይዘቱ ቅርብ የሆነውን የማስተማሪያ ዘዴዎችን እንዳስፈላጊነቱ እጠቀማለሁ።

አልፎ አልፎ አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ብጠቀምም በአብዛኛው ግን ኢ-አሳታፊ ዘዴን እጠቀማለሁ።ምክንያቱም የተማሪዎች ብዛት፣ የመፃህፍት እጥረት እንዲሁም ለትምህርቱ ያላቸው ትኩረት አናሳ መሆኑ ተጠቃሽ ናቸው።

በአብዛኛው ኢ-አሳታፊ ተግባርን እጠቀማለሁ።ምክንያቱም በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር ብዛትና የጊዜ እትረት መኖር ኢ-አሳታፊ ዘዴን እንድተገብር አድርጎኛል።

ከዚህ በላይ ለጥያቄ ሁለት ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች 2(33.3%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።ይኸውም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አዘውትረው ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የማስተማሪያ ዘዴ እንደትምህቱ ይዘት የተለያዩ አሳታፊ ዘዴዎችን እንደሚጠቀሙ የገለጹ ሲሆን 4(66.7%) ደግሞ እንደትምህርቱ ይዘት ሳይሆን ከተማሪው ቁጥር አንፃር፣ ከጊዜ እጥረት፣ ከተማሪዎች ፍላጎት አንፃር ፣በመፃህፍት እጥረት ምክንያት ኢ-አሳታፊ (በመምህር ገለጻ) እንደሚተገብሩ ከመምህራን በተገኘ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል።

3. በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡትን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ተጠቅመው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠመዎት ችግሮች አሉ? ካሉ ምንድን ናቸው?

ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠሙኝ ችግሮች አሉ።እነሱም፡-የመማሪያ ክፍሉ ምቹ አለመሆን (አቀማመጥ)፣ የተማሪዎች ፍላጎት አናሳ መሆን፣ ለክፍለ ጊዜው የተመደበው ይዘትና የክፍለ ጊዜው ርዝማኔ አለመጣጣም ጥቂቶቹ ናቸው።

ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠሙኝ ችግሮች አሉ። የጊዜ መጣበብ እንዲሆም ከተማሪዎች ፈቃደኛ አለመሆን ጋር ተያይዞ ለመተግበር አስቸጋሪ ያደርገዋል።
ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠሙኝ ችግሮችአሉ።የወንበርአቀማመጥ ለእንቅስቃሴ አመች ሆኖ አለመሰራት ማለትም ለየግል የተሰራ ባለመሆኑእንደልብ ማንቀሳቀስ የማይቻልመሆኑአንዱችግር ነው።

ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠሙኝ ችግሮችአሉ፡፡ተማሪዎች ንቁ የሆነ ተሳትፎ አለማድረግ፣ስሜታቸውን ለመግለጽ የፍርሀት ስሜት መኖር፣ የአቀማመጥ ችግር፣ የመጽሀፍትና ሌሎችም ችግሮች አሉ፡፡
ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠሙኝ ችግሮች አሉ፡፡ ተማሪዎች ለትምህርቱ ትኩረት አለመስጠት፣የጥንድና የቡድን ተግባራትን ለማሰራት የተማማሪዎች ቁጥር መብዛት ከችግሮቹ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡
ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሜ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያጋጠሙኝ ችግሮች አሉ፡፡ የጊዜ እጥረት እንዲሁም በክፍል ውስጥ የተማሪ ቁጥር መብዛት ዋናዎቹ ችግሮች ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ ለጥያቄ አራት ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች 6(100%)አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይኸውምየተማሪ ክፍል ጥምርታ አለመመጣጠን‹‹ የጊዜ እጥረት ፣ የወንበሩ አቀማመጥ ምቹ አለመሆን፣ በቂ መፃህፍት አለመገኘት ዋናዎቹ መሰናክሎች መሆናቸውን ከቃለ መጠይቁ የተገኘዉ መረጃ ያሳያል ፡፡ እነዚህ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸዉ መምህራን

ለዘረዘሩዋቸዉ መሰናክሎች በራሳቸዉ ያስቀመጣችሁላቸዉ መፍትሄዎች ካሉ ተብለዉ ለተጠየቁትም በእነሱ አቅም ችግሮቹን ሙሉ በሙሉ መፍታት እንደማይቻል ጠቁመዉ ነገርግን ጊዜያዊ መፍትሄ ያሏቸዉን እንዲህ በማለት ገልጸዋል፡፡ በርካታ ተማሪዎችን በተናጥል ለማሳተፍ ከባድ በመሆኑ ከቡድን አባላት መካከል ለአንድ ተማሪ ብቻ እድል በመስጠት የሌሎችንም ሀሳብ እንዲገልፅ ማድረግ፤ የጊዜ እጥረትን ለመፍታት ባላቸዉ የእረፍት ስዓት ተማሪዎችን በመጥራት ተጨማሪ ጊዜን ተተቅሞ ማስተማር፤የወንበሩ አቀማመጥ ለቡድን ስራ አመች ባይሆንም ሁለቱን ዴስኮች አዙሮ በመግጠም በቡድን የሚያዩበትን መንገድ ማመቻቸት ፤የግል መፅሀፋቸዉንም ጭምር በማዋስና ኮፒ በማስደረግ ችግሩን ማቃለል እና መምህራን የእርስ በርእስ ሱፐርቪዥን በማድረግና ልምድ በመለዋወጥ ለችግሮቹ ጊዜያዊ መፍትሄ ያሏቸውን ገልፀዋል፡፡

4. የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው? በክፍል ውስጥ የሚተገበሩ የማስተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን ሁኔታ ያጣጣመ ሆኖ ስለሚቀርብ ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ አለው ፡፡

የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው፡ ምክንያቱም ምንም በማይሳተፉ ተማሪዎች መምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር አስቸጋሪ ነው፡፡

የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው፡ ምክንያቱም መምህሩ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሲተገብሩ የተማሪዎች ተሳትፎ የበለጠ ይጨምራል፡፡

የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው፡ ምክንያቱም አተገባበሩ ለተማሪዎች ምቹ ካልሆነ የተማሪዎች ተሳትፎ ይቀንሳል፡፡

የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው፡፡ ምክንያቱም አተገባበሩ ለተማሪዎች ግልጽ ወይም ውስብስ ከሆነ ተማሪዎች ሊሰሩም ሆነ ሊከታተሉ አይችሉም፡፡

የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው፡ ምክንያቱም አተገባበሩ ተማሪዎችን የሚስብ ከሆነ ተማሪዎች በንቃት ይሳተፋሉ፡፡

ከዚህ በላይ ለጥያቄ አምስት ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች 6(100%) አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይኸውም ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ አለው፤ የተማሪዎቸ ተሳትፎ የበለጠ እንዲጨምር ያደርጋልለ፤በአጠቃላይ የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ እንዳለው ከመምህራን በተገኘ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረበው በቃለ-መጠይቅ የተገኙት መረጃ ትንታኔ እንደሚከተለው ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ ዘዴን ለመተግበር አስተዋጽኦ ያላቸው መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ስለሆነም ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ከመምህራን በተገኘ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አዘውትረው ተግባራዊ የሚያደርጓቸው የማስተማሪያ ዘዴ እንደትምህቱ ይዘት እንደሚለያይ የተገለጸ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ግን እንደትምህርቱ ይዘት ብቻ

ሳይሆን ከተማሪው ቁጥር አንፃር፣ ከጊዜ አንጻር ወዘተ.ኢ-አሳታፊ ዘዴን እንደሚተገብሩ ከመምህራን በተገኘ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

አሳታፊ የማስተማሪ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ ግንኙነትን ለመመስረት ያለውን ጠቀሜታ በአብዛኛዎቹ መምህራን እንደተገለጸው በመምህራንና በተማሪዎች መካከል እንዲሁም በተማሪዎችና በተማሪዎች መካከል ያለው ግንኙነት (ማህበራዊ አቀራረብ) ለመፍጠር ከፍተኛ ነው ሲሉ የተወሰኑት ግን ግንኙነት ለመፍጠር ዝቅተኛ እንደሆነ ከመምህራን በተገኘ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡትን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ተጠቅሞ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ያጋጠሙ ችግሮች እንዳሉ ከመምህራን በተገኘ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ እንዳለው ከመምህራን በተገኘ የቃለ-መጠይቅ መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ ለመተግበር የላቀ አስተዋጽዖ ያላቸው መሆናቸውን ያሳያል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ2005 ዓ.ም በስራ ላይ በዋለው በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነበር፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስና የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይረዳ ዘንድ ጥናቱ በሚካሄድበት ቦታ በሚገኙ በልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በመካነ እየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ10ኛ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች በምልከታ፣ በፅሁፍ መጠየቅ እንዲሁም በቃለ መጠይቅ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል፡፡ በመሆኑም በምልከታ፣ በፅሁፍ መጠየቅና በቃለ መጠይቅ መረጃዎች መሰረት የመምህራን አተገባበር፣የተማሪዎች ተሳትፎ፣ የስነጽሁፍ አስተዋጽኦ፣ የአሳታፊ ዘዴዎች ጠቀሜታና አሳታፊ ዘዴዎችን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች በሚሉ ተላውጦዎች ከስነ-ጽሁፍ ስራዎች /ከጥገኛ ተላውጦው/ ጋር ጉልህ ተዛምዶ እንዳለው በፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ ዘዴ ተሰልቶ ተተንትኗል፡፡ በተጨማሪም ከመምህራን በቃለ መጠይቅ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ የመማር ማስተማር ዘዴን ለመተግበር ያላቸው ጠቀሜታ ምን ይመስላል? በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አዘውትረው ተግባራዊ የሚያደርጓቸው

የማስተማሪያ ዘዴ የትኞቹ ናቸው?፣ የቀረቡትን ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ተጠቅመው አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያጋጠሙ ችግሮች ምንድን ናቸው? መፍትሄው ምን ሊሆን ይችላል? የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋርተዛምዶ አለው? የሚሉትን ጉዳዮች ለመፈተሽ በገላጭ ስታቲስቲክስ ተተንትኗል፡፡ ከትንተናው በፊትም የመጠይቆቹ አስተማማኝነት በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ዘዴ ቀመር ተሰልቶ ለመምህራን የቀረበው የመጠይቅ ውጤት 0.86 ሲሆን ለተማሪዎች የቀረበው መጠይቅ ደግሞ 0.81 ሆኗል፡፡ይህም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያው አስተማማኝ መሆኑን ያመለክታል ፡፡

በምልከታ እንዲሁም ለመምህራንና ለተማሪዎች የቀረቡት የፅሁፍ መጠይቆች የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለውን ተዛምዶ ለመመርመር ሲሆን የተገኘው መረጃ ጉልህ ተዛምዶ እንዳላቸው በዝምድና ማሳያ (spss)ተረጋግጧል፡፡ ይኸውም በምልከታ እንዲሁም በጽሁፍ መጠይቁ መምህራንና ተማሪዎች ስለመምህሩ የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና ስለተማሪዎች ተሳትፎ ያለውን ተዛምዶ በሰጡት ምላሽ መካከል ጉልህ ተዛምዶ ታይቷል፡፡ በምልካታ ($r=0.855$, $p<0.05$) ከመምህራን በጽሁፍ መጠይቅ (0.857) እንዲሁም ከተማሪዎች (0.385) የተገኘው የውጤት ትንተና መሰረት አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ (ጠንካራ) ጉልህ ተዛምዶ ያለው መሆኑ በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያዘዴ ተረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ በመምህሩ የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል ጉልህ ተዛምዶ አለ፡፡ አዎንታዊ ጉልህ ተዛምዶው የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ጥሩ ካልሆነ ወይም ዝቅተኛ ከሆነ የተማሪዎች ተሳትፎም ዝቅተኛ ይሆናል ፡፡ እንዲሁም የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ጥሩ ከሆነ ወይም ከፍተኛ ከሆነ ተማሪዎች በንቃት ይሳተፋሉ ወይም የተማሪዎችም ተሳትፎ ከፍተኛ ይሆናል ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር የተማሪዎች ተሳትፎ እንዲጨምር ወይም እንዲቀንስ ያደርጋል ወደሚል ማጠቃለያ የሚያደርስ ይሆናል፡፡ ይህም ውጤትLewis and hill (1985)የሰጡትን ሃሳብ የሚደግፍ ነው፡፡ ይኸውም የመምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴአተገባበርየተማሪዎችን ተሳትፎ ይወሰናል፡፡ መምህሩ ጥሩ የሆነ አተገባበር ካለው ተማሪዎች በንቃት ይሳተፋሉ፡፡ በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎ መኖሩ ደግሞ መምህሩ በበለጠ ጥሩ ሁኔታ ትምህርቱን እንዲያቀርብ ያበረታተዋል በማለት ካቀረቡት ሀሳብ ጋር ተደጋጋፊነት አለው፡፡

በውጤት ትንተናው የቀረቡት አተገባበር፣ተሳትፎ፣ስነፅሁፍ አስተዋጽኦ፣ አሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ናቸው ከቀረበው የተዛምዶ ትንተና ውጤት ማስተዋል እንደሚቻለው በጥገኛ ተላውጠውና በንዑስ ተላውጠዎች መካከል ካለው የተዛምዶ ጉልህነት ደረጃ ለመጀመር ያህል ከሰንጠረዥ 4.1 እስከ ሰንጠረዥ4.6 ከቀረበው የተዛምዶ ትንተና ውጤት ማስተዋል እንደሚቻለው በጥገኛ ተላውጠውና በንዑስ ተላውጠነት በተካተቱት መካከል ደረጃው ቢለያይም ተዛምዶ መኖሩ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡

ሰንጠረዥ4.7 በምልከታ፣ሰንጠረዥ4.8 እና 4.9 በጽሁፍ መጠይቅ በፒርሰን ተዛምዶ መለኪያ ዘዴ በጥገኛ ተላውጠዎች መካከል ያለው ተዛምዶ ትንተና የደረጃ መለያየት ቢኖርም ተዛምዶ እንዳለ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ ይኸውም፡- የመምህራን አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር አዎንታዊና በጣም ከፍተኛ የሆነ (ጉልህ) ተዛምዶ እንዳለው በምልከታና በጽሁፍ መጠይቁ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል፡፡ በአንፃሩ ከስነፅሁፍ ጠቀሜታና ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ ጋር ተዛምዶ ቢያሳይም ጉልህ ግን አይደለም:: የተማሪዎች ተሳትፎ ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታ ጋር፣ ከስነፅሁፍ ጠቀሜታና ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች ጋር በምልከታና በጽሁፍ መጠይቁ ከተገኘው መረጃ መካከለኛ የሆነ ተዛምዶ አሳይቷል፤ በአጠቃላይ በጥገኛ ተላውጠዎች መካከልም ይሁን በንዑስ ተላውጠዎች መካከል ያለው ዝምድና በአብዛኛው የጉልህነት ደረጃ (Level of significance/ P-value <0.05)ነው፡፡

ይህ ጥናት የመምህራን አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ተዛምዶ አለው ከሚሉት Teachlng center (2009), Elliott and etal (2000),millis and cottor (1998) and Bligh (2000) የጥናት ውጤቶች ጋር ተመሳስሏል፡፡ ለተማሪዎች ተሳትፎ ከአሳታፊ የማስተማሪያ ዜዴ ጠቀሜታና ስነፅሁፍ ስራዎች ጠቀሜታጋር በጣም ዝቅተኛ የሆነ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ይህም ተዛምዶ አለው ከሚሉት Lazar(1993),Carter and Long (1991) Millis and Cottor (1998),Bligh (2000)እና በድሉ(2007) የጥናት ውጤቶች ጋር ተቃርኗል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ምናልባት የመማር ማስተማሩ ሂደት የቀረበበት ማስተማርያ ዘዴ፣በክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት፣ የማስተማሪያ ቁሳቁስ ወዘተ ተመሳሳይ ባለመሆናቸው ሊሆን ይችላል:: አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ጋር በጣም ዝቅተኛ የሆነ ተዛምዶ አሳይቷል፡፡ ማለትም አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር የተለያዩ ችግሮች እንዳሉ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ Silvareman(1996), Shank (1999) እና Jones(2004) ጋር ከጥናቱ ውጤቶች ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡በዚህ ረገድ ከሰንጠረዥ4.7፣4.8 እና 4.9 መመልከት እንደሚቻለው አብዛኛዎቹ ንዑስ ተላውጠዎች

ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ያላቸው ግንኙነት ቀጥተኛ (Direct) ተዛምዶ ያላቸው ናቸው። ከጥገኛ ተላውጠው ጋር ተገላቢጧዊ (Inverse) የሚባል ዝምድና ያላቸው ንዑስ ተላውጦዎችም ይገኛሉ። በተጨማሪም በተዛምዶ ጥናት ሌላኛው ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ በተላውጦዎ ች መካከል ያለው የግንኙነት መጠን ነው።በዚህ መሰረት በሰንጠረዥ4.7 የቀረቡት ውጤቶች እንደሚያሳዩት በተላውጦዎች መካከል ያለው ግንኙነት በስህተት ይሁንታ መለኪያው መሰረት የአዛኛዎቹ ከ0.05 በላይ ሲሆን፣ከስህተት ይሁንታው የጥንካሬ ደረጃ አንፃር በንዑስ ተላውጦዎችና በጥገኛ ተላውጠው መካከል የጥንካሬ ደረጃ ይለያይ እንጅ ግንኙነት እንዳለ የሚያመለክት ነው። የምመህራን አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ከፍተኛ የሆነ ግንኙነት አለ። ይህ ከአባይ (1994) ጋር ተቃራኒ ነው። ይኸውም መምህራን ጭራሽ ሞያቸውን የዘነጉና የመምህርነትን ስነምግባር የተላበሱ አይደሉም። መምህራን ክፍል ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ ምንና እንዴት እንደሚያስተምሩ ስለማያውቁት እንዲሁም ተማሪዎችና መምህራን ያላቸው ቀረቤታ የገዥና የተገዥነት አይነት እንጂ እናታዊ እና አባታዊ በሆነ መልኩ አለመሆኑን በጥናታቸው አሳይተዋል። ፍቅሬ (1994) በርካታ ተማሪዎች በሚገኙበት ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የቡድን ውይይትን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ያሳየ ቢሆንም በዚህ ጥናት ውጤት ግን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴን ለመተግበር በክፍል ውስጥ የተማሪው ቁጥር መብዛት አንዱ ችግር መሆኑን አሳይቷል። አሳየ (1997) የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው የሚል ነው። ይኸውም መምህራን በክፍል ውስጥ አብዛኛውን ክፍለ ጊዜ ብቻቸውን እንደሚሸፍኑ ጥናቱ ያመላከተ ሲሆን የዚህ ጥናት ውጤት የሚያሳየው ደግሞ ከመምህሩ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ጋር ግንኙነት እንዳለው አሳይቷል።

## ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያ፤ በጥናቱ የተደረሰበት መደምደሚያና ከጥናቱ ውጤት በመነሳት በእጥኝው የተሰነዘሩ መፍትሄዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ10ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ ስነ-ጽሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በመካነ እየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም በመደበኛው መርሃ ግብር በመማር ማስተማር ላይ በሚገኙ የ10ኛ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ በዚህም የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያላቸውን ተዛምዶ ተፈትሿል፡፡ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ መረጃዎች ከአጥኝው ከመምህራንና ከተማሪዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከእነዚህ የመረጃ ምንጮች መረጃዎችን ለመሰብሰብ ደግሞ ምልከታ፣ የፅሁፍ መጠየቅና ቃለ መጠይቅ ተመርጠዋል፡፡ ለምልከታ የተዘጋጀው ቅፅና የፅሁፍ መጠይቁ የዋናውን ጥናት መረጃዎች ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት በአማካሪ ተገምግሟል በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴው ላይ ክለሳና ማሻሻያ ተደርጎበት የዋናው ጥናት መረጃዎች ተሰብስቦበታል፡፡ ለዋናው ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመስጠት በልዋዬ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በመካነ እየሱስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም በመማር ማስተማር ላይ በሚገኙ የ10ኛ ክፍል መምህራን ሴት 3 ወንድ 3 በድመሩ 6፤ ተማሪዎች ወንድ 90 ሴት 90 በድምሩ 180 የተሳተፉ ሲሆኑ፤ ነገርግ የጽሁፍ መጥይቁን ሴት 11 ወንድ 9 በድምሩ 20 ተማሪዎች የአሞላል ስህተት መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ በጥናቱ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ በተጨማሪም በአጥኝው 24 ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ምልከታ ተደርጓል፡፡በዚህ መሰረት ይህ ጥናት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥቷል ፡፡

1.ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር ያላቸው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል ?

2.ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማሳደግ ያለው ጠቀሜታ ምን ይመስላል?

3.መምህራን ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን በመጠቀም የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል ?

4.ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ ችግሮች ምን ሊሆኑ ይችላል? የሚሉ ሲሆን

የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሰረት በማድረግ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል ጉልህ ተዛምዶ መኖሩን በምልከታና በጽሁፍ መጠይቁ ተረጋግጧል፡፡ የጽሁፍ መጠይቁ በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡ በክፍል ውስጥ ምልከታው የተገኘው መረጃ ውጤት እንደሚያመለክተው መምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ሲተገብሩ አብዛኛዎቹ እንደትምህርቱ ይዘት እየቀያየሩ ሲጠቀሙ አንዳንዶቹ ግን በተለያዩ ምክንያቶች የተለያዩ ዘዴዎችን ለመጠቀም እንደተቸገሩ በተገኘው ውጤት ተስተውሏል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የተማሪዎች ተሳትፎ መካከለኛ እንደሆነ በምልከታውና በጽሁፍ መጠይቁ ተረጋግጧል፡፡ ይህም የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር የጠበቀ ተዛምዶ ያላቸው መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል ፡፡

ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማሳደግ አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን በምልከታ፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቁ የተገኘው የውጤት ትንተና አሳይቷል፡፡ ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎችን ተጠቅሞ በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር የሚያጋጥሙ የተለያዩ ችግሮች እንዳሉ በጥናቱ የተገኘው የውጤት ትንተና አሳይቷል፡፡ በአጠቃላይ አሳታፊ የማሳተማሪያ ዘዴዎች የተማሪዎችን ተሳትፎ የሚያጎለብት ቢሆንም ለመተግበር ግን ሙሉ በሙሉም በይሆን ችግሮች እንዳሉ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

ከጥናቱ ውጤቶች በመነሳት አጥኚው ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ደርሷል ፡፡

- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር በምልከታው፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጥይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ምንም እንኳን ችግሮች ቢኖሩም ጥሩ የሆነ አተገባበር እንዳለ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል ፡፡
- ✓ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በምልከታው፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጥይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች መካከለኛ እንደሆነ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡

- ✓ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር እና በተማሪዎች ተሳትፎ መካከል ያለው ተዛምዶ ጉልህ ተዛምዶ ያለው መሆኑን በምልከታውና በጽሁፍ መጠይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ተረጋግጧል ፡፡
- ✓ ስነ-ፅሁፋዊ ስራዎች አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመተግበር እና የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት ጠቃሚ እንደሆኑ በክፍል ውስጥ ምልከታው፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጥይቅ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማዎቅ ተችሏል ፡፡
- ✓ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች ለመማር ማስተማሩ ጠቃሚ ቢሆኑም ለመተግበር ግን የተለያዩ ችግሮች እንዳሉ ከጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሀሣብ

ጥናቱ ካነሳው ዋና ዓላማ አንፃር በምልከታ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ ከተሰበሰቡ በኂላ በተለያዩ ስታስቲክስ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች የተገኙት የጥናቱ ውጤቶች ላይ በመመርኮዝ ድምዳሜዎች ቀርበዋል፡፡ በዚህ ላይ በመመስረት የሚከተሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች አቅርቧል፡፡

- ✓ የመምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርና የተማሪዎች ተሳትፎ ጉልህ ዝምድና ያላቸው መሆኑን ይህ ጥናት አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም መምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበርን ምቹ በማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን በትኩረት እንዲከታተሉ፣ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ እና በቋንቋው ሰፊ ልምምድ እንዲያደርጉ ጥረት ቢያደርጉ፡፡
- ✓ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ተማሪዎችን የሚያሳትፍ መሆኑ ጥናቱ አመላክቷል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መምህራን የራሳቸውን የክፍል ውስጥ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበርም ሆነ የሌሎችን መምህራን አተገባበር ለመጎብኘት እንዲችሉ ልምድ የሚለዋወጡበት የትምህርት ኘሮግራም ቢዘጋጅ፡፡
- ✓ መምህራን፣የትምህር ክፍል ሀላፊዎች፣ ስርዓተ ትምህርት ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች የመምህራን አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎች አተገባበር ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር የጎላ ተዛምዶ ያለው መሆኑን ተገንዝበው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ዙርያ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የተለያዩ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ማቀድና መተግበር ቢቻል፡፡
- ✓ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የመምህራን ምጋቤ ምላሽና ማበረታቻ አስፈላጊ በመሆኑ መምህራን ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ሰጥተው ቢያስተምሩ፣መምህራን

ተማሪዎቻቸው የተለያዩ ልምድ ሊኖራቸው እንደሚችል በመረዳት የትምህርት ይዘቶችን በተለያዩ ዘዴዎች በማቅረብ ተማሪዎችን በልዩ ልዩ ተግባራት ማሳተፍ ቢችሉ፡፡

በመጨረሻም ይህ ጥናት በአንድ ወረዳ ውስጥ በሁለት ትምህርት ቤቶች በአስረኛ ክፍል መምህራንና ተማሪዎች ብቻ የተወሰነ በመሆኑ መምህራንም ሆኑ የትምህርት ባለሙያዎች ከዚህ የጥናት ውጤት በመነሳት በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ጥልቀትና ስፋት ባለው መልኩ ጥናት ቢያደርጉ፡፡

# ዋቢዎች (References)


*አሳየ ገ/ወልድ፡፡(1997)፡፡‹‹ በፋሲሎና በጣና ሐይቅ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የተማሪዎች የክፍል ውሰጥ ተሳትፎ ምን ይመስላል»?*

*ወንደወሠን አዳነ፡፡(1995)፡፡‹‹አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር ሲቲ» ፡ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ፣ ኤም.ኤ.ቲስስ ፡፡ (ያልታተመ)፡፡*

*በድሉ·ዋቅጅራ፡፡(1996)፡፡በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡*

*በድሉ·ዋቅጅራ፡፡(2007)፡፡በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ ንግድማተሚያ ድርጅት፡፡*

ትምህርት ሚኒስቴር፡፡(1989)፡፡ ‹‹በኢትዮጵያ ትምህርት ጥናታዊ ግምገማ፤የስርዓተ ትምህርት ዝግጅትና የመማር ማስተማር ሂደት ጥናታዊ ሪፖርት»፡፡ የስነጽሁፋዊ ይዘቶችፋይዳ፣አመራረጥና አደረጃጀት፡፡ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የቀረቡትን የ7ኛና የ8ኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርቶች ለማሻሻል በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ፡፡ ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዮት (ያልታተመ)፡፡

ዘመንፈስ ባራኪ፡፡(1991)፡፡ ‹‹በስነ-ጽሁፍ አማካኝነት የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና›› አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡(ያልታተመ) ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡(1998)፡፡ *የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን፡ ፡* አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ያለው እንዳዎቅ፡፡(2007)፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር* ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፣ ተፈራ ስዩም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፍቅሬ ጌታቸው፡፡ (1994)፡፡ «የቡድን ውይይት ተግባራዊነትና ውጤታማነት በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በእንጦጦ ወንጌላዊት ትምህርት ቤት 8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ግለ ክፍል ምርምር፡፡»አዲስ አበባዩ ኒቨርሲቲ፡፡( ያልታተመ) ፡፡

*Ary, D., Jacobs, L. C., & Sorensen, C. (2010). Introduction to Research in Education(10th Ed.). Australia፡ Cengage Learning.*

*Bailey,K.m.and Nunan.D.(1996).voice From the Language classroom. Cambridge; Cambridge University press.*

*Berliner,D.andCalfee,R. (1996).Hand Book of Educational psychology.USA;USA printingpress.*

*Bligh'D.A(2000) what is the use of Lectures? San Francssco.,JosseY=Boss,,Inc.*

